ስለዚህ ክርስቲያኖች በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን አብረውን ከሚያመልኩና ከሚያገለግሉ ወንድሞችና እህቶች ጋር የሚኖረን ሕይወት በተግባር በሚገለፅ ርኅራኄ የተሞላ ቢሆን ዋናውን ክርስቲያናዊ ግዴታ ተወጣን ማለት ነው። እንግዲህ ክርስትናችን በእግዚአብሔር ርኅራኄ፥ በክርስቶስ ትምህርትና በቀደሙት ሐዋርያት ዘመን ምዕመናን ምሳሌነት የሚከተል መሆን ያለመሆኑን በሚከተሉት ዓይነት ጥያቄዎች እንመዝነው፡-

1. እግዚአብሔር ለእኔ ባደረገልኝ የርኅራኄ ዓይን ማየት ያለብኝ ወንድሞችና እህቶች እነማን ናቸው?

2. በርኅራኄ አገልግሎት ከጎሊና ወቀሳ ነፃ ነኝን?

3. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኔ ርኅራኄ ተግባራዊ እንዲሆን የሚጠበቅብኝ ድርሻ ምንድር ነው?

printed by SIM Press

ርኅራኄ

ሀ. የርኅራኄ መሠረት እግዚአብሔር ነው

እግዚአብሔር የርኅራኄ ምንጭ ነው። «እግዚአብሔር ርኅሩኅና መሀሪ ነው ለቁጣ የዘገየና በዘላለም ፍቅር የተሞላ ነው እርሱ ለሰው ሁሉ ቸር ነው ለፍጡሮችም ሁሉ ይራራል» መዝ. 145:8-9። የእግዚአብሔር ምሕረት ቸርነትና ርኅራኄው በቃል ደረጃ ተወስኖ የቀረ ሳይሆን በተግባር የተገለፀ ነው። «ያዳናቸው እርሱ ራሱ እንጂ መልአክን በመላክ አይደለም የመከራቸው ተካፋይ በመሆን በፍቅሩና በምህረቱ ብዛት ታደጋቸው ...» ኢሳ. 63:9።

የእግዚአብሔር ቸርነትና ምሕረት እንዲሁም ለተቸገሩት እና ላዘኑ ሰዎች ያለው ዕርዳታን የማድረግ ተግባሩ ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ አይደለም በምድር ላይ የሚገኙ ሰዎች ሁሉ እንዲሁም እንስሳትም ጭምር የምሕረቱ የቸርነቱና የርኅራኄው ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ፈቃዱ ነው። «ነነዌ አንድ መቶ ሃያ ሺህ ሕዝብ የሚኖሩባት ግራና ቀኙንም ለይተው የማያውቁ ሕፃናትና ብዙ እንስሳት የሚገኙባት ታላቅ ከተማ ናት ታዲያ እኔ ለዚህች ከተማ ማዘን አይገባኝምን? ዮናስ 4:11

ለ. ርኅራኄ በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን

የሐዋርያት ዘመን አማኞች የእግዚአብሔርን ምሕረት ቸርነትና ርኅራኄውን ለሌሎች በማካፈል ባላቸው ሕይወት የበኩላቸውን በማድረግ ምሳሌ ሆነዋል። እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ያደረገውን ምሕረት ቸርነትና ርኅራኄን በማሰብ እርስ በእርሳቸው ይተሳሰቡ ነበር። ክርስቲያናዊ ሕብረታቸውም በአምልኮ ጊዜ በሚታይ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ በመስጠት በመረዳዳትና በመተባበር የነበራቸው ሕብረት በተግባር ይገለፅ ነበር። «... ያላቸውም ሁሉ የጋራ ነበር መሬታቸውንና ንብረተታቸውን እየሸጡ ገንዘቡን ለእያንዳንዱ እንደሚያስፈልገው ያከፋፍሉ ነበረ ...» የሐዋ. ሥራ 2:44-45 «... ማንም ሰው ይህ የእኔ ነው» የሚለው ነገር አልነበረውም በመካከላቸው ሁሉ ነገር የጋራ ነበር ... አንድም ችግረኛ አልነበረም» የሐዋ. ሥራ 4:32-35። እንዲህም በመሆኑ ብዙዎች ወደ ክርስቶስ በመምጣት ከማህበራቸው ተቀላቅለዋል። «እግዚአብሔርንም ያመሰግኑ ነበር ሰውም ሁሉ ያከብራቸው ነበር እግዚአብሔርም የሚድኑትን ሰዎች በየቀኑ ወደ ማህበራቸው ይጨምር ነበር» የሐዋ. ሥራ 2:47 ስለዚህ ከዚህ እውነት በመነሳት አማኞች እርስ በእርሳቸው አንዱ ሌላውን በምሕረት ዓይንና በርኅራኄ ልብ እንዲቀበሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። በዚህ ዘመን የምንገኝ አማኞችም ከቀደመችው ቤተ ክርስቲያን መማር የሚገባንም ይኸው ነው።

ሐ. ርኅራኄ ዘመን የማይሽረው እውነት ነው

በዚህ ዘመን በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያንችን ያለነውን ስንመለከት ክርስቲያናዊ ሕብረታችን ያተኮረው በፀሎት፥ በዝማሬና በአምልኮ ወቅት በሚሆኑ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን። ከዚህም የተነሳ ዘመን አይሽሬ የሆነውን የርኅራኄ እውነት በተግባር የምንገልፅ በቁጥር ጥቂቶች ሆነን እንገኛለን። ምክንያቱ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ከርኅራኄ አኳያ ለእግዚአብሔር ቃል የመታዘዝ ፍሬ አለማሳየታችን ነው። ስለዚህ አብረውን ከሚያመልኩና ከሚያገለግሉ ምዕመናን መካከል በተለያዩ መንፈሳዊና ማህበራዊ ችግሮች ውስጥ የሚገኙትን አልተመለከትናቸውም። ከዚህም ሌላ አልፎ አልፎ የምናደርገው ጥቂት የርኅራኄ ሙከራ እንኳ አድሎአዊ ነው። ይህ ደግሞ በቀጥታ ልንከተለው ከሚገባን የእግዚአብሔር ቃል ጋር ተቃራኒ ሆኖ እናገኘዋለን።

የርኅራኄ ተግባራዊነት የሚታየው በተለያዩ ችግሮች የወደቁትን ሰዎች በችግራቸው ወቅት ፈጥኖ በመድረስ ነው። «አምላክህ እግዚአብሔር በሰጠው በአገርህ ደጅ ውስጥ ከሚኖሩ ከወንድሞችህ አንዱ ቢደኸይ ልብህን አታፅና በደሀው ወንድምህ ላይ እጅህን አትጨብጥ ... እርሱም ወደ እግዚአብሔር በአንተ ላይ እንዳይጮህ ኃጢአትም እንዳይሆንብህ ተጠንቀቅ ... አምላክህ እግዚአብሔር ስለዚህ በሥራህ ሁሉ ይባርክህልና ፈፅመህ ስጠው በአገርህ ውስጥ ላለው ደሀ ለተቸገረውም ወንድምህ እጅህን ታካፍላለህ ብዬ አዝዝሃለሁ።» ዘዳ. 15:7-11 ምዕመናን ከዚህ ቃል በመነሳት በመካከላችን የሚገኙትን ሰዎች በግል ሆነ በቡድን በመቀናጀት በጉድለታቸው ብንረዳ በጌታም ዘንድ ሆነ በሰዎች ዘንድ መልካም ምስክርነት እናተርፋለን።

መ. ርኅራኄ ተግባራዊ ነው

ርኅራኄ የሚገለፀው በቃል ሳይሆን በተግባር ነው። ክርስቲያኖች በክርስቶስ የተደረገላቸውን ምሕረትና ርኅራኄ ለወንድሞችና ለእህቶች በሚያደርጉት መልካም ነገር ማሳየት አለባቸው «... የሌላውን ሰው ችግር እንደራሳችሁ አድርጋችሁ አስቡ በወንድማማች ፍቅር ተዋደዱ፤ ደኅችና ትሁቶች ሁኑ» 1ኛ ጴጥ. 3:8 ይህ ቃል በምዕመናን መካከል ሲገለፅ ለሕዝቡ በረከት ለእግዚአብሔርም ደስታ ይሆናል «ሰው በዚህ አለም ሀብት እያለው ችግረኛውን አይቶ ባይራራለት «እግዚአብሔርን እወደዋለሁ» ማለት እንዴት ይችላል? ልጆች ሆይ ፍቅራችን እውነተኛና በሥራ የሚገለፅ ይሁን እንጂ በቃል ወይም በንግግር ብቻ አይሁን «1ኛ ዮሐ. 3:17-18 ለዚህ አምላካዊ መመሪያ ሥፍራ የሚሰጥ ሕይወት ሊኖረን ይገባል።»

«ተሳድቤአለሁ፤ ተቆጥቼአለሁ፤ ውሸት ተናግሬአለሁ፤ ልጆቹ ጋር ተጣልቼአለሁ» አለ።

«ክርስቶስ ላንተ የሠራው ምንድነው?» ብዬ ጠየቅሁት።

«ክርስቶስ ኃጢአቴን ሁሉ ተሸክሞ ሞቶአል» አለ።

«አሁን ክርስቶስ ወደ ልብህ ቢገባ ምንድን ነው ሚያደርግልህ? ብዬ ጠየቅሁት።

«ልቤን ያነጻል» አለ።

ከዚህ በኋላ እንዲህ ብሎ ጸለየ፤

«ክርስቶስ ሆይ፥ ወደ ልቤ ገብተህ ንገሥ፤ ከኃጢአት ሁሉ ንጻኝ። የዘላለምን ሕይወት ስጠኝ። ያንተ ልጅ አድርገኝ፤ ሚን።»

እርሱም ጸሎት ከጸለየ በኋላ እኔም ደግሞ ጸለይሁ። ከዚያም ንደገና ሌላ ጥያቄ ጠየቅሁት። «አሁንስ ስትጸልይ፥ ክርስቶስ ንተ ምን አድርጎአል?» አልሁት።

«አሁን ንጹሕ ልብ ሰጠኝ» አለ።

«ያደረገው ሌላ ነገር አለ?» ብዬ ጠየቅሁት።

«አምን፤ ልጁ አድርጎኛል፤ የዘላለም ሕይወትን ሰጥቶኛል» ለ።

በመጨረሻም አንድ ሌላ ጥያቄ ጠየቅሁት፤ «አሁን ሒደህ ምን ደርጋለህ?» አልሁት።

እጅግ ተደስቶ «ሒጂ ለጓደኞቼ እነግራለሁ» አለ።

እንግዲህ ያ ልጅ ክርስቶስ አስቀድሞ እንዲያደርግ ሚፈልገውን ነገር ሳልነግረው አወቀ። ወደ ልቡ የገባው እግዚአብሔር መንፈስ አሳስቦታል። ከዚያ በኋላ ደስ ብሎት ነሥቶ ሒደ። ለእነርሱም ነገራቸው።

ሮሜ 10:9-10

«ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ በተመስክር እግዚአብሔርም ሙታን እንዳነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ ምኖ ይጸድቃል በአፉም መስክር ይድናል።»

3. ምንድነው በልብህ የምታምነው?

እግዚአብሔር ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በኃጢአቴ ምክንያት ቀረበውን መሥዋዕት ተቀብሎ፥ ሞተው ከተቀበሩት መሐል

እንዳነሣው አምናለሁ፤ ደግሞ ኢየሱስ ሕያው ሆኖ እንደሚኖር ሊያድነኝ እንደሚችል አምናለሁ።

14. ምንድን ነው በአፍህ የምትመሰክረው?

ኢየሱስ አሁን የእኔ ጌታ መሆኑን በአፌ ለሌላ ሰው እመሰክራለሁ።

1ኛ ዮሐንስ 5:12

«የእግዚአብሔር ልጅ ያለው ሕይወት አለው።»

15. የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስን አግኝተሃል? የዘላለምን ሕይወት መቼ ነው የምታገኘው? «ሕይወት አለው» ማለት «ገና ለወደፊት አገኛለሁ» ማለት ነው ወይስ «አሁን አግኝቼአለሁ» ማለት ነው?

16. ኃጢአት እንደገና ብትሠራ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንህን አትጠራጠር! አሁን ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆነው አንድ ሌላ ምሳሌያዊ ታሪክ ልንገርህ።

ዳዊት የአቶ ዮሐንስ ልጅ ይባላል። የአቶ ዮሐንስ ልጅ የሆነው ከአቶ ዮሐንስ ስለተወለደ ነው። ዳዊት«ከአባቴ ጋር አልኖርም» ብሎ ወደሩቅ አገር ሄዶ ቢቀመጥ ዳዊት የማን ልጅ ነው? የአቶ ዮሐንስ ልጅ ነው። ዳዊት ደግሞ ወንጀል ሠርቶ ቢታሠር ወንጀል ቢሠራ እንኳ ያ የሠራው ወንጀል የአቶ ዮሐንስ ልጅ መሆኑን ሊለውጥ አይችልም።

ከእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ተወልዶ የዘላለምን ሕይወት ያገኘው ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ኃጢአት ቢሠራ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ሊለውጥ አይችልም። የማይሞት የእግዚአብሔር መንፈስ በልቡ ነው ያለው። እንደገና ኃጢአት ቢሠራ የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ይመክሰዋል። «ተመለስ» ይለዋል።

ሕፃን ደግሞ ለመራመድ ሲጀምር አንዳንዴ ይወድቃል። ሲወድቅ ወዲያውኑ ተነሥቶ እንደገና ለመራመድ ይሞክራል። ይህንን አስተውለህ ኃጢአት በምትሠራ ጊዜ፥ «ክርስቶስ ሆይ፥ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ» ብለህ እንደገና ተነሥተህ እርሱ በሚሰጥህ ኃይል በመንገዱ ተራመድ።



«እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም
ድምጼን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወ
እርሱ እገባለሁ፤ ከእርሱም ጋር እራ
እበላለሁ፤ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።»
ራእይ 3:20

ኢየሱስ ወደ ልብህ እንዲገባ ጋብዘው

ራእይ 3፡20

«እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምጼን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ፤ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ፤ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።»

. እንዲህ ብሎ የሚናገር ማን ነው?

-የሰማይ ክብሩን ትቶ ወደዚህ ዓለም መርዶ ያንተን ኃጢአት ሊያስወግድ የሞተው፥ ከሞትም የተነሣው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

. በየትኛው ደጅ ነው የሚቆመው?

-በልብህ ደጅ ነው የሚቆመው።

. ለምንድነው የሚያንኳኳው?

- የሚያንኳኳው ወደልብህ ሊገባ ፈልጎ ነው።

. ሊገባ የሚፈልገውስ ምን ሊያደርግ ነው?

-ገብቶ የልብህን ኃጢአት ሁሉ ጠርጎ ሊያስወጣና በልብህ ነግሦ ሊኖር ነው የሚፈልገው።

. ኢየሱስ ሊገባ የሚፈልገው ወደ ኃጢአተኛ ሰው ልብ ነው፥ ወይስ ወደ ንጹሕ ሰው ልብ ነው?

-ወደ ኃጢአተኛ ሰው ልብ ነው ሊገባ የሚፈልገው።

ኢየሱስ በጣም አድርጎ ይወደናል። ደግሞም ሁሉን የሚችል ጌታ ነው። ለእኛ ከባድ የሆነውን ኃጢአት ሁሉ ከልባችን ጠርጎ የያዕቆብ ቤት ይገግል። «አባቴ በዚህ ባልተጠረገ ቤት አይገባም» ብሎ «በሩን አልከፍትም» ይላልን?

አቶ ደምሴ «በዚህ ባልተጠረገ ቤት አልገባም» ብለው ትተው ይሔዳሉን? አይሔዱም። እንደምንም ልጁ ጥፋተኛ ቢሆንም፥ እንኳ አባቱ ስለሆኑ ገብተው ቆሻሻውንና እበቱን፥ በጠጡንም ጠርገው ያወጡለታል።

እንደዚሁም ኢየሱስ የልብህን ደጅ የሚያንኳኳ መሆኑን እወቅ! ወደልብህ ለማስገባት ፈቅደህ የልብህን ደጅ ብትከፍት፥ ይገባል። በእውኑ ምሳሌ እንደ ነገርሁህ አቶ ደምሴ ወደ ያዕቆብ ደጅ ደርሰው ሲያንኳኩ፥ ያዕቆብ «በዚህ ቆሻሻና እበት፥ በጠጥም በሞላበት ቤቴ አባቴ አይገባም» ብሎ መክፈትን ቢተው ኖሮ፥ በኃይል ከፍተው ወይም ሰብረው ይገቡ ነበርን? አይገቡም፤ ትተው ይመለሳሉ እንጂ።

እንደዚሁም ኢየሱስ በልብህ ደጅ ቆሞ ሲያንኳኳ ተነሥተህ ባትከፍት በኃይል አይገባም። በደስታ ከፍተህ ብታስገባው፥ ወደ ልብህ ገብቶ የልብህን ኃጢአትና ኃዘን ሁሉ ጠርጎ አውጥቶ በልብህ ይነግሣል። ለልብህ ደስታና ሰላም ይሰጥሃል።

6. የኢየሱስን ድምጽ እንዴት አድርገህ ታውቃለህ?

-የኢየሱስ ድምጽ መሆኑን ሰምተህ ማወቅ የምትችለው የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተህ ወይም አንብበህ የእግዚአብሔር መንፈስ ልብህን ሲያነሣሣ «በእውነት ይህ ቃል የሚናገረው እኔን ነው» ብለህ ኢየሱስን ወደ ልብህ እንድታስገባው የሚገፋፋህ ከሆነ፥ የኢየሱስን የጥሪ ድምጽ ሰምተሃል ማለት ነው።

7. የልብህን ወይም የሕይወትህን ደጅ እንዴት አድርገህ ነው

መልካም ስፍራ አይገኝም። በግል የሚደረግ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው። ቢሆንም ለብቻ በግል ማጥናቱ በቂ አይደለም። ምክንያቱም የአንድ ሰው ችሎታና እውቀት ብቻውን የተወሰነ በመሆኑ ነው። ያ ሰው እግዚአብሔር ለሌሎች ለእግዚአብሔር ሰዎች የገለጸላቸውን ነገር ደግሞ መማር አለበት። በሌሎች የሚሰጥ ተግሣጽና ማስጠንቀቂያ ደግሞ ያስፈልገዋል። ለአንድ ሰው በገዛ ሕይወቱ ውስጥ የሚገኘውን ኃጢአት ማስተዋል ቀላል አይደለም። እርግጥ መጽሐፍ ቅዱሱን ሲያነብና ሲጸልይ እግዚአብሔር ኃጢአቱን ሊገልጽለት ይችላል። ነገር ግን በልምምድ እንደደረሰበት ከሆነ አንድ ሰው ለራሱ ይህንን ነገር ሊያደርግ አይታይም። ዳዊት እንደጸለየው መጸለይ ቀላል አይደለም። «ፈትነኝ. . . በደልንም በእኔ ውስጥ ብታገኝ እይ...» [መዝ. (139)፡ 23፥ 24]። ሰውም በልቡ ውስጥ ያለ ኃጢአት ተገልጦ መታየት አለበት። በዚህን ጊዜም የእግዚአብሔር ቃል በፊቱ ተገልጾ እንደሚታይ ያህል የራሱን በደል ማየት ይችላል። ሰውዬውም ከበደሉ ተመልሶ እንዲታዘዝ ከዚያም እንዲመስክርና

7. ምስጋና ማቅረብ። ቤተ ክርስቲያን የመሄዳችን አንደኛው ምክንያት እግዚአብሔር ስለ ሰጠን ነገሮች፥ በተለይም በክርስቶስ በኩል ስላደረገልን ደኅንነት ልናመሰግነው ነው። ይህንንም ስንል ቤተ ክርስቲያን መሄዳችን የማይባክን ምስጋና ከእግዚአብሔር ለማግኘት ሳይሆን በልጁ ሞት ስለ ሰጠን ታላቅ ደኅንነት «ተመስገን» ልንለው ብቻ ነው። [መዝ. (122)፡ 1፤ (42)፡4]።

ከብዙ ዓመት በፊት ኢሳይያስ ጥቂት ቃላቶችን ጽፎ ነበር። እነዚህም ቃላቶች ቀድሞ ይሰጡት በነበረ መጠን ዛሬም ትርጉም ይሰጡናል። «ፈቃድህን በተቀደሰው ቀኔ ከማድረግ እግርህን ከሰንበት ብትመልስ፥ ሰንበትንም ደስታ፥ እግዚአብሔርም የቀደሰውን ክቡር ብትለው፥ የገዛ መንገድህንም ከማድረግ ፈቃድህንም ከማግኘት ከንቱ ነገርንም ከመናገር ተከልክለህ ብታከብረው፥ በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ደስ ይልሃል፥ በምድርም ከፍታዎች ላይ አወጣሃለሁ፥ የአባትህንም የያዕቆብን ርስት አበላሃለሁ፤ የእግዚአብሔር አፍ ተናግሮአልና» (ኢሳ. 58፡13፥14)። እኛ የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝ

ቤተ ክርስቲያን የመሄድ አስፈላጊነት

አንዳንድ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን
ሳይሄዱም። እነርሱም ቤተ ክርስቲያን
ለመምጣታቸው ምክንያት ሲሰጡ፥
ግዚአብሔርን በግላቸው ማምለክ
እንደሚችሉና ወይም በየእሑዱ ወደ ቤተ
ክርስቲያን ከሚሄደው ሰው በግብር
እንደማያንሱ ይናገራሉ። ይህም እውነት
ው። እንደተባለውም ወደ ቤተ ክርስቲያን
አዘውትሮ የሚሄደው ሰው ይህን ያህል
ማይሄደው ሰው የተሻለ ላይሆን ይችላል።
ቤተ ክርስቲያንም አዘውትሮ መሄዱ
ውዬውን ክርስቲያን ሊያደርገው
ይችልም። ሆኖም ክርስቲያን መሆን
አዘውትሮ ቤተ ክርስቲያን ከመገኘት የላቀ
ላማና ምሥጢር አለው። ከሌሎች አማኝ
ሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች ጋር ማምለክ
ርስቶስን ወደ ማወቅ ደረጃ ሊያቀርበን፥
ግል የምናመልከው አምልኮት ግን
ሴትንና ደስታን ይጨምርልናል።

«አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን
መንግሥት ፈልጉ» (ማቴ.6፡33)። አንዳንድ

1. እግዚአብሔርን ለማምለክ። ወደ ቤተ ክርስቲያን የምንሄደው አንድ ነገር ለመቀበል ብቻ ሳይሆን አምልኮታችንንና ምስጋናችንን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ነው። «በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖርማለን።» (የሐዋ. 17፡28)። እውነተኛ አምልኮ እግዚአብሔርን በአስተሳሰባችንና በአድራጎታችን ዋነኛ አድርገን እንዳመለክነው ያሳያል። እግዚአብሔርም ሰውን መፍጠሩ ለራሱ ክብር እንዲሆነው ነው። እኛም የእርሱ ፍጥረቶች ነን። እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎች ግን የእግዚአብሔርን ዓላማና ዕቅድ ለውጠው በፈጣሪ ፋንታ ፍጡሩን ያመልካሉ (ሮሜ 1፡25)። እርሱም የሚያከብሩትን ስለሚያከብር እርሱን ብቻ ማክበርና ከፍ ከፍ ማድረግ እንዳለብን አዞናል (ሮሜ 15፡6፤ 1ኛ ቆሮ. 6፡20፤ 1ኛ ሳሙ. 2፡30)። በአምልኮታችንም ጊዜ አክብሮታችን እንደሚገባው በመገንዘብ በጸሎት ስናስበው፥ በመዝሙር ደግሞ እናመሰግነዋለን። እኛም ደግሞ ኃጢአተኞች ስለሆንን የተሰጠንን በረከት ሁሉ እንደማይገባን በመናገር እንናዘዛለን። በእግዚአብሔር ልጆች መሐል ተገኝቶ የሚደረግ ቅዱስ አምላካዊ አምልኮ ከልብ

እንደሚቻል ተረድቼአለሁ። ስለዚህ ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በልና ተቀበልኝ። አሜን።



የሕይወት ቡር
ፖ.ሣ.ቁጥር 4937
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የደግ ሥራ መብዛት እንደ እምነት አይሆንም

ፈጣሪ ሰውን ሲፈጥር እንደ እንስሳት አድርጎ አልፈጠረም። ምክንያቱም እንስሳት ከፈጣሪያቸው ጋር የሚያገናኝ መንፈስ የላቸውም። ሰው ግን ከፈጣሪው ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት መንገድ አለው። በመሆኑም የሰው ልጅ ከፈጣሪው ጋር ግንኙነት እንዲኖረው የሆነውን ዓይነት ሃይማኖት መርጦ መከተል ይጀምራል። ምክንያቱም ሃይማኖት ሁሉ ከፈጣሪ ጋር ያገናኛል ብለው ስለሚያስቡ ነው። ስለዚህ ሃይማኖቶች ሁሉ ዋጋ በመክፈል ላይ ይገኛሉ። የሚከፍሉትም ዋጋ እንደ አቅማቸው ሳይሆን እንደ ሃይማኖቱ ፍላጎት መሆኑ ግድ ይሆናል። ይህም ሆኖ የሰው ልጅ ባገኘው ዓይነት እምነት የተጠየቀውን ዓይነት ዋጋ ሁሉ ከፍሎ ከፈጣሪው ጋር ግንኙነት ለማድረግ መጣጣሩ አስደናቂ ነው።

ምንም ከመለኮታዊ ኃይል ጋር የቅርብ ግንኙነትና ጉብረት መፍጠር ባይችሉም ብዙ ሰዎች በቅርብ ያሉትን ተፈጥሮችን በማድነቅና በማምለክ እንዲሁም ለእነርሱ የሚመስል መሥዋዕት በመስጠትና በማክበር ይለፋሉ። አንዳንዶች

ብዙ ጊዜ የሰው ልፋት ሁሉ ዋጋ ማግኘት አለበት ማለት የሁሉም ሃይማኖታውያን ጥያቄ መሆኑ ግልጽ ነው። ቢሆንም ሰዎች ከአዳም ጊዜ ጀምሮ ከነበረው ውድቀት የተነሣ የቅርቡን እንጂ የሩቁን፥ ግልጹን እንጂ የጥልቁን መረዳት አልቻሉም። በመሆኑም የሰው ልጅ ከፈጣሪው ጋር ለመገናኘትና ጎብረት ለመፍጠር የሚፈጽማቸው ሥርዓቶች፥ አምልኮዎች፥ ስግደቶች፥ ጸሎቶች፥ ጾሞች፥ ስጦታዎችና ሌሎች በጎ ምግባሮች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ በመሆናቸው የሚያኩሩ ቢመስሉም ከአንድ ጋር የማይወዳደሩ ዘጠና ዘጠኞች ሆነው ይቀራሉ። ምክንያቱም በፈጣሪ ዘንድ ከዘጠና ዘጠኝ የሚበልጥ አንድ ታስቦና ተሰጥቶ ሳለ የሰው ልጆች ሳያውቁት ለብዙ ትውልድ ዘመን ኖረዋል። ነገር ግን ቅዱሳት መጻሕፍት በፈጣሪው ለሰዎች የተዘጋጀውን የዘላለም ሕይወት መንገድ በግልጽ ይናገራሉ። በ1 ጢሞ. 2፡5 «አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።» ከመጻሕፍቱም መረዳት እንደሚቻለው ፈጣሪው አንድ ሲሆን የሰዎችን ዘጠና ዘጠኝ

አልመጣም። እንዲሁም ሞትን አሸንፎ ከመቃብር አልተነሣም። የተለያዩ የዓለም ሃይማኖት መሪዎችና አስተማሪዎች አጽም በመቃብር ውስጥ ነው። ጌታ ኢየሱስ ግን ስለ ሰዎች ኃጢአት ሞቶ ሞትንም ድል አድርጎ በመነሣት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የዘላለም ኅብረትና ግንኙነት እንዲኖር አድርጓል። በመሆኑም ጌታ ኢየሱስ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የዘላለም ኅብረትና ግንኙነት እንዲኖር አድርጓል። ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ በእግዚአብሔር ለሰው የተዘጋጀ የደኅንነት መንገድ ነው።

ውድ አንባቢ ሆይ! ለመሆኑ ከባሕላዊ እምነት ወይም ከፈለጉት ዓይነት ሃይማኖት የተነሣ የፈጸምኸው ተግባር ምን ያህል ደርሶ ይሆን? አንተው (አንቺ) የሰባት ትውልድ ውርስ በመምሰሉ ብቻ ጥረቱን እየቀጠልህ (ሽ) ነህ(ሽ)? እስቲ ራስህን (ራስሽን) ጠይቅ(ቂ)! በጸሎት፥ በስግደት፥ በጾም፥ በዓላትንና ነቢያትን በማክበር፥ ቅዱሳን ስፍራዎችን በመጎብኘት፥ ምጽዋትንና ስጦታን በመስጠት ፈጣሪን የረዳህ(ሽ) በመምሰል የተፈጸመው የሰባት ትውልድ ድካም

ስበው ግን በአሪት ሕግ ውስጥ ከተፈለገው ይበልጥ አሁን ከእኛ የሚፈለግብን ይመስላል። ማቴ. ፭፥ ፳፯። ነገር ግን በመኻከላቸው ትልቅ ልዩነት አለ። በአዲሱ ኪዳን መሠረት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል መድኃኒቱ አድርጉ የሚቀበለውን ሁሉ እግዚአብሔር አዲስ ፍጥረት ሊያደርገው ተስፋ ሰጥቷል። ፪ኛ ቆሮ. ፭፥ ፲፯። በክርስቶስ ለሚያምኑ ክርስቶስ ከነርሱ ጋር ይኖራል። ዮሐ. ፲፬፥ ፳። ስለዚህ አስገራሚ እውነት እርግጠኛነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ብቻ አንጣጣ

ልግሎታችን በደስታና በፈገግታ በእውነት መንገድ በሚመራን መንፈስ የተመዘገበ ይሆንልናል።

ዮሐ. ፬፥ ፳፫፣ ፳፬፤ ሮሜ ፯፥ ፮።

በዚህ ትምህርት ተደስተው እንደሆነና በተጨማሪ ሌላ ትምህርት ለማግኘት ቢፈልጉ ወይም ጥያቄ ቢኖርዎት ከዚህ ቀጥሎ ባለው አድራሻ ቢጠይቁ ሊረዱ ይችላሉ።

«እምነትም ሳይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት
ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠበቅ ነበር።»
ገላ. ፫ ፥ ፳፫።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናነበው አብዛ
ኛው ሕግ ከእግዚአብሔር ለሙሴ ስለተሰጠው ሕግ
ው። ይህም የተሰጠው የእስራኤል ልጆች ተስፋ
ወደተሰጣቸው ወደ ከነዓን ምድር ሲጓዙ በምድረ
በዳ ሳሉ ነው። በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር
ከእስራኤል ልጆች ጋር ቃል ኪዳን ተካየደ። ለቃሉ
ሊታዘዙ፥ ሕጉንም ሊጠብቁ ሊያገለግሉትም ተስፋ
ሊሰጡት ከነርሱ ጋር ሊሆን ሊጠብቃቸውም የሚ
ያስፈልጋቸውንም ሊሰጣቸው ቃል ገባላቸው። እግ
ዚአብሔር ሕጉን የሰጣቸው ምክንያት ይታዘዙት
ንድ ሕጉ እንዲረዳቸው ነው። እርሱም የሰጣቸ
ውን ሕግ ቢጥሱ ንስሐ መግባታቸውን የሚያሳዩበ
ትን መንገድ ደግሞ ነገራቸው። አይሁድ ሕግን
ለመጠበቅ ዳድቅ አልሆነም፥ ምክንያቱም አንድ
ው ስንኳ ሕግጋትን ጨርሶ ለመጠበቅ አልተቻለ
ም። ገላ. ፪ ፥ ፲፮። አንድ ሰው ኃጢአት ቢያደ
ርግ መሥዋዕትን ብቻ ቢያመጣ ለጽድቅ አልሆነ
ም። ዓሞጽ ፭ ፥ ፳፩ - ፳፬። ከኃጢአቱ ንስሐ
ቢገቡ፥ እያንዳንዱ ሰው ተገቢውን የግል መሥዋ
ዕት እግዚአብሔር እንደሚቀበልለት እያመነ ከመጣ
በኋላ በእግዚአብሔር ዘንድ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረ
ለት።

ሕግን በመጠበቅ አንድ ሰው እንኳን አልጸደ
ቀም። ልንጸድቅበት የምንችለው አንዱ መንገድ
እምነት ብቻ ነው። አይሁድ ሊጸድቅ ይቻለው
የነበረ መንገድ ደግሞ እምነት ብቻ ነበር። አብር
ሃምም የጸደቀ በእምነት ብቻ ነው። ጳውሎስ በገ
ላትያ ፪ ፥ ፲፮ ላይ «ሰው አሪትን በመሥራት አይጸ
ድቅም።»

አሪት ቅድስት፥ ፍጹም፥ መልካም ናት።
ሮሜ ፯ ፥ ፲፪ ና ፲፬። ነገር ግን፥

ሀ) ልታጸድቅ አትችልም — ሮሜ ፫ ፥ ፳።
ለ) ጽድቅንም አትሰጥም — ገላ. ፫ ፥ ፳፩ - ፳፪።
ሐ) ማናቸውንም ፍጹም አታደርግም — ዕብ.
፯ ፥ ፲፱።

እግዚአብሔር ሕግን መስጠቱ እኛ ኃጢአት
ምን እንደሆነ ለማወቅ እንድንችል ነው። ጳውሎስ
በሮሜ ፯ ፥ ፯ «ሕግ አትመኝ» ትላለችና በለው
ምንንም መመኘት ኃጢአት እንደሆነ እንረዳለን
ማለት ነው። እግዚአብሔር ሕግን በመስጠቱ ሌላ

ሕይወት ለሕይወት

ከምሥራት የተገኘ ታሪክ።



ከዚህ የሚከተለው ታሪክ ከብዙ ዓመታት በፊት የተፈጸመ አስደናቂ ታሪክ ነው።

በአንድ ከተማ ሁለት ወንድማማቾች በአንድነት ይኖሩ ነበር። ታናሽየው በከፋትና በስንፍና ይኖር ነበር፤ ታላቅየው ግን እግዚአብሔርን የሚፈራ፥ ትሑትና

እንድጽፍ ወረቀት፥ ብዕር ና ቀለም፥ ለማጣቢያም ሰም ይፍቀዱልኝ። ይህንም ደብዳቤ በፖስታው እንደ ታሸገ እኔ ከሞትሁ በኋላ በአድራሻው እንዲላክልኝ ይዘዙልኝ" አለው።

አዛዡም የተፈረደበትን ሰው ፊት እያስተዋለ ሲመረምር በሚታይበት ሰላምና ትዕግሥት ተደነቀ፤ ቅንነቱንም ስላየ የሚፈልገውን ዕቃ አቀረበለት፤ የሚጽፈውንም ደብዳቤ ሌሊት ለጥበቃ የሚዞረው ዘበኛ እንዲቀበለው አዘዘ።

ሌሊቱም አለፈ፤ ንጋትም ነጋ። የወጎኒ ቤት ወታደሮችም ተግባራቸውን አከናወኑ፤ በአንዲት ሰዓት ውስጥም የተወሰነውን ፍርድ ፈጸሙ።

ከጥቂት ጊዜያት በኋላ አንድ መልእክተኛ የሚቹን ደብዳቤ ይዞ ሁለቱ ወንድማማቾች ይኖሩበት ወደ ነበረው ቤት ደረሰ። መዝጊያውንም ቢመታ ፊቱ የገረጣ፥ በጭንቀት ላይ ያለ፥ አንድ ወጣት ጉበዝ በሩን ከፍቶ ደብዳቤውን ተቀበለው። ፖስታውንም እየተመለከተ ረጅም ጊዜ ከዘገየ በኋላ ማጣበቂያውን ቀድዶ ሲያነበው ሰውነቱ ተሳቅቆ ያለቅስ ጀመር። በመጀመሪያ ወደ በሩ ሮጠ፤ በኋላ ግን እየባከነ እየተንቀጠቀጠም ወደ ቤቱ ተመለሰ።

<u>በደብዳቤው ውስጥ የተጻፈው ምን ናርአል</u>? ከዚህ ቀጥሎ ከሰፈሩት ሁለት

እነርሱም መፈተናቸውን ትተው
ብዙዎቹ ከእርሱ ራቁ። አንዳንዶቹ ግን
ከኃጢአት ተመልሰው በአዲስ ሕይወት
ለመራመድ ከዚህ ከቀድሞ ጓደኞቻው ጋር
ተባበሩ።



ኃጢአትና ርኵሰት ተሸክሞ፥ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ስለ አንተ ሞተ። እንግዲህ ይህን ታላቅ ፍቅሩን አስበህ በእርሱም አምነህ በራሱ ደም ያስገኘልህን የኃጢአትን ይቅርታና የዘላለምን ሕይወት ተቀበል እንጂ እምቢ አትበለው።

እርሱ እንደዚሁ የአንተን ኃጢአት ሁሉ አስወገደልህ። አሁንስ የቀረው ምንድን ነው? ያ ታናሽየው ወንድም የተሰጠውን ንጹሕ ልብስ ለብሶ ከዚያ ቀን ጀምሮ በአዲስ ሕይወት ይኖር እንደ ነበረ፥ አሁንም አንተ የመድኃኒትህን የኢየሱስ ክርስቶስን ጽድቅ ተቀበልና ልበስ፥ ከእንግዲህም ወዲህ እርሱን በማሰብ ተወስነህ ከክፉ ሁሉ እየራቅህ ለእርሱ ክብር በቅድስና ኑር፥ ያደረገልህንም ውለታ ሁሉ ለሌሎች አውራ። ከዚህ ቀጥሎ ለተጻፈው ለእርሱ ደብዳቤ ምን ትመልሳለህ?

"እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል"

"ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም"

"ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና"

"እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ

ጽሑፍ፡- በአቶ ገብረ እግዚአብሔር ካህሳይ፥
በአቶ አሰፋ ጃቴ፥ እና
በሚ/ር ግሪጎር ቦይድ
እርማት፡- በፋሲል ግዛው
አሳታሚ፡- የኤስ.አይ.ኤም ፕብሊኬሽን

የፖ.ሣ.ቁ 127፥
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ
1992 ዓ.ም

አስተያየት

አነስተኛዋ መጽሐፍ በቀላል አቀራረብ የተዘጋጀችና ጥሩ ሆና አግኝቻታለሁ። «ኢየሱስ ብቻ» ብለው የሚሰብኩ ሰዎች ከሚያነሡዋቸው ርእሰ-ጉዳዮች አብዛኛው ተካትቷል። ብዙዎች የአቅጣጫ ለውጥ እንዲያደርጉ መሣሪያ ትሆናለች የሚል እምነት አለኝ።

ግርማዊ

መግቢያ

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ወይም በተለምዶ «ኢየሱስ ብቻ» በመባል የሚታወቀው ቡድን ወደ ኢትዮጵያ የመጣው በ1965 ዓ.ም. አካባቢ ነው። ከዚያ በፊት ግን ስለዚህ ትምህርት አልሰማንም ነበር። በመጀመሪያ ብዙ ጥያቄዎች አልተፈጠሩም ነበረ። ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ግን ብዙ ማደናገር ጀመረ። ዛሬ እነዚህ ሰዎች ምን እንደሚያስተምሩና ምክር ሊጠይቁን ለሚመጡ ሰዎች ምን መልስ እንደምንሰጥ ማወቅ ያስፈልገናል።

ይህ አጭር ጽሑፍ ከሦስት ጸሐፊዎች የተውጣጣና የተቀነባበረ ማጠቃለያ ነው። ጸሐፊዎቹ አቶ ገብረእግዚአብሔር ካሕሳይ፥ አቶ አሰፋ ጃቴ እና (Oneness Pentecostals and The Trinity) «ሥላሴና የአንድነት ጰንጠቆስጤዎች» የተባለውን የእንግሊዝኛ መጽሐፍ የጻፉት ሚስተር ግሪጎሪ ኤ. ቦይድ ናቸው። ሚስተር ቦይድ የዚህ ሃይማኖት ተከታይ ነበሩ። አንድ ቀን የሮሜ መልእክት ምዕራፍ 8 ቁጥር 13 በሚያነቡበት ጊዜ መንፈሳዊ ዓይናቸው ተከፍቶ ሊድኑ በቁ። ከዚያም ሰዎች የዚህን የስሕተት ትምህርት ስሕተት ለመረዳትና ለማየት እንዲችሉ መጽሐፉን አበረከቱ።

ይህችን ትንሽ መጽሐፍ ያዘጋጀንበት ዓላማ አማኞች በዚህ የስሕተት ትምህርት እንዳይወሰዱ ለማስጠንቀቅና ትምህርቱንም አውቀው ስሕተቱን ለመረዳት እንዲችሉ እና ራሳቸው በትምህርቱ ተወስደው ከእውነት እንዳይወድቁ ነው። እግዚአብሔር ከስሕተት እንድንጠበቅ ይርዳን። አሜን።

ማውጫ

መግቢያ.....

ሀ. «ኢየሱስ ብቻ» በመባል የሚታወቀው እንቅስቃሴ (የሐዋርያት ቤተክርስቲያን) ታሪክ 1

ለ. «የኢየሱስ ብቻ» ተከታዮች ብዙ ጊዜ ምን ያስተምራሉ? 3

ሐ. ሥላሴን በተመለከተ ምን እናምናለን? 4

መ. የሐዋርያት ሥራ 2፡38 ትርጉም ምንድን ነው?..... 10

ሠ. እምነታችንን ለመደገፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስንጠቅስ ማስታወስ የሚያስፈልጉን ነጥቦች..... 14

ረ. ሥላሴን በተመለከተ ለ«ኢየሱስ ብቻ» ተከታዮች የስሕተት ትምህርት መልስ መስጠት 15

ሰ. ደኅንነት በጥምቀት ለሚለው የስሕተት ትምህርት መልሶች 19

ሸ. ምልክቶችን የደኅንነት ማረጋገጫ ለሚያደርገው የስሕተት ትምህርት መልሶች..... 23

ቀ. የመጨረሻ ማሳሰቢያዎችና ማስጠንቀቂያዎች..... 26

«ኢየሱስ ብቻ» በመባል የሚታወቀው እንቅስቃሴ (የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን) ታሪክ

ከሐዋርያት ጋር በተጀመረው የቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ነን የሚሉቱ እንቅስቃሴዎቹ የተጀመረው በቅርቡ ነው። በ1912 ዓ.ም. አካባቢ በአሜሪካን አገር ሰዎችን በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቅ ስሕተት ነው የሚል አዲስ ትምህርት ተጀመረ። ይህም መጠመቅ የሚገባን አንድ ትክክለኛ መንገድ በኢየሱስ ስም ብቻ ነው የሚል ነበር። በዚያን ጊዜ ይህ «አዲስ ትምህርት» ወይም «አዲስ ጉዳይ» ተብሎ ተጠራ።

በዚህ ትምህርት ምክንያት አንዳንድ ሰዎች የወንጌል አማኝ ቤተ ክርስቲያንን ትተው የራሳቸውን አብያተ ክርስቲያናት ቡድኖች መመሥረት ጀመሩ። እነዚህ ቡድኖች በሚያድጉበት ጊዜ ብዙ ክፍፍሎች በመካከላቸው ነበሩ። እነዚህ በሙሉ የሥላሴን ትምህርት ይቃረኑ ነበር። እግዚአብሔር አንድ ብቻ ስለሆነ እግዚአብሔር አብ ኢየሱስ ራሱ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ኢየሱስ ራሱ ነው ይላሉ።

«ኢየሱስ ብቻ» የተባለው ክፍል አንድ ማዕከላዊ ቢሮ ስለሌለው የሥላሴን ትምህርት ለሚቃወሙት ለሁሉም ቡድኖች አንድ ድምፅ ለማሰማት አይቻልም። ስለዚህም በአንድ አካባቢ የሚሰጠው ትምህርት ምናልባት በሌላ ስፍራ ከሚሰጠው ትምህርት የተለየ ሊሆን ይችላል። በኢትዮጵያ ያለው የሐዋርያት ቤተክርስቲያን ወይም «የኢየሱስ ብቻ» ተከታዮች

የሚያስተምሩት ትምህርት በሌላ ክፍለ ዓለም ከሚያስተምሩት ትምህርት የተለየ ሊሆን ይችላል።

በአሜሪካ ውስጥ የ«ኢየሱስ ብቻ» ክፍል አባላት የሆኑት ሰዎች አንድ ሚሊዮን ይገመታሉ። በጠቅላላው ዓለም ደግሞ አምስት ሚሊዮን ያህል የሚሆኑ የዚህ ክፍል ተከታዮች እንደሚገኙ ይነገራል። በኢትዮጵያ ውስጥ ምን ያህል እንዳሉ አይታወቅም።

በ«ኢየሱስ ብቻ» ትምህርት መሠረት፥ በኢየሱስ ስም ብቻ ያልተጠመቀ ክርስቲያን ይጠፋል። በዚህም ምክንያት በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በተጠመቁት አማኞች መካከል ትምህርታቸውን ማስፋፋት ይፈልጋሉ። በሌላ አነጋገር የእነርሱ ዓይነት ጥምቀት የሰዎችን ነፍስ ያድናል ብለው ያምናሉ። በአማኞች ላይ ስለሚያተኩሩ በተለይም መጽሐፍ ቅዱስን በደንብ ባልተማሩ አማኞች ላይ ብዙ መደናገር ይፈጥራሉ።

በዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩና ሥላሴን በተመለከተ የስሕተት ትምህርታቸውን ለማስተማር መጽሐፍ ቅዱስን የሚጠቀሙ ሁለት ዋና ቡድኖች አሉ። አንደኛው የይሖዋ ምስክሮች ሲሆኑ፥ እነርሱም ኢየሱስ የተፈጠረ ሰው ነበር በማለት የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ይክዳሉ። የ«ኢየሱስ ብቻ» ተከታዮች ደግሞ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ልዩነት የለም ብለው ያስተምራሉ። ሁሉም የኢየሱስ የተለዩ ስሞች መግለጫ ናቸው ይላሉ።

ሥላሴን በተመለከተ የሐሰተኛ አስተማሪዎች መነሣት በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አዲስ ነገር አይደለም። በመጀመሪያ ከሐዋርያት ዘመን 300 ዓመት በኋላ ሥላሴን የካዱ ሰዎች ነበሩ። እነርሱም ሐሰተኛ አስተማሪዎች ተባሉ። ስለዚህም ከቤተክርስቲያን ጎብረት ተወግደው እንዳያስተምሩ ተከልክለው ነበር። በሌላ በኩል ስለ አብ፥ ስለ ወልድና ስለ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክነት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጽፈው ነበር። የዚህ ጽሕፈት ቅጂዎች ዛሬ በተወሰኑ መጻሕፍት ቤቶች ይገኛሉ። ስለዚህም ጥምቀት በኢየሱስ ስም ብቻ ይሁን የሚለው ትምህርት ሐዋርያት ያስተማሩት ሳይሆን እስከ 1912 ዓ.ም. ድረስ ተረስቶ የነበረ ነው። በተሳሳተ መንገድ በተተረጎሙ የሐዋርያት ሥራ ክፍሎች ላይ የተመሠረተ አዲስ ትምህርት ነው። ይህንን በኋላ በዝርዝር እንመለከተዋለን።

የ«ኢየሱስ ብቻ» ተከታዮች ብዙ ጊዜ ምን ያስተምራሉ?

የ«ኢየሱስ ብቻ» እንቅስቃሴ ክፍሎች አንድ ዓይነት አስተምህሮ ስለሌላቸው፥ ትምህርታቸው ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላው ሲኬድ ሊለያይ ይችላል። ቢሆንም ብዙዎቹ የሚያስተምሩዋቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ሥላሴን ይክዳሉ።

ለ. ጥምቀት በኢየሱስ ስም ብቻ መሆን አለበት ይላሉ። እንዲህ ዓይነቱ ጥምቀት ለአንድ ነፍስ መዳን አስፈላጊ ነው ሲሉ፥ በሌላ አነጋገር ጥምቀት ያድናል ማለታቸው ነው።

ሐ. ደኅንነት በምንሠራው ሥራ ይፈጸማል እንጂ

መ. በልሳን መናገር አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ የመሞላቱ ምልክትና የመዳኑም ምልክት ነው። ተከታዮቻቸውም አንድ ሰው በልሳን ካልተናገረ በስተቀር ሰው አልዳነም ብለው ይናገራሉ።

ሥላሴን በተመለከተ ምን እናምናለን?

የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ በምናነብበትና በምናጠናበት ጊዜ የሰማይና የምድር ፈጣሪ ራሱን አንድ አምላክ በሦስት ስሞችና በሦስት አካላት በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ገልጧል (የማቴዎስ ወንጌል 28፡19-20 እና 2ኛ ቆሮንቶስ 13፡14።) ምንም እንኳ ይህ በሦስት የተገለጠ አንድነትን ለመረዳት አስቸጋሪ ቢሆንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተገለጠ እውነት ነው ብለን እናምናለን። ስለ እግዚአብሔር ከእግዚአብሔር ከራሱ በላይ ማወቅና መግለጥም አይቻልምና፥ ስለ ራሱ ራሱ የገለጠውን ማመን አዋቂነት ነው።

«ሥላሴ» የተባለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይገኝም፥ ራሱን በሦስትነትና በአንድነት የገለጠውን አምላክ ለማስረዳት ዛሬ የምንጠቀምበት ቃል ነው። በራሳችን ማስተዋል ይህንን መቀበል አዳጋች ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ትምህርት በእምነት እንቀበላለን። የማይቀበሉትም እንደተሳሳቱ እናረጋግጣለን። ክርክራቸው ስለ ራሱ በሦስት ስምና አካል ከገለጠው ከእግዚአብሔር ጋር እንጂ ከሰው ጋር እንዳልሆነ እንጠቁማቸዋለን።

በዘዳግም ምዕራፍ 6፡4 ላይ እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ በግልጥ እናያለን። በሌሎች ቦታዎችም ቢሆን ሦስት አምላክ እንደሚኖር ወይም አንዳንድ ጊዜ አንዱ አምላክ ሌላኛውን ሲያመልክ አናገኝም። መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ እግዚአብሔር በብዙ ቁጥር በብዙ ስፍራዎች እንደሚጠራ ያስተምረናል። ስለዚህም ከአንድ አካል በላይ እንደሆነ እናያለን።

ለምሳሌ በብሉይ ኪዳን፡-

1. ዘፍጥረት 1፡26 «ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤»
2. ዘፍጥረት 3፡22 «እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤»
3. ዘፍጥረት 11፡7 «ኑ፥ እንውረድ፤ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው።»
4. ኢሳይያስ 6፡8 «የጌታንም ድምፅ፡- ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል? ሲል ሰማሁ።»

በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድ ሆኖ የሚጠራው እግዚአብሔር በአካል ሦስት እንደሆነ የሚያሳዩ ብዙ ጥቅሶች አሉ። እነዚህ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው፡-

1. ዮሐንስ 5፡17-18 «አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ»
2. ዮሐንስ 14፡15-17 «እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤»
3. 1ኛ ቆሮንቶስ 8፡6 «ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም

በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።»

4. 1ኛ ጴጥሮስ 1፡1-2 «የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ጴጥሮስ፥ እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስም እንደሚቀደሱ፥ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ...»። በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን በሦስት አካላት ተገልጦ እናየዋለን። ነገር ግን እያንዳንዱ አካል እኩል አምላክ እንደሆነ የሚያሳይ ባሕርይ እንዳለው እናያለን። ከዚህ በታች በተጠቀሱት ምሳሌዎች ስለ አብ የተነገረው ስለ ወልድ እንደተነገረና ስለ መንፈስ ቅዱስም እንደ ተነገረ እናሳያለን። ስለዚህም እያንዳንዱ አካል ፍጹም አምላክ ነው።

ባሕርያት	አብ	ወልድ	መንፈስ ቅዱስ
ዘላለማዊነት	መዝ. (90)፡2	ዮሐ. 8፡58	ዕብ. 9፡14
ሁሉን ቻይነት	1ኛ ቆሮ. 8፡6	ዮሐ. 1፡3	የሐዋ. ሥራ 1፡8
ሁሉን አዋቂነት	መዝ. 7፡9	ራእይ 2፡18-23	1ኛ ቆሮ. 2፡10
በሁሉ ቦታ መገኘት	ኤር. 23፡24	ማቴ.28፡20	መዝ. (139)፡7
ቅድስና	1ኛ ሳሙ. 2፡2	የሐዋ.ሥራ 3፡13-14	ሮሜ 1፡3-4
እውነተኛነት	ዘዳ. 32፡4	ዮሐ. 14፡6	ዮሐ. 14፡17
ፍቅር	1ኛ ዮሐ. 4፡8	ዮሐ. 13፡1	ሮሜ 15፡30
ፈጣሪ	ዘፍጥ. 1፡1	ቆላ. 1፡15-17	ኢዮብ 33፡4
አምላክነት	ኢሳ.8፡13-14	1ኛ ጴጥ.	የሐዋ. ሥራ

ሦስት አካላት አንድ አምላክ ናቸው በምንልበት ጊዜ አብ ወልድ ነው ማለታችን አይደለም። ወልድ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ አይደለም። በአካልም በስምም ሦስት ናቸው፤ ደግሞም በመለኮታዊ ባሕሪ አንድ ናቸው- አንድ አምላክ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አብ ስለ ወልድ ይናገራል (ማቴ. 3፡17)። በተጨማሪ ወልድም ስለ እግዚአብሔር አብ ይናገራል (ዮሐ. 7፡16)። እንዲሁም ወልድ ስለ መንፈስ ቅዱስ ይናገራል (ዮሐ. 16፡13)። መንፈስ ቅዱስ ስለ ወልድ (ስለ ልጁ) ይመሰክራል (ዮሐ. 15፡26-27)። ስለዚህም አብ ከወልድ በስምና በአካል የተለየ ነው። ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ የተለየ ነው። ነገር ግን አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ በባሀርይ አንድ አምላክ ናቸው። አንድነት- በሦስትነት... ሦስትነት-በአንድነት...አሐዱ-ሥሉስ አምላክ!

ሥላሴን በምንመለከትበት ጊዜ ማሰብ የሚገባን ዋና ነገር

ሥላሴ ከፍጥረት በኋላ የተከናወነ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልገናል። ከፍጥረት በፊት ሥላሴ ዘላለማዊ በሆነ ሁኔታ መኖሩን ከሚያረጋግጡልን ጥቅሶች አንዱ ዮሐንስ 1፡1 -3 ሲሆን፥ እንዲህ ይነበባል፡-

«በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።»

በዚህ ቦታ ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን እንመለከታለን። የመጀመሪያ የቃልን እግዚአብሔርነትና ቃል ከእግዚአብሔር አብ ጋር ያለውን ቅርብ የሆነ ግንኙነት ሲያሳየን፥ ሁለተኛው ይህ ግንኙነት የነበረው ከፍጥረት በፊት መሆኑን ያሳየናል።

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን እምነት አንዱ እግዚአብሔር ኢየሱስ በመሆን እንደገናም መንፈስ ቅዱስ በመሆን በሦስት አካል ተገለጠ እንጂ ሥላሴ የለም በሚል አስተምህሮ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፥ የወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን እምነት መሠረት ደግሞ የተመሠረተው በሥላሴ አሳብ ላይ ነው።

ዮሐንስ በዚህ በምዕራፍ 1፡1–3 በመጀመሪያ ያስቀመጠው አሳብ በቃልና በእግዚአብሔር አብ መካከል ያለውን ልዩነት በግልፅ የሚያሳይ ነው።

«በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» (1፡1)።

በቃልና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው ቅርብ ግንኙነት የሚያሳየው ቃል ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ነው። ቃል እግዚአብሔር አብ አይደለም። እግዚአብሔር አብም ቃል አይደለም። በሁለቱ መካከል ግን የቀረበ ግንኙነት መኖሩን ያሳያል። በእንድ በኩል ልዩነታቸውን በሌላ በኩል የቀረበ ግንኙነታቸውን ሲያሳይ የቃልን እግዚአብሔርነት ጠንከር በማድረግ «ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» ይለናል። በሌላ መንገድ ብናስቀምጠው በእግዚአብሔር አብና በእግዚአብሔር ወልድ መካከል የነበረውን ግንኙነት ያሳየናል።

በሁለተኛ ደረጃ ስለዚህ ግንኙነት ዮሐንስ ሲናገር ከጊዜ በኋላ የተፈጠረ ሳይሆን፥ ከፍጥረት በፊት እንደሆነ ይናገራል።

«ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም» (1፡2–3)።

ዮሐንስ ለአንባቢዎቹ የሚያረጋግጥልን ነገር ሥላሴ መጀመሪያውኑ እንደነበር ነው። «ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።» ፍጥረት ሁሉ ከሥላሴ አንዱ አካል በሆነው በቃል እንደሆነ ቃሉ በግልጽ አስቀምጦታል።

ጠቅለል ባለ መልክ ስናስቀምጠው መጽሐፍ ቅዱሳችን ከፍጥረት በፊት ሥላሴ በዘላለማዊነት መኖሩን ሲያረጋግጥልን፥ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ በመለኮታዊ ባሕሪያቸው እኩል እንደሆኑ ነገር ግን የራሳቸው አካል እንዳላቸው ያስቀምጥልናል። የሥላሴ እምነታችን መሠረት ከኢየሱስና ከመንፈስ ቅዱስ ወደ ምድር መምጣት በኋላ ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ በማንሣት የምናሳየው ብቻ ሳይሆን ከፍጥረት በፊት በዘላለማዊነት የነበረ መሆኑን ቅዱስ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጣል (ዘፍጥ. 1፡1–2፤ ዮሐንስ 1፡1–2)።

የሐዋርያት ሥራ 2፡38 ትርጉም ምንድን ነው?

ይህ ክፍል የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ወይም የ«ኢየሱስ ብቻ» ተከታዮች ዋና መሠረት ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ማለትም በሐዋ. ሥራ 2፡38 እነዚህ ሰዎች

እንደሚሉት በሐዋርያት ዘመን ሰዎች የሚጠመቁት በኢየሱስ ስም ብቻ ነበረ። ይህን ዓይነት ጥምቀት በመቀበልም እነዚህ ሰዎች ደኅንነትን ያገኙ ነበር። በሌላ አነጋገር የ«ኢየሱስ ብቻ» ተከታዮች በኢየሱስ ስም መጠመቅ ደኅንነትን ያስገኛል ብለው ያስተምራሉ። በዚህ ምክንያት የዚህን ክፍል ትርጉም በትክክል ለመረዳት የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለትን በሙሉ ማጥናት ያስፈልገናል።

ሐዋርያው ጴጥሮስ እነዚህን በሐዋ.ሥራ 2:38 ያሉትን ቃላት የተናገረው በጰንጠቆስጤ በዓል ለተሰበሰቡት ላላመኑ አይሁዶች ነው፤ የሐዋ. ሥራ 2:1 እና ቁጥር 5ን ተመልከቱ። ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ተናገራቸው (በቁ. 22–24)። ከዚያም በኋላ በቁ. 25–34 ስለ መሢሑ መምጣት ከዳዊት ትንቢቶችን ጠቀሰ። በቁጥር 36 ላይ መሢሑን ኢየሱስን እንደሰቀሉት ተናግሮ መልእክቱን ጨረሰ። ውጤቱም የሰዎቹ ልብ መነካት ነበር። በሌላ አነጋገር መንፈስ ቅዱስ ወንጀላቸውን አሳያቸው፤ ወቀሳቸው። ዮሐ. 16:8–11ን አንብቡ። ከዚያም እንዲህ ብለው ጠየቁ «ምን እናድርግ?»

የሐዋርያው የጴጥሮስ መልስ ቀጥተኛ ነበር። በመጀመሪያ ንስሐ መግባት ነበረባቸው። ይህ ቃል በግሪክ ሲተረጎም አንድ ሰው አመለካከቱን ሲቀይር ወይም የሕይወቱን መንገድ ሲለውጥ ማለት ነው። መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ንስሐ በማቴዎስ ምዕራፍ 3 ላይ እንደ ሰበከ አስታውሱ። እርሱ ንስሐ የሚገቡት አስተሳሰባቸውንና የአኗኗር መንገዳቸውን በመለወጥ እንደሆነ ነገራቸው። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 መሠረት ይህ መለወጥ ኢየሱስን ለተቃወሙትና ለሰቀሉት አይሁድ አስፈላጊ ነበር።

ቀጥሎም ሐዋርያው «ተጠመቁ» አለ። ጥምቀት ለኃጢአት ይቅርታ አስፈላጊ ነውን? ከሆነ ለምንድን ነው ሐዋርያው ጴጥሮስ ይህን ነገር በሌላ ጊዜ ደግሞ ያልተናገረው? የሐዋ. ሥራ 5:31 እና የሐዋ. ሥራ 10:31 እንደገና ተመልከቱ።

ትክክለኛውን የክፍሉን ትርጉም ለመረዳት እንድንችል ቃላቱንና የግሪኩን ቋንቋ ሰዋሰው ማጥናት ያስፈልገናል። በግሪክ ቋንቋ ሰዋሰው «ንስሐ ግቡ» የሚለው ቃል ሁለተኛው መደብ የብዙ ቍጥር ነው። እንዲሁም «ኃጢአታችሁ ይሰረይ ዘንድ» የሚለው ቃልም በብዙ ቍጥር ስለሆነ አብረው ይሄዳሉ። በሐዋ.ሥራ 10:43 ላይ በዚህ ዓይነት ሐረግና ሰዋሰው እንደተጠቀመ እናያለን። ነገር ግን በግሪኩ አዲስ ኪዳን በሐዋ. ሥራ 2:38 ላይ ያለው «ተጠመቁ» የሚለው ቃል በሦስተኛ መደብ ነጠላ ቍጥር ነው የተጻፈው። ስለዚህም ከኃጢአት ይቅርታ ጋር የተገናኘ አይደለም።

በመሆኑም ሐዋርያው ጴጥሮስ የሚያስተምረው እነዚህ አይሁዶች ኃጢአታቸው ይቅር እንዲባልላቸው ንስሐ መግባት እንደነበረባቸው ነው። በሉቃስ 24:47 ጸሐፊው (የሐዋርያት ሥራንም የጻፈው ሰው) ይህንን አመለካከት ይደግፋል። በዚህ ምክንያት የኃጢአት ይቅርታ የንስሐ ውጤት እንደሆነ እናያለን።

ለምንድን ነው ሐዋርያው ጴጥሮስ እነዚህ ሰዎች በኢየሱስ ስም ይጠመቁ ያለው? መልሱ እርሱ በዚህ ሰብከት ስለ ኢየሱስ ይናገር የነበረው በጰንጠቆስጤ ቀን ለአይሁድ ነበር። ቍጥር 36ን ተመልከቱ። በስብከቱ ውስጥ ዋና አሳቡ ስለ ሥላሴ ወይም ስለ

ጥምቀት አልነበረም። ነገር ግን አይሁዶች ኢየሱስ መሢሕ ነው በሚለው ነጥብ ተሰናክለው ስለነበረ ሐዋርያው ጴጥሮስ በዚያ ነጥብ ላይ አተኮረ። እነርሱም እግዚአብሔር አብን እንደ አባት ስለማየት ችግር ወይም በብሉይ ኪዳን ስለተገለጠው ስለ መንፈስ ቅዱስ ማንነት ጥያቄ አልነበራቸውም። ይልቅስ እግዚአብሔር ወልድ ሥጋ ለብሶ በመገለጥ «የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ» ማለቱ አልዋጥ ብሎ ስለተናነቃቸው ገድለውት ነበርና የሞትን ጣር አጥፍቶ በመነሣት ማንነቱን በመግለጥ መለኮትነቱን ማመን እንዳለባቸው መመስከር ነበረበት።

የሐዋርያት ሥራ 2፡38ን መሠረተ-አሳብ በቅጡ ልንረዳው ያሻል። ክፍሉ የሚያስተላልፈው መልእክት የሚጠመቀው ሰው ከኢየሱስ ጋር ኅብረት እንደሚመሠርት ነው። ይህም በዚያን ጊዜ ይደረግ እንደነበረው ሰውዬው ሲጠመቅ «ኢየሱስ ጌታ ነው» በሚል የአፍ ምስክርነት ይገለጻል (ሮሜ 10፡9፤ 1ኛቆሮ. 12፡31)። ስለሆነም አንድ ክርስቲያን ሲጠመቅ ጥምቀቱ የእምነት መግለጫና ጌታ (አምላክ) ለሆነው ኢየሱስ ራስን የመስጠት ተግባር ነው።

በሐዋ. ሥራ 2፡38 ላይ የሚገኘው ዓረፍተ ነገር አማኞች በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም እንዳይጠመቁ አያግዳቸውም። በማቴ. 28፡19-20 ኢየሱስ ለተከታዮቹ የሰጠውን ትእዛዝ ለመሻር ጴጥሮስም ሆነ ማንም ምንም ሥልጣን የለውም።

ለማጠቃለል «የኢየሱስ ብቻ» ተከታዮች ይህችን አንድ ጥቅስ ከሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክት መደገፊያ ካደረጉ በኋላ በአማኞች መካከል መደነጋገርን ይፈጥራሉ፤ ስሕተትም ያስተምራሉ። ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ ግን የሐዋ. 2፡22-24ን ሳይነጣጥል አንብቦ መተርጎም ያለበት ከዮሐ. 14፡6፤ የሐዋ. 4፡12፤ 16፡31፤ 17፡30-31፤ 1ኛ ጢሞ.2፡5 እና ማር. 16፡16 አባባሎች ጋር በማዛመድ እንደሆነ ልብ እንበል።

እምነታችንን ለመደገፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስንጠቅስ ማስታወስ ያለብን ነጥቦች

(«ኢየሱስ ብቻ» የማይከተሏቸው ነጥቦች)

1. ለእምነታችን መሠረት የምንጠቀምባቸውን አሳቦች የሚደግፉ ጥቅሶችን ነጥለን ከመውሰድ ይልቅ በግልጽ የሚያስተምሩ ክፍሎችን ወስደን መጠቀም አለብን።
2. የእምነታችንን ትምህርት በአንድ ክፍል ላይ ብቻ መመሥረት የለብንም። ይልቅስ ጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ ሌላውን ክፍል ይተረጉማልና፥ በግልጽ የሚያስተምሩት ክፍሎችም በደንብ ግልጽ ያልሆኑትን ክፍሎች ይተረጉማሉና ከፍ ብለን የሐዋ. 2፡38 ትምህርትን ስናጠቃልል እንዳደረግነው ከሌላው ከፍል ግልጽ አባባል ጋር አያይዘን መተርጎም አለብን።
3. በእምነታችን ውስጥ ዋና የሆነ ትምህርትን መመሥረት በምንፈልግበት ጊዜ በሚገባ ለመረዳት ጠቅላላውን መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት እንጂ፥ አንድ ዓረፍተ ነገር ከዚህ፥ ሌላ ዓረፍተ ነገር ከዚያ ወስደን እምነታችንን የምንመሠርት ከሆነ አደገኛ ነው። ወደ ስሕተት ትምህርት ሊመራን ይችላል።
4. ትርጉሙ ምን እንደሚል ለመረዳት እንገነዘባለን። የመጽሐፍ ቅዱስን የተወሰነ ክፍል ለመተርጎም ስናስብ የተደበቀ መንፈሳዊ ምሥጢሩን ለማውጣት ከመፈለግ ይልቅ ሰዋሰውና አገባብን በሚገባ ማወቅና መረዳት ይኖርብናል። የዚህን ፈለግ መከተል እምነታችንን ለመመሥረት ይረዳናል።
5. በዚህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ለእምነታችን ዋና ማዕዘን የሆኑት መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች የተመሠረቱት ሐዋርያት በጻፉአቸው መልእክቶች ላይ ሞምር ነው። ይህም ማለት የእምነታችንን ዋና ነጥቦች የመሠረትነው እንደ ጢሞቴዎስ ወይም እንደ ቲቶ ላሉ መሪዎች ወይም እንደ ቆሮንቶስና እንደ ኤፌሶን ለመሳሰሉት አብያተ ክርስቲያናት ሐዋርያት በጻፉአቸው ትምህርቶችና መልእክቶች ላይ ሞምር እንጂ፥ ከእስራኤል ዘመን ወደ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ስለሆነው ሽግግር የተጻፈ የታሪክ መጽሐፍ በሆነው የሐዋርያት ሥራ ብቻ መሆን የለበትም።
6. ባለፉት ትውልዶች የነበሩት ክርስቲያኖች የማያውቁትን አዲስ ትምህርት ማውጣት ብዙ ጊዜ አደገኛ ነው።

ሥላሴን በተመለከተ ለ«ኢየሱስ ብቻ» ተከታዮች የስሕተት ትምህርት መልስ መስጠት

ሀ. ትምህርታቸው

አንዳንድ የ«ኢየሱስ ብቻ» ተከታዮች እኛ እግዚአብሔርን በሦስት እንደምንከፍለው ወይም እግዚአብሔር «ኮሚቴ» ነው ብለን እንደምናምን አድርገው ይናገራሉ። ይህ ማለት እኛ ሥላሴን እንደ ጴጥሮስ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ እናያለን ማለት ይሆናል።

ለመቃወም እግዚአብሔር አብ ኢየሱስ ነው፤ እንዲሁም ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ነው በማለት ሥላሴን ይክዳሉ። ስለዚህም ኢየሱስ ወደ አባቱ ሲናገር ሌላ አካል ወይም ሥላሴ እስከሌለ ድረስ ለራሱ ነው የሚናገረው ብለው ያምናሉ።

ለ. የእኛ መልስ

እግዚአብሔር መንፈስ ነው (ዮሐ. 4፡24)። ስለዚህም ሥላሴ ሦስት አማልክት ሊሆንና ሊከፋፈል አይችልም። ምድር ከመፈጠሯ በፊት እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በአንድ አምላክነት ነበሩ። እግዚአብሔር በአንድ አምላክነት ይታወቅ ነበር (ዘዳግ. 6፡4–5)። በተጨማሪም እግዚአብሔር በሦስት አካላት ይታወቅ ነበር። ለምሳሌ አብ በፍቅሩ ይታወቅ ነበረ (ዮሐ. 3፡16)። እግዚአብሔር ወልድ አዳኝ ሆኖ ወደዚህ ዓለም በመምጣቱና በመስቀል ላይ በመሞቱ ይታወቃል (ዮሐ. 1፡29)። መንፈስ ቅዱስ የሚታወቀው ስለ ኃጢአትና ስለ ፍርድ ዓለምን በመውቀሱ ነው (ዮሐ. 16፡7–11)።

ኢየሱስ ከአብ ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ የሚነጋገረው ከራሱ ጋር አልነበረም። በዮሐንስ 11፡41 እና 17፡1 ላይ ዓይኑን ወደ ሰማይ አቅንቶ ይናገር ነበር። ወደ ማን ነበረ የሚናገረው? ወደ አብ ካልነበረ ወደ ማን ነበር ታዲያ? ለምንድን ነው «ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ» ያለው? አብ በሰማይ የሚኖር ካልሆነ በማቴ. 3፡7 ስናነብ የማን ድምፅ ነው ከሰማይ የመጣው? ኢየሱስ በተጠመቀበት ጊዜ በርግብ አምሳል ወርዶ በላዩ ላይ የተቀመጠው መንፈስ ቅዱስ ካልሆነ ማን ነበር? (ማቴ. 3፡16)።

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ «እኛ» ብሎ ሲናገር ስለ ራሱና ለራሱ ነው የሚናገረው ትላለች። እንዴት ኢየሱስ ስለ ራሱ ሲናገር «አንተ» ብሎ ይናገራል? በሌላ ስፍራ ስለ ራሱ አስመልክቶ «እኔ» ብሎ ሲናገር ለምንድን ነው ታዲያ በሌላ ስፍራ ስለ ራሱ የሚናገር ከሆነ አንተ የሚለው? በዮሐ. 17፡22–23 ለማን ነው የሚናገረው? ይህ ክፍል ስለ አብና ስለ ወልድ አስመልክቶ እንደሚናገር በግልጥ አያሳይምን?

«ኢየሱስ ብቻ» የሚባለው እምነት ተከታዮች በመንፈስ ቅዱስና በኢየሱስ መካከል ልዩነት የለም እያሉም ያስተምራሉ። መንፈስ ቅዱስ ማለት «ኢየሱስ» ራሱ በአማኞች ልብ ውስጥ ሲኖር ነው ይላሉ።

እንዲህ ዓይነቱ ትምህርት እንደ እግዚአብሔር ቃል አይደለም። የሚከተሉት ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ የሚናገሩት ብዙ ከሆኑት ጥቅሶች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው። ነገር ግን ይህ የኢየሱስ ሥራ ተብሎ አይታወቅም።

መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን መርቷል፤ ጠርቷልም (የሐዋ. ሥራ 8፡29፤ 10፡19–20፤ 13፡2፤ 20፡28፤ 16፡7 እና 9)።

ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ዋሹት (የሐዋ. ሥራ 5፡3)።

ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ተፈታተኑት (የሐዋ. ሥራ 5፡9)።

መንፈስ ቅዱስን ተቃወሙት (የሐዋ. ሥራ 7:51፤ 1ኛ ተሰ. 5:19)።

መንፈስ ቅዱስን ሊያሳዝኑ ይችላሉ (ኤፌ. 4:30)።

መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስ ምን እንደሚያስተምር መራው (1ኛ ቆሮ. 2:13)።

ነቢያት ምን እንደሚናገሩ በመንፈስ ቅዱስ ተነግሯቸው ነበር (የሐዋ. ሥራ 1:16፤ 1ኛ ጴጥ. 1:11–12፤ 2ኛ ጴጥ. 1:21)።

መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ይወቅሳል (ዮሐ. 16:7–11)።

መንፈስ ቅዱስ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ያመለክታል፤ እርሱንም ያከብረዋል።

መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ይሰጣል (1ኛ ቆሮ. 12:4–11)።

መንፈስ ቅዱስ ከአብ ያለውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማሳየት ምን መጸለይ እንዳለብን በውስጣችን ሆኖ ይማልድልናል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን ጸሎት በመውሰድ ወደ እግዚአብሔር አብ ያቀርባል።

ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ሊሆን አይችልም ማለት ነው (ሮሜ 8:26–27)። ይህ ልዩነት በ1ኛ ቆሮ. 2:10 ላይም ታይቷል።

መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ የተለየ መሆኑን የሚያሳዩ ጥቅሶች፦ ገላ. 4:6፤ ኤፌ. 4:4–6፤ 2:18፤ ቲቶ 3:4–6።

እኛ ራሱን እንደ እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በሦስት አካላት በገለጠ በአንድ አምላክ እናምናለን። ከላይ በተጠቀሱት ጥቅሶች እግዚአብሔር አብ ኢየሱስ እንዳይደለ ወይም

ከሐዋርያት ጊዜ ጀምሮ ሥላሴን የካዱት ሰዎች ሐሰተኞች አስተማሪዎች ተብለው ተወግዘዋል።

ደኅንነት በጥምቀት ለሚለው የስሕተት ትምህርት መልሶች

ሀ. ትምህርታቸው

በ1921 ዓ.ም. በአሜሪካ አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎች አዲስ ትምህርት እንዳገኙ ተናገሩ። እነርሱ የዚህ በኢየሱስ ስም የመጠመቅ እንቅስቃሴ ጀማሪዎች ነበሩ። እነርሱ ይህ ዓይነቱ ጥምቀት ለአንድ ነፍስ መዳን አስፈላጊ ነው ብለው ነበር። የ«ኢየሱስ ብቻ» ተከታዮች ብዙ ጊዜ የሚጠቅሷቸው ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው፦

በኢየሱስ ስም ብቻ ስለ መጠመቅ የሐዋ. ሥራ 2:38፤ 8:16፤ 10:48፤ 19:5፤ 22:16።

ደኅንነትን በጥምቀት ስለ መቀበል 1ኛ ጴጥ. 3:20–21፤ ዮሐ. 3:5፤ ሮሜ 6:3–4፤ ገላ. 3:27፤ ቲቶ 3:5።

ከላይ ከተጠቀሱት የሐዋርያት ሥራ ጥቅሶች ጋር ለመስማማት በሚሞክሩበት ጊዜ የሚያስቡት አብና መንፈስ ቅዱስ ራሱ ኢየሱስ ነው ብለው ነው (ማቴ. 28:19)። በነጠላ ቍጥር እስከተጠቀመ ድረስ የሚያመለክተው ኢየሱስን ብቻ ነው ይላሉ።

ለ. የእኛ መልስ

በመስቀል ላይ የተሰቀለው ወንበዴ ወደ ገነት የገባው ሳይጠመቅ ወይም ሌላ መልካም ሥራ ሳይሠራና እየሞተ ላለ ነው (ሉቃስ. 23:40–42)።

«የኢየሱስ ብቻ» ወይም የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን በብሉይ ኪዳን የነበረው መገረዝ በጥምቀት ተተክቷል ብላ ታስተምራለች። ስለዚህም አንድ ሰው ለመዳን እንዲችል መጠመቅ አለበት ይላሉ። ነገር ግን ይህ ክርክራቸው በሥራ የመዳንን አሳብ ስለሚያካትት ትክክል አይደለም። ምክንያቱም አብርሃም የጸደቀው ሳይገረዝ በፊት በእምነት ነው (ሮሜ. 4:9–12፤ ዘፍጥረት 15:6 እና 17:9–14)።

ሐ. መደምደሚያ

የውኃ ጥምቀት አንድን ሰው ለማዳን አይችልም። ምክንያቱም አንድ ሰው የኃጢአት ይቅርታ ሊያገኝ የሚችለው በፈሰሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም አማካይነት ነው። አንድ አማኝ በሚጠመቅበት ጊዜ በክርስቶስ ላይ ያለውን የእምነት ምስክርነት ነው የሚሰጠው። ምስክርነት እስከሆነ ድረስ በአንደበት ከሚሰጠው ምስክርነት ጋር ዋጋው እኩል ነው፤ (ሮሜ 10:9–10ን ተመልከቱ)። የአንደበት ምስክርነትና የጥምቀት ምስክርነት የሁለቱም ዋጋ ለሌሎች የሚገልጠው በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ጌታን ለመከተልና ለመታዘዝ ፍላጎት ያለ እንደሆነ ነው። ስለዚህ አንድ ሰው በዚህ መንገድ በሚመሰክርበት ጊዜ እርሱ ሕይወቱን ለጌታ መስጠቱን ያሳያል (ሮሜ 6:1–11)።

በምንም ዓይነት መንገድ አንድ ሰው በመጠመቁ በዚያ ሥርዓት የእግዚአብሔር ልጅ ሆኗል ማለት አንችልም። በዮሐንስ 1:12 የተጻፈውን ስንመለከት ስለ ጥምቀት ምንም አይናገርም። በኤፌሶን 2:8–9 እንደተጻፈው ደኅንነት መልካም ነገር በመሥራት እንዳልሆነ ይናገራል። በ1ኛ ዮሐንስ 1:19 ላይ እንደተጠቀሰው ከኃጢአታችን የሚያጥበን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም እንደሆነ ይናገራል። አሁንም መሠረታዊ ሐዋርያት ነን ባዮቹ በጥምቀት ስለመዳን እንደሚያስተምሩ ለማስጠንቀቅ ስንፈልግ ከፍ ብለን የጠቀስናቸውን ጥቅሶች ለሌሎች መተርጎም ያለብን ከሌሎች በደኅንነት ጉዳይ ግልጽ ከሆኑ ጥቅሶች ጋር አመዛዝነን እየጠቆምን፥ የውኃ ጥምቀት አማኙ በእምነቱ ለኃጢአት የመሞቱና ለጽድቅ የመነሣቱ፥ የክርስቶስ አካል የሆነችው የቤተ ክርስቲያን አንድ ብልት የመሆኑ ውጫዊ ምስክርነት ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባናል።

ስለዚህ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን (የ«ኢየሱስ ብቻ» ቡድኖች) አንድ ሰው የሚድነው እርሱ ወይም እርሷ በኢየሱስ ስም በሚጠመቁበት ጊዜ ብቻ ነው በማለት የሚያስተምሩትን ትምህርት ስሕተት ነው ብለን እንደመድማለን።

ክርስቲያኖች ለምን ይጠመቃሉ?

ስለ ጥምቀት በምናነሣበት ጊዜ ስለ ደኅንነት ማንሣት አለብን። ደኅንነት የምናገኘው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ብቻ ነው (1ኛ ዮሐንስ 1:12)። መጽሐፍ ቅዱስ በጥምቀት ደኅንነትን እንደምናገኝ አያስተምረንም፤ ጥምቀት የሚያድን ከሆነ የክርስቶስ የመስቀል ሥራ ከንቱ ይሆናልና። ጥምቀት የሚያድን ካልሆነ ለምን ክርስቲያኖች መጠመቅ ያስፈልጋቸዋል?

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የውኃ ጥምቀትን ስናጤን መመልከት የሚገቡን፡–

ሀ. የዮሐንስ ጥምቀት

የዮሐንስ ጥምቀት ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሞቱ በፊት የነበረ ሲሆን፥ «የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥሪጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ» (ማር. 1፡3) ጋር የሚያያዝ ነው። ጥምቀቱ ሰዎችን እንዲናዘዙ በማድረግ ለሚመጣው መሢሕ የሚያዘጋጅ ሲሆን፥ ሙሉ ለሙሉ አዲስ ሕይወትን ሊሰጠን የሚችል አልነበረም።

ለ. የክርስቶስ ጥምቀት

ኢየሱስ ክርስቶስ «የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ» በሠላሳ ዓመቱ መጠመቁንና የተጠመቀውም በዮሐንስ እንደሆነ እናነባለን (ማቴ. 3፡13–17)።

ኢየሱስ ኃጢአቱን ለመናዘዝና ከኃጢአቱ ለመዳን አልተጠመቀም። ዮሐንስ «የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» በማለት ኢየሱስ ክርስቶስን ከመጠመቁ በፊት ወደ ፊት የሚያከናውነውን ሲናገር ከዚህም በላይ ሊያጠምቀው እንኳ እንዳልደፈረ በማቴ. 3፡13–15 እናነባለን። ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው የእግዚአብሔርን ፈቃድና «ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም» (ማቴ. 3፡15) እና ከአማኞች ጋር ያለውን አንድነት ለማሳየትም ጭምር ነበር።

አማኞች ለምን ይጠመቃሉ?

ሀ. የኢየሱስ ክርስቶስን ትእዛዝ ለመፈጸም ይጠመቃሉ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ለሐዋርያት የሰጣቸው አንዱ ትእዛዝ– «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው፥ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» የሚል ነበር (ማቴ. 28፡19–20)። አማኞች ይህንን የጌታ ትእዛዝ ለመጠበቅና ለመፈጸም ሲሉ ይጠመቃሉ።

ለ. አማኞች እምነታቸውን ለመግለጽና ከሌሎች አማኞች ጋር ያላቸውን ኅብረት ለማሳየት ይጠመቃሉ (የሐዋ. 2፡41–42)። ጥምቀት በፊት የምንናገርበትንና የምናምነውን ነገር ትተን በክርስትና ሕይወት እንደ እግዚአብሔር ቃልና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመመላለስ ከአማኞች ጋር ያለንን ኅብረት ለማሳየት የምናደርገው ሥርዓት ነው።

ሐ. በጥምቀት የክርስቶስን ምሳሌ ለመከተል መወሰናችንን እናረጋግጣለን (ሮሜ 6፡4–8)። በጥምቀት ጊዜ በምንጠመቅበት ውኃ ውስጥ ስንገባ ክርስቶስ እንደ ሞተ መሞታችንን፥ ወደ ውኃ ውስጥ ስንጠልቅ ኢየሱስ እንደተቀበረ መቀበራችንን፥ እንዲሁም ከውኃ ውስጥ ስንወጣ ኢየሱስ ከሞት እንደ ተነሣ በአዲስ ሕይወት መነሣታችንን እናሳያለን።

ምልክቶችን የደኅንነት ማረጋገጫ ለሚያደረገው የስሕተት ትምህርት መልሶች

ሀ. እነርሱ የሚያስተምሩት፥–

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አንድ አማኝ በልሳኖች መናገር አልቻለም ማለት መንፈስ ቅዱስ ስለሌለው አልዳነም ማለት ነው ብለው ያስተምራሉ። ስለዚህ በዚህ ቡድን ውስጥ ያሉ ሰዎች ብዙ ጊዜ በታላቅ ጥረት በልሳን መናገርን ይፈልጋሉ። በየቀኑ እንኳን

መዳናቸውን በልሳን በመናገር ለማረጋገጥና ለማሳየት ይጣጣራሉ።

እነዚህን ምልክቶች በተመለከተ ለትምህርታቸው መሠረት የሚያደርጉት በሚከተሉት የሐዋርያት ሥራ የንባብ ክፍሎች ላይ ነው፦

የሐዋ. ሥራ 2፡14 ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበላቸው በልሳን መናገራቸው ምልክት ነበረ ይላሉ።

የሐዋ. ሥራ 8፡13–17 ሲሞን መጠቀም የሚፈልገውን ነገር አየ ወይም ሰማ ብለው ያስተምራሉ። የሚፈልጉትም ምልክቱን መቀበል ነው።

የሐዋ. ሥራ 10፡44–46 ጴጥሮስ የልሳኖችን ምልክት ባየ ጊዜ ቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ መዳናቸውን አወቀ ብለው ያምናሉ።

የሐዋ. ሥራ 19፡6 በዚህ ቦታ ያሉት ሰዎች ስብከት ከሰሙ በኋላ ተጠመቁ፤ ነገር ግን የልሳኖችና የትንቢት መናገር ምልክቶች መዳናቸውን አረጋገጡ ብለው ያምናሉ።

ለ. የእኛ መልስ

ከላይ በተጠቀሱት የሐዋርያት ሥራ ክፍሎች ለአንባቢው «ለቴዎፍሎስ» በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ወይም በልሳን መናገር ከነፍሳቸው መዳን ጋር ግንኙነት እንዳለው የሚያሳይ ምንም ነገር የለም። መዳናቸውን ለማሳየት ምልክቶችን ይጠቀሙ ነበር የሚል አንድም ቃል የለም። አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት እና ከእነርሱ ጋር የነበሩት ሌሎች መዳናቸውን በልሳን ምልክትነት ማሳየት አልነበረም። በሐዋ. ሥራ 1፡8 ለአይሁድ የተሰጠው ተስፋ መፈጸሙ ግልጽ እንዲሆን ነበር የተሰጠው። በዚሁ መሠረት በሐዋ. ሥራ ምዕ. 8 በሰማርያ ምን እንደሆነ እንዲያውቁ፥ በሐዋ. ሥራ 10 ለአሕዛብ ምን እንደሆነላቸው እንዲያውቁ፥ በሐዋ. ሥራ 19 የንስሐን ጥምቀት ብቻ ለሚያውቁ ምን እንደሆነላቸው እንዲያውቁ ነበር የልሳን ምልክት የተሰጣቸው። በሌላ አነጋገር እነዚህ ሦስት የተፈጸሙ የልሳን ምልክቶች በሐዋርያት ሥራ 2 ላይ ከተፈጸመው ጋር አንድ ያደርጓቸዋል። ይህ ወንጌል በሰማርያ ሰዎች መካከልና በአሕዛብ መካከል እየሠራ እንደነበረ ያሳያል። ይህ ለአብያተ ክርስቲያን ዘመን መግቢያ ነበረ።

ሐ. መደምደሚያ

ሉቃስ ወንጌሉንና የሐዋርያት ሥራን የጻፈው የኢየሱስን ታሪክና የቤተ ክርስቲያን ዘመን አጀማመርን ታሪክ ለቴዎፍሎስ ለመንገር ነበር። ምን ተፈጽሞ እንደነበረ የሚያስረዳን ታሪክ ስለሆነና ለእምነታችን መሠረት የሚሆነን ማብራሪያ እስከዚህም ስለማይታይበት ለዚያ ወደ ሌሎች መጻሕፍት ይኖርብናል። በልሳኖች ስለ መናገር ያለውን አንዱን የሐዋርያት ሥራ ክፍል ለእምነታችን መሠረትነት የምንጠቀምበት ከሆነ እንግዲያው ንብረታችንን በሙሉ ሸጠን በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን ላሉ ሰዎች ማከፋፈል አለብን ማለት ነው፤ (የሐዋ ሥራ 4፡32–37ን ተመልከቱ)። ምልክቶችን ለእምነታችን የግል ልምምዶች አድርገን ወስደን በዶክትሪን ላይ መመሥረት የለብንም። አለበለዚያ ልሳንን ዋነኛ አስፈላጊ ነገር አድርገን ወስደን ሁሉንም ነገር

ለመተው ሥልጣን አልተሰጠንም። እንዲህ ዓይነቱ አተረጓጎም የተሳሳተ ነው።

አንድ ሰው መዳኑን ለማረጋገጥ ምልክቶች መታየት አለባቸው ማለት ክርስቶስን ለማመን ለሚፈልጉ ሰዎች አስጨናቂ ሸክም ይሆንባቸዋል። በልሳን የማይናገሩት ሰዎችስ? እንግዲያስ እነርሱ መዳን አይችሉም ማለት ነዋ!? ሐዋርያው ጳውሎስ ሁሉም ክርስቲያኖች በልሳን እንደማይናገሩ ይናገራል (1ኛ ቆሮ. 12፡30)። በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት እግዚአብሔር እንደወደደ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይሰጣል (ሮሜ 12፡3)። ስለዚህ አንድ ሰው ደኅንነትን እንዳገኘ ለማሳየት የልሳን ምልክቶች መገለጥ አለባቸው የሚለው ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ውጪ ነው። ምልክቶች መታየት አለባቸው ቢባል እንኳ ምልክቱ የመንፈስ ፍሬ እንጂ ልሳን አይሆንም (ዮሐ. 15፤ ገላ. 5፡23)። ይህም የመንፈስ ፍሬ የሥጋን ፍሬ ተክቶ አዲስ የተለወጠውን ሕይወት በውብ መዓዛ የሚሞላው ነው– ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት።

የመጨረሻ

ማሳሰቢያዎችና ማስጠንቀቂያዎች

አንድ ሰው ሥላሴን በሚክድበት ጊዜ ስለ ደኅንነት ያለውን ትምህርት በሙሉ ይገለብጣል። እንደ «ኢየሱስ ብቻ» ተከታዮች ትምህርት እግዚአብሔር ልክ በቀጠራቸው ሠራተኞች ላይ ስሕተትን ለመፈለግ የሚሞክር፥ ከዚያም የሚቀጣቸው ወይም ከሥራ የሚያስወጣ ቅጡ አሠሪ ዓይነት ነው። በሌላ አነጋገር ከእርሱ እንደሚጠብቀው ካልተጠመቀ እግዚአብሔር አይቀበለውም ወይም አይቀበላትም፤ ስለዚህም ያ ሰው ሊድን አይችልም ይላሉ።

ይህን ቡድን የሚከተሉ በፍርሃት ውስጥ ይኖራሉ። በየጊዜው መዳናቸውን ለማሳየት የተወሰኑ ነገሮችን ማድረግ አለባቸው። በሌላ በኩል የዘላለም ሕይወት ያለን ክርስቶስ ለእኛ ባደረገው በሞቱና በትንሣኤው ሥራ ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው። ስለዚህ የ«ኢየሱስ ብቻ» ተከታዮችን በምናገኛቸው ጊዜ በእግዚአብሔር ቃል መሠረትነት በውስጣችን ስላለው ደስታ ለመናገር ታማኝ ምስክሮች እንሁን።

የሚከተለውን ስለ ሐሰት አስተማሪዎች እና ትምህርታቸው የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ካነበባችሁ በኋላ ጥያቄዎቹን መልሱ።

ዕብራውያን 13፡9–በእግዚአብሔር ቃል ከተገለጠው በቀር፥ የማይስማማ አዲስና እንግዳ ትምህርት አንቀበልም። መንፈሳዊ መሪዎች ለ1990 ዓመታት ያህል ያልሰሙትን አዲስ ትምህርት መስማት አደገኛ ነው። ለምን?

1ኛ ዮሐንስ 2፡22– የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን (የ«ኢየሱስ ብቻ» ቡድን) እግዚአብሔር አብ እንዳለ ይክዳሉ። ይህ ጥቅስ ምን ብሎ ይጠራቸዋል?

1ኛ ዮሐንስ 2፡24–25– በእምነታችን እንድንቀጥል እንበረታታለን፤ የእግዚአብሔርን ቃል ሁልጊዜ በማጥናት መልካሙን የክርስትና እምነት መሠረታችንን ማጥበቅ ይኖርብናል። የሥነ መለኮት መጻሕፍትን ደግሞ በማንበብ በዚያም መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታችንን በሚገባ እንረዳለን።

ጠንካራ መሠረት እንዲሰጣችሁ ምን እያደረጋችሁ ነው?

ማቴዎስ 7፡21–23 እነዚህ ሐሰተኛ ተዓምረኞች በዚህ ክፍል የተጠቀሰውን የጌታ ምስክርነት የሚያልፉ ይመስልሃል?

ገላትያ 1፡6–9 – ሐዋርያው ጳውሎስ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ቢሰማ ምን ይል ነበረ? የስሕተት ትምህርት አስተማሪዎች ከየት እንደሚመጡ የሚናገሩ አንዳንድ የንባብ ክፍሎችን አንብቡ።

1ኛዮሐ. 2፡19– እነዚህን የስሕተት አስተማሪዎችን «ወንድሞች» ብለን ልንጠራቸው እንችላለን?


ማቴ. 7፡15– ምንም እንኳ የ«ኢየሱስ ብቻ» ቡድን ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ቢሸከሙና ብዙ ጥቅሶችን ቢጠቅሱም ይህ ጥቅስ ስለ እነርሱ ምን ይላል?

የሐዋ. ሥራ 20፡29–30– ሐዋርያው ጳውሎስ እርሱ በኤፌሶን ያሉትን አማኞች ትቶ ከሄደ በኋላ የስሕተት አስተማሪዎች እንደሚከተሉ ያውቅ ነበር።

በእነርሱ ዘንድ ያለውን አገልግሎቱን በሙሉ እንዳያጠፉበት ወይም ከንቱ እንዳያደርጉበት ምን አድርጎ ነበር?

ከሐዋርያው ጳውሎስ በመማር የእግዚአብሔርን ሥራ እንዳያጠፉ የስሕተት ትምህርትን ለመከላከል ምን ማድረግ አለብን?

ራእይ 2፡2– በምን መንገድ ነው ዛሬ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ለእኛ መልካም ምሳሌ የምትሆነን? ስለቀረበላቸው የስሕተት ትምህርት ምን አደረጉ? ይሁዳ 24።



አቤት ውሸት!

ጸሐፊው – ዴአ ተስማ

አሳታሚ
BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING
መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት
የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
የፖ. ሣ. ቁጥር 127፥ አዲስ አበባ

ማውጫ

መቅድም .....

መግቢያ 1

1. በቤተሰብ ውስጥ የሚከሰት ውሸት..... 1

2. በጎረቤትና በአካባቢ ያለው ውሸት..... 4

3. በገበያና በጉሊት ያለው ውሸት..... 5

4. በሱቅ ያለው ውሸት..... 11

5. ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ውሸት..... 23

መደምደሚያ..... 30

መቅድም

አቤት ውሸት! በሚል ርእስ ይህችን ትንሽ መጽሐፍ ለማዘጋጀት የተነሣሣሁበት ምክንያት ውሸት የሚናገሩና የሚያጭበረብሩ ሰዎች በዓለም ላይ በመብዛታቸው ብቻ ሳይሆን ከአማኞችም መሀል የዚህ ዓይነት ክፉ ድርጊት የሚፈጽሙ ብዙ ሰዎችን ስላየሁ ውሸት ምን ያህል ክፉ ነገር እንደሆነ ለማሳየት ስለፈለግሁ ነው።

ያለፈው ኮምኒስት መንግሥት ሰውን በእግዚአብሔር ላይ አደፋፍሮ ለማነሣሣትና ለማስካድ ፈልጎ «ኃጢአት የሚባል ነገር የለም፤ እውነት ማለትም ትርጕሙ ብዙኃኑ ይሆናል ብለው የተስማሙበት ሐቅ ነው፤ በግድም በውድም ተፈጻሚነት ያለው ይህ ሐቅ ነው። እውነት ስለሚባለው ሌላ ጉዳይ ምንም አትጨነቁ» እያለ ያስተምር ነበር። በአንድ አካባቢ ያሉ ሰዎች ተስማምተው የሚፈጽሙት ወንጀል እንደ ተገቢ ተግባር ይቆጠር ነበር ማለት ነው። ለእግዚአብሔር ትእዛዝና ለቅዱስ መጽሐፍ ተቃራኒ የሆኑ አስተሳሰቦችን የተቃወሙ ሃይማኖተኞች ብዙ መጉላላትና መታሠር፥ በአካልና በአዕምሮም ብዙ ጭንቀት እንደደረሰባቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ቀደም ሲል በአብያተ ክርስቲያን ላይ ታልሞ በነበረው ይፋ ባልሆነ የባህል አብዮት ምክንያት የተዘጉ አብያተ ክርስቲያን እግዚአብሔር በሰጠን ተራ ተከፍተዋል፤ የቤተ ክርስቲያን ንብረቶችም ተመልሰዋል። ነገር ግን ኮምኒዝም በሰዎች አዕምሮ የተከለው ክፉና ሐሰተኛ ግንዛቤዎች እንዲሁም ልማዶች ከአንዳንድ ሰዎች አዕምሮ አልተፋቁም። ይህም ሰዎች በየዕለቱ በሚያሳዩዋቸው ጠባዮች፥ ከአፋቸው በሚያወጧቸው ንግግሮችና በሚፈጽሟቸው ማኅበራዊ ተግባሮች ሲንጸባረቁ ይታያሉ። ከነዚህም አንዱ «ውሸት» ነው። ውሸት ሐሰትን፥ ማጭበርበርን፥ ማታለልንና መስረቅንም ይዛመዳቸዋል።

ከጥንት ጀምሮ አልፎ አልፎ ሰዎች ውሸትን መውደዳቸውን በአንዳንድ አባባሎች ይገልጻሉ፤ ለምሳሌ «ሐሰተኛ እንደዋርካ ይተልቅ፤ እውነተኛ እንደ ሰንበሌጥ ይድረቅ።» «ዋሽ ቢሉኝ እዋሻለሁ፤ ንፋስን በወጥመድ እይዛለሁ።» «ሐሰት ስለበዛ እውነት ሆነ ዋዛ» እያሉ ለሐሰት እየወገኑ ሲናገሩ ተሰምተዋል። ይህ እንግዲህ «ውሸትም የሕዝቡ ባህል ሊሆን ነው ወይ?» የሚያሰኝ እየሆነ ሄዷል ማለት ነው። በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ አማኞች ከማያምኑ ሰዎች ባላነሰ ሁኔታ እየዋሹ መሆናቸውን በብዙ ነገር ስላየሁ ይህንን ስሕተት ለማሳሰብና ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደሚል ለመጠ`ምና ለመምከርም ስለፈለግሁ ይህችን ጽሑፍ አቅርቤአለሁ። «ስለዚህ ውሸት አትናገሩ! ሁላችንም የአንድ አካል ክፍሎች ስለሆንን እርስ በርሳችን እውነት እንናገር» (ኤፌ. 4፡25)።

«ለምትዋጁበት ቀን መያዣ እንዲሆናችሁ የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ» (ኤፌ. 4፡30)።

«ይልቅስ እርስ በርሳችሁ ደጎችና አዛኞች ሁኑ» (ኤፌሶን. 4፡32) ይላል።

መዋሸት በግለሰቡ ሕይወት ውስጥ ያለውን መንፈስ ቅዱስ አሳዝኖ ግለሰቡን ለመንፈሳዊ ተግባር ስሜት የሌለው ያደርጋል። መንፈስ ቅዱስ አዘነ ማለት ክፉውን የሚቃወመው መንፈሳዊ ኃይል ከዳ ማለት ነው። ለመልካም

ተግባር የሚያነሣሣው በጎ መንፈስ ተለየው ማለት ነው። ከዚህ በኋላ የመንፈስ ፍሬ የሆኑ መልካም ጠባዮች ሁሉ ይወገዱና በዚያ ፋንታ የሥጋ ፍሬ የሆኑ ክፉ ጠባዮች በቦታው ይተካሉ። ሰው ከተመኘለት የመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት ደረጃ ወደ ክርስቶስ ሙላት (ቆላስይስ 2፤10) እንዳይደርስ ዕንቅፋት ሆነው ከሚጠቀሱ ነገሮች አንዱ መዋሸት ነው። ስለዚህ ይህች ጽሑፍ ሰው ከቤቱ ጀምሮ እስከ ጎረቤት፥ ገበያ፥ ሱቅና የተለያዩ የሥራ ቦታዎች ድረስ በየዕለቱ በሚውልበት ውሎ ሁሉ ምንና ምን እየዋሸ እንደሚውል፥ እንዲሁም መዋሸት በጌታ ዘንድ ምን ያህል እንደሚጠላ ትናገራለች። በመደምደሚያውም ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ውሸት ምን ዓይነት ቦታ እንዳለው ጥቅስ በጥቅስ ተጠቅሷል።

ውሸትን የሚያዘወትር ሰው በዚህች መጽሐፍ መንፈስ ቅዱስ በሚመክረው ምክር እንዲመለስና ልቡንና አንደበቱን ከዚህ ክፉ ልማድ እንዲያጸዳ የዘወትር ጸሎቴ ነው።

ደራሲው ዴአ ተሰማ

አቤት ውሸት!

መግቢያ

ውሸት፥ ማታለልና ማጭበርበር ዛሬ በዓለማችን እጅግ ተስፋፍተዋል። ትልቁ ትንሹ፥ ሽማግሌው ወጣቱ፥ ምሁሩ መሃይሙ ሁሉም ለራሱ ሳይለፋና ሳይደክም፥ በሌላ ሰው ድካምና ላብ ተጠቅሞ ለመኖር ጥረት ያደርጋል። ለራሱ ሊጠቀም ፈልጎ፥ ኃይል ስለማያዋጣውና ስለማይመቸው ይዋሻል፤ ያታልላል፤ ወይም ያጭበረብራል። ውሸት በሁሉም ቦታ መኖሩ ግልጽ ነው።

1. በቤተሰብ ውስጥ ያለ ውሸት

ሀ) አንዳንድ ባል ለሚስቱ ይዋሻል። ስለሚያገኘው ደመወዝ፥ ስለሚያገኘው ገቢ፥ ስለሚያወጣው ወጪ፥ ስለሚውልበት ውሎ፥ ስለሚገባላት ተስፋ...ይዋሻል። ሚስትም ለባሏ እንዲሁ ለምትወስደውም ሆነ ለምትሰጠው ነገር ትዋሻለች። እንዲያውም ትክክለኛ ነገር ለመናገር የሚከብዳቸው ሰዎች አሉ። ውሸትን ስለተለማመዱ ምንም ቅር ሳይሉቸው ይዋሻሉ። ለምን እንደሚዋሹ እንኳን ሳይረዱ ይዋሻሉ። ምን ሊያተርፉ ወይም ከምን ሊድኑ እንደፈለጉ ገና ሳያውቁ የሚዋሹም አሉ። ይህ በቤተሰብ መሥራቾች (በባልና በሚስት) መካከል አለመተማመንን፥ ከጠነከረ ደግሞ የቤተሰብ መፍረስን ሊያስከትል ይችላል።

ለ) አንዳንድ ልጆች ለወላጆቻቸው ይዋሻሉ። ወደተላኩበት ሳይሆን ወዳሰቡበት ይሄዳሉ። የቤት ሥራን ሠርተው

ወላጆቻቸውን ወይም አሳዳጊዎቻቸውን ሳይረዱ ወይም ወላጆቻቸው «በአልባሌ ቦታ አትዋሉ» ብለው ለሚሰጧቸው ምክር ዋጋ ሳይሰጡ የውሸት ምክንያቶችን ይደረድራሉ።

«ዛሬ ጥናት አለብኝ፣ አስተማሪዬ ለተጨማሪ ትምህርት ጠርቶኛል፣ ፕሮግራም አለብኝ፣ ከእገሌ (ከእገሊት) እንትን እወስዳለሁ፣ ይህ ጉዳይ ዛሬ ያሳድረኛል» እያሉ ይዋሻሉ። ደግሞም አንድ ዋጋ ያለውን ነገር ይወስዱና «በፍጹም አልወሰድኩም፣ አላውቅም፣ አላየሁትም፣...» እያሉ ምለው ይዋሻሉ። ልጆች ዕውቀት የሚቀስሙበት የመጀመሪያው ትምህርት ቤት ቤታቸው ሲሆን አስተማሪዎቹም ወላጆቻቸው ወይም አሳዳጊዎቻቸው ናቸው። ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች የሚዋሹ ከሆነ ልጆች ውሸትን የሚማሩት ከእነርሱ ነው። እነርሱ ውሸትን እንደ ወላጆች በረከት አድርገው ይቀበላሉ።

አንዳንድ ሰዎች ልጆቻቸው ብልጥ እንዲሆኑላቸውና ተታልለው የሚገቡ ገሮች ሳይሆኑ አታልለው የሚበሉ ጎበዞች እንዲሆኑላቸው ያሠለጥኗቸዋል። ገና ሕፃናት ሳሉ አንድን ነገር «እንካ» ይሉና ሕፃኑ ለመውሰድ እጁን ሲዘረጋ እየከለከሉ፥ ደግሞም ከእነርሱ የወሰዱትን ነገር «የለም አልወሰድኩም» እያሉ፥ ደግሞም ምንም በሌለበት «ጅብ መጣ!» እያሉ፥ የማያደርጉትን «ጆሮህን እቆርጣለሁ!» እያሉ ገና በሕፃንነቱ ለውሸት ያሠለጥኑታል።

የእነርሱ ዓላማ «ልጆችን እናስታለን፥ እናጫውታለን፥ ንግግር እናስተምራለን፥ ጣፋጩንና ኩልትፍትፍ የሚለውን ሸጋ ንግግራቸውን እንሰማለን» ለማለት ቢሆንም፥ በልጆች

አዕምሮ በማይፋቅ ቀለም ውሸትን እየጻፉባቸው ነው። ይህ ብቻም አይደለም። በሰዎችና በእንስሳት እየመሰሉ መጥፎ ተረት ይነግሯቸዋል። ለምሳሌ የጦጣን ብልጠት፥ የአንበሳን ኩራት፥ የሌባን አታላይነት፥ የቀማኛን ነጣቂነት (ዘራፊነት)፥ የፍቅረኞችን መፈላለግ፥ የአጓጉል ወንዶችና ሴቶችን መማገጥ.... ወዘተ አንሥተው በጣፈጠ ሁኔታ ይነግሯቸዋል። በተጨማሪም ልጆቻቸው ለማንም እጅ የማይሰጡ ደፋሮች እንዲሆኑላቸው «ግጨው! ካ አድርገው! እንካ በዚህ በለው! እንዲህ ብለህ/ሽ/ ስደበው /ስደቢው/!» እያሉ ይመክሯቸዋል። በዚህ እየተለማመዱ አድገው ትልቅ ሲሆኑ የማይለያቸውን መጥፎ ጠባይ በአዕምሮአቸው ይተክላሉ። እውነት፥ ጽድቅ፥ ቅድስናና መልካም ጠባይ አድጎ ሊስፋፋበት በሚችለው ለጋ አዕምሮአቸው ውስጥ መጥፌያቸው የሚሆነውን የማይጠቅም ግላንግስ ይሞላሉ።

እንግዲህ በዚህ ዓይነት መጥፎ ልምምድ ውስጥ ያደጉ ልጆች የመጀመሪያውን የውሸት ፍሬ የሚያቀምሱት ለወላጆቻቸው ወይም ለአሳዳጊዎቻቸው ነው። ቀምሰው የጣፈጣቸው ጣፈጣቸው፣ ያንገሸገሻቸው ወላጆች ግን ሲራገሙ፥ ከቤት አውጥተው ሲያባርሩና ለአላፊው አግዳሚው ስሞታ ሲያሰሙ ይደመጣሉ። በልጆቻቸው ምክንያት የታሠሩ፥ መቀጫ የከፈሉና ሀብት ንብረታቸውን ያጡ እጅግ ብዙዎች ናቸው። የገዛ ልጆቻቸውን በአደባባይ የካዱና «አርም» ብለው የተውዋቸውም ጥቂቶች አይደሉም።

ስለዚህ የሕፃናት አዕምሮ ውሸት፥ ማታለልና ማጭበርበር ሳይጠቀጠቅበት በንጽሕና እንዲዳብር ወላጆች ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል። በልጅነት የለመዱት ነገር

መልካምም ይሁን መጥፎ ባደጉ ጊዜ አይረሳም (ምሳሌ 22፡6ን ይመልከቱ)። ገና በልጅነቱ ውሸትን የተለማመደ ሰው በጌታ ቤት ለመቆየት ሲቸገር ይታያልና። እንደዚያ ዓይነቱ ሰው መላልሶ ኃጢአት እየሠራና ንስሐ እየገባ የእፎይታ (ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የመስማማት) ኑሮ ሳይኖር ከዚህ ዓለም ይሸኛል። «ስለዚህ ሰድዶ ማሳደድ» እንዳይሆንብዎ ልጆችዎን ከእነዚህ የእውነት ተውሳኮች ይጠብቁ።

2. በጎረቤትና በአካባቢ ያለው ውሸት

በድሮ ዘመን በዓለማውያን ባህል ውሸትን እውነት አስመስሎ ተናግሮ ማሳመን፥ በሐሰት መከሮ የአንድን ሰው ጥቅም ማስከበር፥ ዳኛን በገንዘብ ኃይል አሳውሮ ለራሱ ማስፈረድ፥ በጉቦ መበልጸግ፥ ሀብታም የሆነውን ውሸተኛ ደግፎ እውነተኛውን (የተበደለውን) ድሃ ማስረታት... ይህ ሁሉ በፍትሕ አደባባይ እንደ ተፈጸመ ጀብዱ ይቆጠር ነበር።

በዓለማውያን ባህል የሴባ ዋሻ ሆኖ የሀብታሞችን ሀብት ማሰረቅ (ማስዘረፍ)፥ አንዱን ሹም ከሥልጣን ለማስወገድ ገና ሲሾም ጀምሮ ትግል ማካሄድ፥ የጭካኔን ሥራ መሥራት፥ እንዳሻው መሆን፥ ከተሾሙ «አብሱኝ» ማለት፥ ምስኪን ድሃንና አደባባይን የማያዘወትረውን የሥራ ሰው ረግጦ መግዛት የመሳሰሉት አንድን ግለሰብ «ጎበዝ» ያሰኙት ነበር።

ዛሬም ኢየሱስ ክርስቶስን ተቀብለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሕይወታቸው ያልተለወጠ ፍጥረታዊ ሰዎች ብዙዎቹ

ዓላማቸውና ዕቅዳቸው እንደዚያ ለመሆን ነው። ዛሬ ዓለም በጋለ ምጣድ ላይ እንደተጨመረ ማሽላ እየተሸበረ ያለው በዚህ ምክንያት ነው።

ስለዚህ እርስዎ ጌታ ኢየሱስን የተቀበሉና ለአዲስ ሕይወት የሚሆነውን አዲስ ልደት የተቀበሉ ከሆኑ የዚህን ዘመን ክፋት ተገንዝበው፥ እርስዎም ከዓለም ክፉ ሥራ እንዲለዩ የተጠሩ ሰው መሆንዎን ተረድተው ጌታን እያመሰገኑ በጽድቅ ጎዳና እንዲመላለሱ እመክርዎታለሁ። ነገር ግን ዛሬም ያልተለወጡና የእነዚህን ክፋቶች የመጨረሻውን ከፍተኛ ደረጃ ለመድረስ በቆክከር ላይ የሚገኙ ከሆኑ የክፋትና የሐሰት ሁሉ አባት ከሆነው ዲያብሎስ ጋር ዕድልዎ በገሃነመ እሳት እንዳይሆን ሕይወትዎን መለወጥ ወደሚችለው ጌታ በአስቸኳይ ይመለሱ። ክርስቶስ ብርሃኑን ያበራልዎታል። የሚያረካ አዲስ ሕይወትም ይሰጥዎታል። ያውም የዘለዓለም ሕይወትና የደስታ ሕይወት!

3. በገበያና በጉሊት ያለው ውሸት

ሁሉን ከሚያውቅ አምላክ በቀር የሰውን ልብ የሚያውቅ የለም እንጂ ማወቅ ቢቻል ኖሮ በአንድ ትልቅ ገበያ የሞላው ገበያተኛ የተናገራቸውን ውሸቶችና የፈጸማቸውን ማጭበርበሮች ከጠዋት እስከ ማታ ቢመዘግቡት የአንድ ቀኑ ብቻ ከአንድ ትልቅ መዝገብ ሳይበልጥ አይቀርም። ይህ እንግዲህ በጥቅሉ በምድር የሚኖሩ ሰዎች ፈጣሪ አምላካቸውን፥ ከፋትን ሁሉ የሚጸየፈውን ጌታ (ሉቃስ 16፡15) ምን ያህል እያንገሸገሹትና እያስቀየሙት እንደሚውሉ ያሳያል። ዛሬ

ምድር በአለመታዘዝ እንደ ተሞላችና ለመጨረሻ ጥፋትዋ እየተዘጋጀች ለመሆንዋ የሰዎች ባሕርይ እውነተኛ ምስክር ነው (2ኛ ጢሞ. 3፡1–9)።

– አንዳንድ ገበሬ ጆንያው (መስፈሪያው) እንዲሞላ ወይም ሚዛን እንዲደፋለት ሲፈልግ እህሉን በአውድማው ላይ ሳለ በደንብ ሳያጠራ ከነግርዱ ሰፍሮ ሞልቶ ገበያ ያመጣል። ከዚያም «ምርጥ እህል ነው፤ ግዛ!» ይላል። ሸማቹ አግራጭ ስለሌለው ይገዛና ቤት አምጥቶ እንደገና አበጥሮ ካጣራ በኋላ የገዛው መቶ ኪሎ ከሆነ አሁን የተጣራ ሰማንያ አምስት ኪሎ እህልና አሥራ አምስት ኪሎ ዕብቅ (ግርድ) ገዛ ማለት ነው። እህሉ በአጠቃላይ የተገዛው በመቶ ብር ቢሆን በአሥራ አምስት ብር ዕብቁ ተገዛ ማለት ነው።

በገበያ እህል እየገዙ ከሚቸረችሩ ነጋዴዎች አንዳንዶቹ ሁለት ዓይነት መለኪያ (መስፈሪያ) አላቸው። አንዳንዶቹ በትልቅ መስፈሪያ ይገዙና በትንሽ መስፈሪያ በተመሳሳይ ዋጋ ይሸጣሉ። አንዳንዶች ግን መጠናቸው ከውጭ ሲታይ እኩል ሆኖ በውስጣቸው እህል የመያዝ ዓቅማቸው ይበላለጣል። ለምሳሌ በጣሳ (ሰለሞኒ) የሚገዙና የሚሸጡ አንዳንድ ሰዎች ጣሳውን ከቂጡ ወደ ላይ ይመቱና በራሱ ቂጥ ይሞሉታል። ከሌላው እኩል አስመስለው በዚያው ይሸጣሉ። ጣሳውን ቂጡን ወደ ታች ይደቁሱና ከዓቅሙ (ከመጠኑ) በላይ የሆነ እህል እንዲይዝ ያደርጉታል። በዚያ ለራሳቸው ከገበሬው ይገዛሉ። ታዲያ ለሻጩ ምለው ተገዝተው «መስፈሪያዎቹ ፍጹም እኩል ናቸው» ይላሉ። ወይም በሚሰፍሩት ቆርቆሮ ውስጥ የሚያጣብቅ ነገር ያደርጉና እህሉ ሩብ ያህሉ እዚያው ተጣብቆ ስለሚቀር

ሰዎቹ የቆርቆሮውን መልክና መጠን ከውጭ አይተው በደስታ ይገዛሉ። ነገር ግን የገዙት .....! አቤት ውሸት!

በዚህ ዓይነት ሸማቹ ዓይኑ እያየ ተታልሎ በቂ ላልሆነ እህል ገንዘቡን ይከፍላል።

አንዳንድ ባለሚዛኖችም እንደዚሁ ቍጥር አዛብተው ከቁጥሩ ወይንም ከሚዛኑ አስበልጠው ያስከፍላሉ፤ ወይም አሳንሰው ነግረው ይከፍላሉ። ይህ ብቻም አይደለም፤ በተለያዩ የአመዛዘን ሥልቶች አማካይነት ያለሚዛኑ ያስከፍላሉ። አቤት ስንት ውሸት አለ!

በከብት ተራ

አንዳንድ ሰው ለእርሻ የሰነፈ በሬ፥ የምትራገጥና ጡቷ የተደፈነባት ላም፥ የማትወልድ በግ፥ ወልዳ የማታሳድግ ፍየል፥ ሰነፍ አህያ፥ አመለኛ በቅሎ፥ ዳተኛ ፈረስ... በጠቅላላውም ለራሱ አይጠቅሙም የተባሉትን ለሽያጭ ገበያ ያቀርባል። ሲያቀርብ ታዲያ ስመ እግዚአብሔርን ጠርቶ ምሎ «ፍጹም እንከን አይወጣውም፤ ግዛ!»ይላል። ከዚህ የሚብሰው ደግሞ የታመመበትን ከብት እንደምንም ነድቶ አምጥቶ ገበያ አድርሶ፥ አታልሎ በጤነኛ ዋጋ መጠን መሸጡ ነው። ከብቱ ቢሞትበት ባለገንዘቡ መጥቶ እንዳይይዘውና ገንዘቡን በሕግ እንዳይጠይቀው ስሙንና አድራሻውን ቀይሮ ይነግርና ይጽፋል። ወይም ሆን ብሎ የሸያጩን ገንዘብ ይዞ ከአካባቢው ይሰወራል። ስለ አንድ አጭበርባሪ እስቲ ልንገራችሁ፡–

አንዲት ወፍራም ጊደር ይዞ ቆሞአል፤ ያለው በትልቅ ገበያ መሀል በከብት ተራ ነው፤ አንድ የወተት ላም የፈለገ

ሰው መጥቶ «እስቲ ጊደርህን ለእኔ ሽጥልኝ፤ ለመሆኑ ሁኔታዋ እንዴት ነው?» ብሎ ሲጠይቀው፥ አጅሬ አፉን ሞልቶ «ጊደሪቱ እርጉዝ ናት፥ አራት ወርዋን ይዛለች ግዛት» ይላል።

በዋጋ ሳይስማሙ ቀርተው ሰውዬው ከተሰናበተው በኋላ አንድ ለድግስ ሊያርድ የሚፈልግ ሰው ቀርቦ «እስቲ ጃል፥ ጊደርህ እንዴት ነች?። እኔ ለእርድ የሚሆን ከብት እየፈለግሁ ነኝ» ሲል፥ አጅሬው ለቀም አድርጎ «እንዴታ! ይህችማ የስንት ዘመን መሲና ናት። ባስጠቃትም እንቢ ብላ ይኸው 3ኛ ዓመቷን ይዛለች፤ ጮማዋ ሽኗን ዘግቶታል ግዛት! ትሆንሃለች» ይላል።

እንግዲህ የዚህ ነጋዴ ውሸት ምን ይባላል!? እውነትን የሚናገሩ ነጋዴዎች የሉም ማለት አይደለም። ነገር ግን አብዛኛዎቹ ሲዋሹ ታይተዋል። እያንዳንዱ አጭበርባሪ ነገ በተራው ሊገዛ ገበያ ወጥቶ የባሰ በሽተኛ ያጋጥመዋል። ገንዘብን የማይጠግብ ሌላውን ያታልላል ማለት ነው። አንባቢ ሆይ! እርስዎስ ከዚህ ሁሉ ውሸትና ማጭበርበር ነፃ ነዎትን? የተለወጡ ክርስቲያን ከሆኑ ስለዚህ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

«ዘኬዎስ ግን ቆሞ ጌታን፦ ጌታ ሆይ፥ ካለኝ ሁሉ እኩሌታውን ለድሆች እሰጣለሁ፤ ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደ ሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ አለው» (ሉቃስ 19፡8)። ከዚህ ቀደም በሠራው ኃጢአት አዘነ። አሳቡንና ዓላማውን መቀየር ብቻ ሳይሆን ለበደላቸው ሰዎች ካሣ ሊከፍል ጭምር ወስኖ ከፈለ። ራሱ ወስኖ ራሱ ከፈለ ማለት ነው። መለወጥ ማለት እንደዚህ ነው።

«እንግዲህ ፈጽሞ የእርስ በርስ ሙግት እንዳለባችሁ በእናንተ ጉድለት ነው። ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን? ነገር ግን እናንተ ትበድላላችሁ፤ ታታልሉማላችሁ፥ ያውም ወንድሞቻችሁን» (1ኛ ቆሮ. 6፡7-8)።

«ችግረኛን የምትውጡ፥ የአገሩንም ድሀ የምታጠፉ እናንተ ሆይ፦ እህልን እንሸጥ ዘንድ መባቻው መቼ ያልፋል? የኢፍ መስፈሪያውንም እያሳነስን፥ ሰቅሉንም እያበዛን፥ በሐሰተኛም ሚዛን እያታለልን፥ ድሀውን በብር ችግረኛውንም በአንድ ጥንድ ጫማ እንገዛ ዘንድ፥ የስንዴውንም ግርድ እንሸጥ ዘንድ ስንዴውን እንድንሸምት ሰንበት መቼ ያልፋል? የምትሉ.... ዓመት በዓላችሁንም ወደ ልቅሶ፥ ዝማሬአችሁንም ወደ ዋይታ እለውጣለሁ» (አሞጽ 8፡5-10) አለ። በማታለል ለመበልጸግ ለሚጓጉ ወዮላቸው! ለማለት ነው።

አንዳንድ ሸማኔዎች የመጀመሪያውን ዘርፍ (ጅምሩን) በምርጥ ማግ አሳምረው ይሠሩና መሀሉን በመናኛ ማግ ይሠራሉ። ገበያ ሲያቀርቡ ከሩቅ እንዲማርከላቸው መልካሙን ዘርፍ እያሳዩ «ጥራቱ ግሩም ነው! ግዛ» ይላሉ። አብዛኛው ሻጭ በዚህ ዓይነት የሠራ ስለሆነ ከብዙ መጥፎዎች ውስጥ የመጥፎነቱ ደረጃ የሚቀንሰውን መርጦ መግዛት የግድ ይሆናል።

አንዳንድ የቅቤ ነጋዴዎች በቅቤአቸው ውስጥ ቅቤ የሚመስል ሌላ ባዕድ ነገር በውስጡ አድርገው ከላይ ምርጥ ቅቤ ለብጠው በኩባ ግጥም አድርገው ጠቅልለው አስረው ገበያ ያቀርባሉ። ከዚያም «ንጹሕ የወላይታ፥ የቁጫ፥ የቦረዳ ቅቤ ግዙ» እያሉ በውድ ዋጋ ይሸጣሉ። ገዢው ቤት

አድርሶ ውስጡን ሲያይ ሌላ ነገር የተጨመረበትና ሲያቀልጡት ሽታው የሚገማ፥ እጥፍ በነደደ እሳት እንኳ የማይቀልጥ፥ የእስሩ 8/10ኛው ያህል ቆሻሻ ሆኖ ቁጭ ይላል። አሁን ይህ ሰው ቅቤ ገዛ ይባላል!?

አንዳንድ ባለ ሉካንዳዎች ዘንድ ሲሄዱ ብዙ ጉፋያ ከሥር ያደርጉና ጥቂት ጮማ በላዩ ላይ ይደርቡና (ያለብሱና) «ጮማ ብላ!» ይላሉ። ይህ የሚታየው ሁሉ ጮማ እንደሆነ አድርገው እየተናገሩ።

ሽንኩርት ተራ ሲሄዱ ደግሞ አንዳንድ ትንንሽ ራስ ያላቸውን ከሥር አድርገው ትልልቅ ራስ ያላቸውን ከላይ ይደርቡና ያሳያሉ። በአካባቢው ከሚሸጡት ነጋዴዎች በዛ አድርገው ይመድባሉ። ገንዘብ ከከፈሉ በኋላ ወደ ዘንቢል ውስጥ ለመጨመር ለገዢው አይፈቅዱም። በፍጹም በጣቱም አይነካም። «ገንዘብ የከፈልኩበት ነውና እኔ ነኝ ዘንቢሉ ውስጥ መጨመር የሚገባኝ» ካለ ገንዘቡን መልሰው ይሰጡታል። እዚህ ላይ አንድ ምሥጢር አለ። ይሸውም ሻጩ ዘንቢሉ ውስጥ በሚከትበት ጊዜ በሌብነት ሠለጠኑ ጣቶቹ እነዚያን ዓይን የሳቡ ትልልቅ ራስ ያላቸውን ሽንኩርቶች ወደ ዘንቢል የጨመረ እያስመሰለ ወደ ኋላ መልሶ ካልተሸጠው ሽንኩርት ጋር ያስቀምጣል። በዚህ ዓይነት ቅድም ከተመደበው መደብ ግማሽ ያህሉን ለራሱ ያስቀራል። ለመሆኑ ንግድ ማለት ማታለል ማለት ነው ወይ?» እስከ ማለት አድርሶናል።

አቤት ስንት ውሸት አለ!!

ለመሆኑ ውሸተኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት ይወርሳሉን?

«... ውሻዎችና አስማተኞች ሴሰኞችም ነፍሰ ገዳዮችም ጣዖትንም የሚያመልኩት *ውሸትንም የሚወዱና የሚያደርጉ ሁሉ* በውጭ አሉ» (ራዕይ 22፡15)። በዚህ ቃል መሠረት መልሱ «አይወርሱም» ነው።

ስንት ውሸት አለ!? ላምባ ብለው ገዝተው ሽንት ተቀላቅሎባቸው ያፈሰሱ፥ ሥራሥር (ድቡል፥ ድንች፥ ጎደሬ፥ ዋንጫሮ...) ገዝተው ቀቅለው የማይበስል ሆኖ ሳይበሉ፥ የጣሉት፥ ዱቄት ገዝተው የመረረባቸው፥ የጨፍ ዘር ገዝተው ዘርተው ያልበቀለላቸው፥ ወለላ ማር ነው ተብለው ገዝተው ዕቃው ውስጥ ሰፈፍ የተጠቀጠቀባቸው፥ በጠቅላላውም በውሸት ዘመቻ ዋጋ ለማይሆን (ለማይጠቅም) ነገር ገንዘባቸው የተወሰደባቸው ስንቶች ናቸው? በከፍተኛም ሆነ በዝቅተኛ የንግድ ቦታ፥ ሰው በዋለበት መስክና አካባቢ ሁሉ እንደዚህ ያለ ውሸትና ማጭበርበር ያልተፈጸመበት ቦታ ቢኖር በጣም ጥቂት ነው። አብዛኛው ሰው ክፉን በማድረግ አሸናፊ ለመሆን ይሽቀዳደማል ማለት ነው። አንባቢ ሆይ! እርስዎስ ከዚህ የሐሰት ቀለበት ውስጥ አልዝሙም? ካልገቡ፥ ጌታን ያመስግኑ፤ ነፃ ካልሆኑ ግን ዛሬውኑ በአስቸኳይ መንገድዎትን ይቀይሩ። ኃጢአትዎን በመናዘዝ ወደ ጽድቅና ወደ ቅድስና ጉዳና ይመለሱ። ያለ ቅድስና ጌታን ለማየት የሚችል ማንም የለም (ማቴ. 5፡8)።

4. በሱቅ ያለው ውሸት፡-

አንዳንድ ባለሱቆች ደንበኛው የገዛውን ምርጥ ዕቃ ለውጠው መናኛውን ዕቃ ይሰጡታል። እንዲያውም ልብሱን ለውጠውና በተመሳሳይ ጋዜጣ የተጠቀለለ ቡቱቶ ሰጥተውና ሸኝተው፥ ቤቱ ሲደርስ ይህንን ጉድ አይቶ አልቅሶ የተወ ስንትና ስንት ሰው ነው!?

አንዳንዶች የሚመዘኑ ዕቃዎችን ከሚዛኑ ንባብ ቀንሰው ሒሳብ በመሥራት ሒሳብ ይከፍላሉ። ወይም ቁጥር ጨምረው ሒሳብ በመሥራት ያስከፍላሉ። አንዳንዱ በመናኛ ዕቃዎቻቸው ላይ «ምርጥ ዕቃ» የሚል ምልክት ይለጥፉና መናኛውን ዕቃ ምርጡን ዕቃ አስመስለው በውድ ዋጋ ይሸጣሉ። አንዳንድ ነጋዴዎች በአገር ውስጥ የተመረተውን ዕቃ ከውጭ አገር የመጣ ነው ይላሉ። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ውስጥ የሠሩትን ጫማ በኢጣልያ አገር የተሠራ ነው ብለው በውድ ዋጋ ለመሸጥ ይሞክራሉ። አንዳንድ የዕቃ ስሞችንና ምልክቶችን ብቻ ገዝተው አምጥተው በተሠራ ዕቃ ላይ ይለጥፉ ወይም ይሰፉና በውድ ዋጋ ይሸጣሉ። አንዳንድ ነጋዴዎች በመልክ አንድ የሚመስሉ ነገር ግን የተሠሩባቸው ንጥረ ነገሮች የተለያዩ (አንዱ መናኛ ሌላው ጥራት ያለው) ዕቃዎች ከሱቆቻቸው በፍጹም አያጡም። የአንዳንዶቹ አሳብ ታዲያ መናኛውን በውድ ዋጋ ለመሸጥና ገንዘብ ለመሰብሰብ እንዲመቻቸው ነው።

ሊቀየጡ የሚችሉ ዕቃዎችን (እህል፥ ሽሮ፥ በርበሬ) ንጹሑን ንጹሕ ካልሆነው ጋር አቀላቅለው ንጹሑ በሚሸጥበት ዋጋ ይሸጣሉ። ለአካባቢው እንግዳ የሆነን ዕቃ ሲያስተዋውቁ ዋጋውን ብዙ ዕጥፍ ጨምረው

ያስተዋውቃሉ። ለምሳሌ የዲስኮ ሰዓት ዛሬ ከአሥር ብር በታች የሚሸጠውን በብር 170 (አንድ መቶ ሰባ ብር) የሸጡበት ጊዜ አለ። የአንዳንድ ነጋዴዎች ዓላማ ከአገልግሎታቸው ጋር የተመጣጠነ ትርፍ ወስደው ደንበኞችን በትሕትና ማስተናገድ ሳይሆን በተቻለ መጠን ትርፍ ለማግኘት ብቻ መዋሸት ነው። ሃያ ብር ለሚያወጣ ዕቃ አርባ አምስት ብር መጠየቅ የተለመደ ሆኗል። መቼም በዚያ ዓይነት ሙያ የተካነና ትክክለኛ ዋጋውን የሚያውቅ ሰው ካልሆነ ሱቅ ሄዶ ወይም ገበያ ሄዶ ዕቃ መግዛት ከማይቻልበት ደረጃ እየተደረሰ ነው። ለዚህ ማስረጃው የአሻሻጮች (የደላሎች) መብዛት ነው። የሻጭ አሳብና የገዢ አሳብ በጣም እየተራራቀ ከመሄዱ የተነሣ ሁለቱን ወገኖች መዋጮ ጠይቆ የሚሠራ የደላላ ድርጅት አሠራር ከተከሠተ ውሎ አድሮአል።

አቤት ስንት ውሸትና ማጭበርበር አለ?

እንዲህ ያለው እውነትን ለመናገር እስኪያቅት ድረስ የሚዋሹና የሚያጭበረብሩ የማያምኑ ሰዎች ብቻ ቢሆኑ ኖሮ እጅግም የሚያስደንቅ ባልሆነም ነበር። ምክንያቱም እነርሱ ጌታን አያውቁም፤ አይፈሩትም፤ አያከብሩትምም። እነርሱ የገዛ ስሜታቸውን ተከትለው እንዲሁ ይኖራሉና። ነገር ግን ይህንን ስሕተት ከሚፈጽሙት መካከል «እኔ አማኝ ነኝ፤ ክርስቶስን አውቃለሁ፤ እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኛለሁ። የሚሉ ክርስቲያኖች መገኘታቸው ነው። እነርሱ ራሳቸው የገዛ ወንድሞቻቸውንና እኅቶቻቸውን ሲያታልሉና ሲያጭበረብሩ ማየት ምንኛ ያሳዝናል። ለመሆኑ እርሷ (እርሱ) የክርስቶስ ቤተሰብ ነች (ነው) ወይ? ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን።

እንግዲህ እነርሱ «ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም» (ማቴ. 5፡20) የሚለውን የጌታ ቃል ንቀው «ብልጠታችሁና ንቃታችሁ ከዓለማውያን ብልጠትና ንቃት ካልበለጠ በዚህ ዓለም ላይ ከብራችሁ መኖር አትችሉም» የሚለውን ጣፋጩን ሰይጣናዊ ምክር አክብረው ይቀበላሉ። ዛሬ የዓለም ሰዎች (አሕዛብ) በጥበብና በተንኮል እንዳይበልጡን ያደረግነው እሽቅድድም ከእነርሱ የበለጥን ተንኮለኞች፥ ኃጢአተኞችና ከሐዲዎች እንድንሆን አድርጎናል (ኤር. 4፡22)። እርስዎስ ከዚህ ዓይነት ሕይወት ነፃ ነዎትን? ካልሆኑ ዛሬውኑ ለምን አይመለሱም? ልብዎንና እጅዎን ለክርስቶስ በማንሣት ተናዝዘው አሁኑኑ አሳብዎን ይለውጡ። በመንፈስ መታደስ ይለወጡ እንጂ ይህንን ዓለም አይምሰሉ (ሮሜ 12፡2)።

በግል ሥራ በሚተዳደሩ ሰዎች ሁኔታ ላይ ተጨማሪ

አንዳንድ ስግብግብ አናጢዎች በአካባቢያቸው አንድ የሚሠራ ሥራ ኖሮ ሲጠሩ አስቀድመው ቀብድ ይወስዳሉ፤ ይህንን ሥራ ፈጽመው ሳያስረክቡ ለሌላ ሥራ ሌላ ቀብድ ይወስዳሉ። ይህንንም ሳያጋምሱ ለሌላ ሥራ ቀብድ ይወስዳሉ። እንደዚህ እያደረጉ አንዱንም ሳይጨርሱ ዓመት ሙሉ ይፈጃሉ። ቢለመኑ፥ ገንዘብ ቢጨመርላቸው፥ በሕግ ቢከሷቸው እንቢ ብለው በመጨረሻም የማይረባ ሥራ ሠርተው ይተውታል።

ስንቱ የጭቃ ሠራተኛ ነው ቀብድ በልቶ ለጭቃ የቆፈረውን ዐፈር ከዚያው ኩይሳ አድርጎ ያልጠፋ? ስንቱ ብረት ሠራተኛ ነው ሥራ ተብሎ የተሠጠውን ልዩ ልዩ የብረት መቆፈሪያ፥ ማጭድ፥ ዶማ፥ ጦድራ... ሠርቶ ሲያበቃ ለባለንብረቱ በመስጠት ፈንታ ገበያ አውጥቶ ሸጦ ያልበላ? ሲጠየቅ ግን «ገና ነው፤ ነገ ሠርቼ አስረክባለሁ» ይላል። ከዓመታት በኋላም «ነገ» ይላል። ሰው መመላለሱ ካልሰለቸው እርሱ መዋሸቱ አይሰለቸውም።

አቤት ውሸት!

ስንቱ ሸክላ ሠሪ ነው የተሰነጠቀውን ዕቃ ባለው ችሎታው ደህና አስመስሎ ለብጦ ያልሸጠ? ለአንድ ቀን እንኳ ሳያገለግል ገል ሆኖ ይቀራል። ታዲያ እርሱ «ደህና አድርጌ በላሁት!» ይላል።

አንዳንድ ሊስትሮም ጫማ ሲጠርግ አስጠራጊው ትኵረት ሰጥቶ ካልተቆጣጠረው ቀለም ሳያስነካ ይወለውልና «ቦቃ ክፈል» የሚል የቆርኪዎች ድምፅ ያሰማል።

አንዳንድ ባለ ወፍጮዎች የቀረበላቸውን እህል ሲመዝኑ ቁጥር አመልካቹ የሚዛን ምላስ ገና ቁጥሩ ላይ ሳያርፍ በፍጥነት በመመለስ ከእህሉ የበለጠ ቁጥር ነግረው ያስከፍላሉ። ወፍጮው እህል እያደቀቀ እያለ ጊዜና ነዳጅ እንዳይፈጅባቸው መቆጣጠሪያውን ያላሉና ሽርክት ያወርዳሉ።

የቅጥር ሠራተኞችን ሁኔታ በተመለከተ

እስኪ ደግሞ እንግዲህ በግል ሥራ ከሚተዳደሩ ሰዎች ወጣ ብንል ተቀጥረው ስለሚሠሩ ሰዎች ጥቂት እንመልከት፡-

ብዙ ሥራ ያጡ ሰዎች ሥራን ይፈልጋሉ። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ሥራን ሲያገኙ ግን መሥራት አይፈልጉም። ቀድሞውኑ ሥራን የፈለጉ አይመስሉም። ይህ ማለት በሥራ ገበታ ላይ ይሰየማሉ፤ ደመወዝ፥ የደረጃ ዕድገት፥ የሠራተኛ መብት፥ የሥራ ቦታዎች፥ ደኅንነት፥ ከሁሉም የተሻለና ምቹ ቦታ እንዲሁም ኃላፊነት ተሰጥቷቸው ማዘዝ ይጀምራሉ። ይህንንም እንደ ሥራ ይቆጥሩትና በተመደቡበት ሥራና ኃላፊነት መለገም ይጀምራሉ። መፈጸም ያለበት ተግባር መኖሩንም ይዘነጋሉ። «ፊትን ማስገረፍ፥ አለቃን መያዝ፥ ከምላሳቸው የማር ወለላን የመሰለ ንግግር ማንጠባጠብ፥ ራስን በራስ ማሞጋገስ፥ ያልሠሩትን ማውራትና መዋሸትን» ሥራቸው ያደርጋሉ። ይህንን ለምደው ለአካባቢያቸውና ለአገራቸው ዕድገት፥ ለሃይማኖታቸውና ለጌታቸው ክብር ምንም የማይረቡ ከንቱ ሰዎች ይሆናሉ። ሲቀጠሩ የተናገሩትን ቃልና የገቡትን ውል በመተው ይዋሻሉ። የሥራ ሰዓት መስረቅ፥ ሳይቸገሩ ቸገረኝ ማለት፥ ከሚዋሹ ሰዎች ጋር ተመሳጥረው ሳይታመሙ የሐኪም ማስረጃ ማውጣትና ለአለቃ ማቅረብ፥ በተቻለ መጠን ደመወዝ እንዳይቆረጥ ልዩ ልዩ ውሸቶችን መዋሸት የሚያዘወትሩ ሰዎች ጥቂቶች አይደሉም። እሠራለሁ ያሉትን ወይም በመንግሥት የተደነገገውን ያህል ሰዓት ሳይሠሩ ወይም እፈጽማለሁ ያሉትን ተግባር ሳይፈጽሙ ያንን የተመደበውን ገንዘብ መውሰድ ማጭበርበር ወይም መዋሸት አይመስላቸው ይሆን?

አቤት ስንት ማጭበርበር አለ!

እርስዎስ ከዚህ ነፃ ነዎትን? እርስዎም ድንገት ጌታ ሳይመጣብዎ ወይም ተራዎ ደርሶ ከመወሰድዎ በፊት

ይታረሙ። የእያንዳንዱ አማኝ ሥራ በእሳት ስለሚፈተን በዚያ ቀን የሚቃጠልብዎን ሥራ እየሠሩ መሆንዎን ይገነዘባሉ? እምነት (ሃይማኖት) በየዕለቱ በምንፈጽመው ተግባር የሚንፀባረቅ መለኮታዊ ባሕርይ እንጂ በእምልኮ ቀን ለብሰነው የምንወጣ ‹ዩኒፎርም› አይደለም።

አንዳንድ የሥራ ኃላፊዎች ደግሞ ኃላፊነታቸው ከሰውና ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው አደራ መሆኑን ይዘነጋሉ። «ሲኖም ያልበላ ሲሻር ይቆጪዋል» ከሚሉ ውሸተኞች ጋር ይስማማሉ። በኃላፊነታቸው ምክንያት እንዲያንቀሳቅሱት በእጃቸው የገባውን ገንዘብና ንብረት በተቻለ መጠን ለራሳቸው ለማድረግ ጥረት ያደርጋሉ። እንደ ምንም አድርገው ሒሳብ ለማወዳደቅና ገንዘቡን ከያዘው ሰው ጋር ተመሳጥረው ለመብላት ሽርጉድ ይላሉ፤ ወይም አስቀድሞ ከበላው ሰው ጉቦ ይበሉና ሒሳቡ እንዳይጣራ ጋሬጣ ይሆናሉ። ሐሰተኛ ደረሰኝ (የወጪ ማስረጃ) እየፈጠሩ ገንዘቡን ሙልጭ አድርገው ይጨርሱታል። ሰው ደርሰባቸው ካልወቀሳቸው እግዚአብሔርም በዚህ ድርጊታቸው የተስማማ ይመስላቸዋል። አንዳንድ ስግብግብ ዕቃ ሻጮች ብዙ የድርጅት ዕቃ ገዢዎችን ደንበኞቻቸው ለማድረግ ጓጉተው የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄ ሰምተዋል? እንበልና ገዢው የ100 ብር ዕቃ ከገዛ በኋላ ደረሰኝ ለመጻፍ ሲነሡ «ስንት ብዬ ልጻፍ?» ይላሉ። ወይም ማጎተምና ፊርማቸውን አኑረው ባዶ ደረሰኝ ቆርጠው ይሰጣሉ። በዚያም ከሽያጩ ውጪ የ «ወጪ» ይሰጧቸዋል። ያለድካም ለመበልጸግ የሚፈልጉ አንዳንድ ዕቃ አቅራቢዎችም እንደዚያ ዓይነቱን ሰው ይወዳሉ። ሊገዙ የፈለጉት ዕቃ እርሱ ዘንድ ሳይሆን ሌላ ቦታ ቢኖርም እንኳ ከተማ ውስጥ የዚያ ዓይነት ዕቃ

እንደሌለ አለቆቻቸውን ለማሳመን ይሞክራሉ። ይህ እንግዲህ የሕዝብን ወይም የድርጅትን ገንዘብ ሁለቱም ወገኖች እንክት አድርገው ለመብላት መቋመጣቸውን ያሳየናል። ጥቅስ ይዞ የሚመጣውን ሰይጣን ሳይጠራጠሩ፥ ወደ ኋላም ሳያፈገፍጉና ቅርም ሳይላቸው ያስተናግዳሉ።

የጌታን ቃል ችላ የሚሉ አንዳንድ ክርስቲያኖች የዚህን ዓይነት ነውረኛ ረብ መቀበል ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ሥራ ብለው ከዚያ አሥራትና ምጽዋት ይሰጣሉ። በዚያም ራሳቸውን በብርቱ ክርስቲያኖች ቊጥር ያስገባሉ። «እግዚአብሔር ምን ይለኛል?» ከማለት ይልቅ በአካባቢው ካለው ኀብረተሰብ ጋር ተመሳስሎ መኖርን እንደ ትልቅ ሃይማኖት (እምነት) አድርገው ይቆጥራሉ። አቤት ውሸት! ለሰውም ለአምላክም መዋሸት!

ስለዚህ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

«እግዚአብሔር ሆይ! ከሐሰተኞችና ከአታላዮች አድነኝ። እናንተ አታላዮች! እግዚአብሔር እናንተን ምን ቢያደርጋችሁ ይሻላል? እንዴትስ ቢቀጣችሁ ይሻላል? በተሳለ የወታደር ፍላጻ ይውጋችሁን? በከሰል ፍምስ ያቃጥላችሁን? ከእናንተ ጋር መኖር በሚሺክ ወይም በቄዳር ሕዝብ መካከል እንደ መኖር አስከፊ ነው። ሰላምን ከሚጠሉ ሕዝቦች ጋር ለረዥም ጊዜ መኖር ሰለቸኝ። እኔ ስለ ሰላም በምናገርበት ጊዜ እነርሱ ስለ ጦርነት ያወራሉ» (መዝ. 120፡2–7፥ በአዲስ ትርጉም) ይላል። ውሸትና ማጭበርበር ባለበት ቦታ ሰላምን አገኛለሁ ብሎ መጠበቅ ከንቱ ልፋት ነው።

አንዳንድ ሰዎች ውሸት ለማቀነባበር ጊዜ አይፈጅባቸውም። ለምሳሌ ለባሏ የማትታመን ሴት በድንገት ስትጠየቅ ቅጽበታዊ የሆነ የውሸት መልስ ትሰጣለች። ማምለጫ መልሱን በዚያ ቅጽበት ብዙም ሳይጨነቁ በአፋቸው የሚያኖረው ማን ይመስልዎታል? መንፈስ ነዋ! ያ ርኩስ የዲያብሎስ መንፈስ።

ስንቱ ተነግሮ ስንቱ ይቀራል! በመኪናዎች፥ በአየርና በመርከብ ስለሚሠሩ ሰዎች፥ በጤና፥ በትምህርት፥ በአስተዳደር፥ በሰላም ጥበቃ፥ በሕግና ፍትሕ... ወዘተ በሚሠሩ ሰዎች መካከል ስላሉ አንዳንድ ውሸተኞች ሁሉ ለመናገር ጊዜ መች ይበቃል? ለመጻፍም ጊዜም ወረቀትም አይበቃም።

ቤት በትንሹም ውሸት! በትልቁም ውሸት! በድሀውም ውሸት! በሀብታሙም ውሸት! በከተማው ውሸት! በገጠርም ውሸት! በቆላም በደጋም ውሸት! በቀጣሪም በተቀጣሪም ውሸት! በአለሪም በሠራተኛም ውሸት!! የሰይጣን ውሸት ምድርን አጥልቀለቀ!!

መጽሐፍ ቅዱስ ግን «... እርስ በርሳችሁ ውሸት አትናገሩ፥...» ይላል።

ውሸተኞች እነማን ናቸው?

ይህ እንግዲህ «ሥራዬ» ብለው የሚሰርቁትን የለየላቸውን ሌቦች፥ ቤት የሚሰረስሩትን፥ ኪስ የሚያወልቁትን፥ ከብቶችን ከበረት የሚነዱትን፥ ከማሳ የሚቀጥፉትን፥ ማጅራት መቺዎችን፥ ዘራፊዎችንና በሐሰት የሚከሱትንና የሚመሰክሩትን ሳይጨምር፥ «ጨዋ» በሚባሉ

«ሰላማዊ» ሰዎች የሚፈጸም ማታለል፤ ውሸትና ማጭበርበር ነው።

ሰው ለምን ይዋሻል?

እንደምናውቀው ውሸት ከእውነት ጋር መስማማት የለውም (1ኛ ዮሐ. 5፡1)። ከፍ ብለን እንደተመለከትነው የዚህ ሁሉ ውሸት መነሻ ምክንያት «ያለ ድካም እህል እጠግባለሁ፤ ያለ ችግርና ብዙ ውጣ ውረድ እበለጽጋለሁ» የሚል ምኞት ያላቸው ሰዎች ናቸው።

ጌታ ሲያዝ፥ ሠርተህ በላብህ እንጀራህን ብላ (ዘፍጥ 3፡19) አለ። ሐዋርያው ጳውሎስ የጌታን ቃል በማሳሰብ «ሊሠራ የማይወድ አይብላ» አለ። እነርሱ ግን ይህንን መለኮታዊ ቃል በመቃረን የብልጽግናን (የጥጋብን) አቋራጭ መንገድ በመፈለግ ላይ ናቸው። ለመሆኑ ይህ ውሸት ሁሉ ከየት እንደሚነሣ ያውቃሉ?

በመላው ዓለም እንደ የሰው ሥልጣኔና እንደ ኑሮ ደረጃው በምድር፥ በባሕርና በአየር በመስፋፋት ላይ ያለው ይህ ውሸትና ማጭበርበር ያለ ምንም አንቀሳቃሽ ኃይል የሚነሣ አይደለም። የዓለም ገዢ የተባለው የውሸት ሁሉ አባት የሆነው (ዮሐ. 8፡44) ሰይጣን የዚህ ክፉ ተግባር አንቀሳቃሽ ኃይል ነው። ምንም ዓይነት የዕድሜ፥ የዜግነት፥ የማዕረግ፥ የጾታ... ወዘተ ልዩነት ሳይኖር ሰዎች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ለዚህ የርኩስ መናፍስት አለቃ ይታዘዛሉ። እየዋሹም ተልእኮውን ይፈጽሙለታል። ይህ ውሸታቸው ከሚነቃባቸው ወይም ከሚጠቀስባቸው ሞትን ይመርጣሉ። እነርሱ በወቀሳ አዕምሮአቸውን ከማቊሰል ስለ ፈጸሙት

የውሸት ተግባር አንሥቶ የሚያጋልጥ ሰው (ቢደመሰስ) ደስታቸውን አይችሉትም።

እንደነዚህ ዓይነቶቹ ውሸተኞች ሰው ባያያቸው፥ ሌሊት ባይነጋላቸው፥ ሕግ ባይኖራቸው ይመርጣሉ። ቅዱስ መጽሐፍ እነርሱን «... ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለወደዱ...» (ዮሐ. 3፡19) የሚለው ለዚህ ነው።

ውሸት ያልደረሰበት ቦታ ይኖር ይሆን?

በዓለማችን የሚዋሹ ሰዎች በዝተዋል። ምንም ዓይነት የርዕዮተ-ዓለም አመለካከት፥ የሃይማኖት ጎራ፥ የአገርና የአህጉር ወሰን አልገደባቸውም። በክርስቶስ አምነው ለጋጢአት ሞተው ለጽድቅ ሕያዋን የሆኑ ካልሆኑ፥ በክርስቶስ በርግጥ አዲስ የተወለዱ ካልሆኑ (ካልተለወጡ) በአዳማዊ ተፈጥሮ ከውሸት ነፃ መሆን አይቻልም።

መዋሸት፥ ማታለልና ማጭበርበር ምድሪቱን ሣር እንዳለበሳት ያህል አጥለቅልቋታል። ሰይጣን የውሸት ሁሉ አባት የምድር ገዢ የተባለበት ምክንያት እነዚህን መሣሪያዎች በማንም ላይ ያለ ገደብ ስለሚጠቀም ሳይሆን ይቀራል?

ክርስቲያን ነን የምንል ሁሉ አዘውትረን የምናታልል፥ የምናጭበረብርና የምንዋሽ ከሆነ አባታችን ሌላ፥ ስማችንም ሌላ መሆኑን እንዘነጋ። ከመጨረሻው ሐፍረት ጌታ ይጠብቀን።

ዘመኑ ከውሸተኞችና ከእውነተኞች ማናቸውን ያከብራል?

የሚዋሹና የሚዋሹትን በግዴታም ሆነ በውዴታ የሚደግፉ ሰዎች ስለ በዙ እነዚህን ርኩስ ባሕርያት የሕዝብ ባህል እየሆኑ ሄደዋል። (በውዴታ፡– አብረው ጥቅምን ለመጋራት ነው። በግዴታ ቂም፡– ይዘውባቸው በሌላ አጋጣሚ እንዳይጎዱቸው በመፍራት ነው።) ከዚህም የተነሣ ሌባ ሲሰርቅ አይቶ የጠቆመ፥ የዋሹትን ወይም ሐሰት የተናገሩትን ያጋለጠ፥ እንዲሁም እውነትንና ታማኝነትን ሙጭጭ አድርጎ የያዘ ሰው–ባለጌ፥ አላዋቂ፥ የኅብረተሰብን አሳብ ያልተከተለ፥ ጊዜ በላፈበት ዘይቤ የታሠረ፥ ከሥልጣኔ በፊት በነበረው አስተሳሰብ የታጀለና ወግ አጥባቂ በመባል እየተተቸበት ነው። ለምን ይመስልዎታል? ሰው ሁሉ በዚህ ዓይነት ዐመጽ እንዲሞላና የእግዚአብሔርን ቍጣ አነሣሥቶ እንዲቀሠፍ ሰይጣን ስለ ወጠነው ነው። ለዚህ ግቡም ሰውን ሁሉ ልቡን አጥፍቶ በማስቸኮል ላይ ይገኛል። ሰው በቅድስና ጎዳና መሄዱ ቀርቶ በልቡም ስለ ቅድስና እንዳያስብበት ልቡን ያሳውራል። ስለ ቅድስና መንገድ ኢሳይያስ የተነበየውን (35፡8–10 በአዲስ ትርጉም) ይመልከቱ። « ‹የቅድስና መንገድ› የተባለ አውራ ጎዳናም በዚያ ይኖራል፤ በዚያም መንገድ ኃጢአተኛ አይራመድበትም፤ አሳሳቾችም አይገኙበትም። አንበሶችም ሆነ ነጣቂ አውሬዎች በዚያ አይገኙም፤ በዚያ መንገድ የሚመላለሱ እግዚአብሔር የታደጋቸው ወገኖች ብቻ ይሆናሉ» (ቁጥር 8–9)። እግዚአብሔር የታደጋቸው ሰዎች ከቅድስና ጎዳና ውጭ አይመላለሱም ማለት ነው።

ከሕይወት ዛፍ ፍሬ ለመብላትና በደጃፎችዋም ወደ ከተማይቱ ለመግባት መብት እንዲኖራቸው ልብሳቸውን ያጠቡ ዕድለኞች ናቸው። ነውረኞች ... ውሸትን የሚወዱና የሚናገሩ ሁሉ ከከተማይቱ ውጭ ይሆናሉ (ራእይ 22፡14–15)። በክንቱ እየገሠገሡ እንደሆነ አስተውለዋልን? ለመታደግና ልብስዎን ለማጠብ እርግጠኛ ነዎትን? እስካሁን የሰይጣንን ምኞት እያስተናገዱና በውሸትና በነውረኛ ነገር እየተጨማለቁ ከሆነ ክርስቶስን ወደ ልብዎ መቀበልዎና ለደኅንነት በሚያበቃዎት እምነት ውስጥ መሆንዎ ያጠራጥራልና አቋምዎን መርምረው አሁኑኑ ንስሐ ይግቡ። የሰይጣን አንዱ ዘዴ አምኖ የዳነውን ሰው «አልዳንክም» ብሎ በማጠራጠርና በማስፈራራት ሰላም ማሳጣት ሲሆን፥ ያላመነውንና ደኅንነት ያላገኘውን «ድነሃል፤ ጻድቅ ነህ፤ ከሌሎች ትሻላለህ /ትሻያለሽ/» ብሎ ማወናበድ መሆኑን ይገንዘቡ። ስለዚህ የማንነትዎን ምሥጢር በትክክል እንዲረዱና ለመንግሥተ ሰማይ እንዲበቁ ጌታ ይርዳዎት።

5. ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ውሸት

ውሸት በቤተ ክርስቲያን አምልኮ ውስጥ መገኘቱ ግን ከሁሉም እጅግ የሚያሳዝን ነው። ሌሎች እግዚአብሔርን በተዘዋዋሪ ማለትም ለሰው በሚፈጽሙት በደል በኩል ይበድሉታል። በቤተ ክርስቲያን የሚዋሹት ግን እግዚአብሔርን በቀጥታ ይበድሉታል። እግዚአብሔር ሳይናገራቸው «እግዚአብሔር በሕልም፥ በራእይ፥ በመገለጥ ተናግሮኛል» እያሉ ይዋሻሉ። በልባቸው ያሰቡትን መልእክት ያስተላልፋሉ። ለራሳቸው ሥጋዊ ፍላጎት የሚያስቡትን፥ ለምሳሌ አንድን ሀብታም «ይህንን ያህል ገንዘብ እንድትሰጠኝ ጌታ ልኮኛል፤ ካልሰጠኸኝ እግዚአብሔር መቅሠፈት ይልክብሃል» ይላሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ «እኔ እንዳገባሽ (እንዳገባህ) እግዚአብሔር አመልክቶኛል፤ እንቢ ብትይ ወይም ብትል

ትሞቻለሽ/ትሞታለህ/» ወዘተ እያሉ ግለሰቦችን እያስቸገሩ በጌታ ስም ያስፈራሩዋቸዋል በዚያም አሳባቸውን ይፈጽሙባቸዋል።

አንዳንዶቹ ደግሞ ለእንግድነት በሄዱበት ወይም በተጠሩበት አካባቢ ያዩትን አዲስ ነገር ሁሉ ወይም እንግዳ ሆኖ ወደዚያ አካባቢ የመጣ ሰው ሲያደርግ ያዩትን እንቅስቃሴ ሁሉ ሳይመረምሩ ማለትም ድርጊቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆን አለመሆኑንና የአድራጊው ክርስቲያናዊ (መንፈሳዊ) ሕይወት እንዴት እንደሆነ ምንም ሳይረዱ ድርጊቱን እንዳለ እየቀዱ ያልሆኑትን ሆነው (መስለው) ለመገኘት ይጥራሉ። እንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ይህንን እንደ አዲስ በረከትና በቀላሉ እንደማይደረስ ዕድገት አድርገው ስለሚቆጥሩ ሰው ሁሉ እንደ እነርሱ እንዲሆን ይጨቃጨቃሉ። ትንሽ የሚያንገራግር ካለ መንፈስ ቅዱስ በዘመኑ (?) የሚያደርገውን እንቅስቃሴ የሚቃወም ሰው አድርገው በጅምላ ይኮንናሉ።

ይህ ብቻም አይደለም። እንደ አይሁዶች በየዕለቱ አዲስ ነገር (ተአምር) ከላይ ለማየት ይናፍቃሉ። እግዚአብሔር በሰማይና በምድር በየዕለቱ እንደ በጎ ፈቃዱ በሚያደርገው ነገር (ዓቅማችን ማድረግ፥ አዕምሮአችን ማሰብ በማይችለው፤ ነገር ግን በየዕለቱ በሚያስፈልገን ነገር) ሁሉ እያስደነቀን መሆኑንና ለዚህ በቂ ምሥጋና ልናቀርብ ያልቻልን መሆናችንን አያስተውሉም። እንደነዚያ ዓይነቶቹን ሰዎች ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «መቼም አይሁዳውያን ተአምር ማየትን ይፈልጋሉ፤ ግሪካውያን ደግሞ ጥበብን ይሻሉ። እኛ ግን ክርስቶስ ስለ እኛ መሰቀሉን እንመስክራለን...» ብሏል (1ኛ ቆሮ. 1፡22–23 በአዲሱ ትርጉም)።

እንደ ጳውሎስ ዘመን አይሁዶችና ግሪኮች ዛሬም በሴቱ ክርስቲያን ውስጥ ድንቅና ተአምር (በተለይም አካላዊ) ካልታየ የምሥራቹ ቃል የማያረካቸው ሰዎች እየበረከቱ ናቸው። በመታዘዝ በሚገኝ ደስታና በክርስቶስ ዘላለማዊ ፍቅር እየረካን እንደ ፈቃዱ ብንኖር አይሻልምን? ደግሞም እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን እኮ ነው ውጤት የምናገኘው (1ኛ ዮሐ. 5፡14)። ከፈቃዱ ውጭ የምንለምነው ነገር ዳቦ መሆኑ ቀርቶ ድንጋይ፥ ዓሣ መሆኑ ቀርቶ እባብ ሊሆንብን እንደሚችል መገንዘብ ይኖርብናል።

አንዳንድ ሰዎች በምድር ላይ ሰዎችን እያታለለ ያለ ሌላ መንፈስ መኖሩን ለማመን ይቸገራሉ። ራሳቸውን መለኮታዊ ኃይል የተገለጠባቸው ፍጹም መንፈሳውያን አድርገው ሲ`ጥሩና ሌሎችን በጣም ዝቅ አድርገው ሲመለከቱ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች በብዙ ሕዝብ ፊት እንደ ዕብድ ሲሮጡ፥ ወድቀው ዐረፋ ሲደፍቁና አጋንንት ወትውተው እያስጮ኿ቸው ሲወጡላቸው ታይተዋል። ነገር ግን አንዳንድ ችኩሎች ይህንን እያዩም እየተነገራቸውም በ... ስም!! እያሉ መካሪዎችን እያወገዙ ልምምዳቸውን ከመቀጠል በቀር ትንሽም አያስቡም።

ሐሰተኞች በምን ይታወቃሉ?

በእርግጥ ሁሉም እንቅስቃሴ ውሸት ነው ወይም ማስመሰል ነው፤ ወይም ከሐሰተኛው መንፈስ የተቀነባበረ ተንኮል ነው ብሎ ለመደምደም የሚደፍር ሰው አይኖርም። ምክንያቱም ጊዜ፥ ቦታና ሁኔታ የማይወስነው መለኮታዊ ኃይል አይሠራም ማለት ትልቅ ስሕተት ነው። የአንዳንድ ሰዎች የልፋት ውጤትና የሕይወታቸው ምስክርነት ሲታይ

ግን በቅዱስ መጽሐፍ ከሰፈረልን እውነት ጋር አይገጣጠምም። ይህም የእነርሱን ማንነት ስለሚጠቁም ዛፉን በፍሬው ከማወቅ የተሻለ ማስረጃ አያሻንም።

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የሚገለጥብን ሰዎች ለመሆን ልምምድ ያስፈልገናል ወይ?

«ልምምድ» የሚለው ቃል አንድን ሥራ ወይም ማንኛውንም ተግባር ደጋግሞ በመሥራት መሠልጠንንና የዚህ ጉዳይ ኤክስፐርት መሆንን የሚያመጣ አካላዊና አዕምሮአዊ እንቅስቃሴ መሆኑ የታወቀ ነው።

ወደ መንፈሳዊ ትርጉም ሲመጣ ጌታ ስለ ክብሩና ስለ ፍቅሩ ካዘዛቸው ትእዛዞች በታደሰ አዕምሮአችን ምድብ ምድብ ቦታቸውን በማስያዝ፥ ማድረግ የሚገባንን በማድረግና ማድረግ የማይገባንን ባለማድረግ አካላዊ እንቅስቃሴአችንን መግራት ማለትን ያጠቃልላል።

በዚህ አንፃር በልሳን መናገርንና ትንቢት መተንበይን፥ ከሌሎች ሰምተው፥ የሰሙትንም መላልሰው ተናግረው በመለማመድ በቤተ ክርስቲያን ወይም በክርስቲያኖች ስብሰባ ቦታ ያንን ለማሰማት የሚሞክሩ ሰዎች መኖራቸው ያስደንቃል። እነዚህን መንፈሳዊ ተግባራት በተውሶ ወይም በልምምድ የፈጸሙ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነበሩ ወይ? የጥንቶቹ ነቢያትም ሆኑ ሐዋርያት እነዚህን መንፈሳዊ ምግባሮች «ከማድረጋቸው በፊት ልምምድ ወስደዋል» የሚል አልተጻፈም።

ለምሳሌ የሐዋርያት ሥራ 2፡1 ላይ «በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው

አብረው ሳሉ፥ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥... በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥... በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር» ይላል። የድምፁ መምጣት፣ የመንፈስ ቅዱስ መሞላትና በሌላ ልሳኖችም መናገር ሁሉ በልምምድ የተገኘ ውጤት ሳይሆን በአምላክ በጎ ፈቃድ የተሰጠ ችሮታ ነበር። በሐዋርያት ሥራ 10፡17 እንደተመለከተው ቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላትና በልሳን ለመናገር ልዩ ልዩ ሥልጠና አልወሰዱም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደዚህ ያሉ ብዙ ቦታዎች አሉ።

ነገር ግን በዚህ ዘመን ፊደላት ወይም ቃላት መርጠው ሰጥተው እነዚያን ቃላት በጣም በፍጥነት፥ ልባቸው እስኪጠፋ ድረስ ደጋግመው እንዲሉ አድርገው፥ ያ ሰው እንደዚያ እየደጋገመ እያለ ጆሮባውን ተጭነው እያርገበገቡ ማሠልጠን፥ ሰው በመንፈስ ቅዱስ የሚሞላበት ዓይነተኛ ዘዴ አድርገው የወሰዱ ብዙዎች ናቸው። ብዙዎችም በዚህ ዘዴ በአንዳንድ ቦታዎች እያሠለጠኑ ይገኛሉ።

እኔ ይህንን የጻፍኩት ሰው በመንፈስ ቅዱስ የሚሞላበትና በልሳን የሚናገርበት ሌላ ዘዴ አለ ብዬ ለመናገር ሳይሆን– አንዳንድ ራሳቸውን በጣም መንፈሳውያን አድርገው የሚ`ጥሩ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተገለጠውን ዘዴ እያመጡ ሰዎችን እያታለሉ መሆናቸውን ለመግለጽና ለማስጠንቀቅ ነው። የእግዚአብሔር መለኮታዊ ሙላት በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳለና የክርስቶስ አሳብም አጽናኝና አስተማሪ በሆነው ቅዱስ መንፈሱ አማካይነት በቅዱሳን በኩል በቅዱስ መጽሐፉ የተመዘገበ በመሆኑ፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት

ጋር በማይጣጣሙ መገለጦች ላይ ምርመራ እንድናካሂድ ተመከረናል። 1ኛ ዮሐንስ 4፡1 እንደዚህ ይነበባል፡– «ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ፤ ብዙዎቹ ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና።»

ብዙ ልሳኖች ትርጉማቸው ሲመረመር ክርስቶስን የሚረግሙ ሆነው የመገኘታቸው ሁኔታ ሲታይ ዲያብሎስ በዚህ መስክ ሰውን ለማሳሳት ከፍተኛ ርብርቦሽ በማካሄድ ላይ መሆኑን ይጠቁማል።

አቤት ውሸት! ያውም ረቂቅ ውሸት! የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በልምምድ የሚገኙ አይደሉም። ቀደምት ነቢያትና ሐዋርያት ሁሉን የሚችለውን አምላክ ለመኑ እንጂ «እንዲህ እንዲህ በል!» ተብለው አልሠለጠኑም። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በእግዚአብሔር ፈቃድ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም የሚሰጥ እንጂ ሰዎች በልምምዳቸው የሚያገኙት ወይም የሚቀበሉት አይደለም። በመሠረቱ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትና መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠውን ልዩ ልዩ ስጦታ በተግባር መግለጥ የተለያዩ መሆናቸውን መገንዘብ ይኖርብናል። ለማንኛውም 1ኛ ቆሮ. 12 እና 13ን ልብ አድርገው ያንብቡ።

በክርስቲያኖች ላይ የሚጫወቱ ክፉ ሠራተኞች

አንዳንድ ሰዎች በአማኞች ላይ የተመኙትን ነገር ሁሉ ሊለማመዱ ይፈልጋሉ። ክቡር የሆነውን የጌታን ስም ጠርተው፥ ጊዜ ወስነው «ይህ ይሆናል» ወይም «ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ‹እንዲህና እንዲህ አደርጋለሁ› ብሏል» ብለው በብዙ ሰዎች ፊት ትንቢት ይናገራሉ። ነገር

ግን ሳይሆን ይቀራል። እንደዚህ የሚሉ ሰዎች ክቡር የሆነውን የጌታ ስም አጉድፈው፣ በማያምኑ ሰዎች ዘንድ አሰድበው፥ ይህ የተሰፋ ትንቢት የተነገረላቸውን ሰዎች እምነት በጥርጣሬ ጥለው፥ የወደፊቱን ተስፋቸውንም የሚያጨልሙ የማይታመኑ ነቢያት ናቸው። እነርሱ ሰው ሳያውቃቸው ለሰይጣን ተቀጥረው የሚሠሩ ከፉ ሠራተኞች ሳይሆኑ ይቀራሉ?

አቤት ውሸት!

ስለ መንፈሳዊነት ግድ የሌላቸው ሰዎች

አንዳንድ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር መለኮታዊ ትእዛዞች፥ ማስጠንቀቂያዎችና ተስፋዎች ምንም ደንታ ሳይኖራቸው «ክርስቲያኖች ነን» የሚሉ ናቸው። እነርሱ ለቤተ ክርስቲያን የልማት ሥራ (አጥር ለማጠር፥ እንግዳ ለመቀበል፥ ገንዘብ ለማዋጣት... ወዘተ) በአጭር ታጥቀው ይነሣሉ። ነገር ግን እውነትን ተናግረውና ትክክለኛ ሥራ ሠርተው፥ ቅን ነገር አስበውና አድርገው፥ በፍቅር ክርስቶስን መስለው መኖር የሚገባቸውን ዋናውን የሃይማኖት ሥነ ምግባር ችላ ይላሉ። እነርሱ በትክክል የጌታ ቤተሰቦች ሳይሆኑ ዝም ብለው የጌታን ቤት ሥራ የሚረዱ እንግዶች ናቸው። ይህም የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ በውስጣቸው ሆኖ አነሣሥቷቸው ሳይሆን፥ ለሳይን የሚያምር፥ በሰዎች ዘንድ የሚያስመሰግንና የሚያስከብር መልካም ሥራ ነው ማለት ነው።

ስለዚህ ብዙ ሰዎች የእነርሱን ልብ ስለማያውቁ እነርሱን ከፍ አድርገው ያመሰግኑዋቸዋል። በእምነታቸው ልል የሆኑ ሰዎች የእነርሱን ሁኔታ ያሞጋግሳሉ።

የእንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች ውሸት ከሌሎቹ ውሸት የከፋ ነው። ምክንያቱም በውስጣቸው የመንፈስ ፍሬ ባይኖርም እነርሱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሾሙ (ሊመረጡ) ይታገላሉ። አብዛኛዎቹ ሰዎች ቊሳዊ ፍላጎታቸውን ከመንፈሳዊ ሕይወታቸው አስበልጠው በሚያዩበት በአሁኑ ከፋ ዘመን የእነዚህ ዓይነት ውሸተኞች በቤተ ክርስቲያን መገኘት ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ዕድገት ፀር ነው። ምናልባት እነርሱ በቤተ ክርስቲያን በኃላፊነት ደረጃ ተመርጠው ቢቀመጡ የሚመሩዋቸውን ሕዝብ ከራሳቸው የከፉ ሥጋውያን እንዲሆኑ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ስለዚህ መንፈሳዊ ዓይኖቹ የተከፈቱለት ማንም ሰው በምርጫ ወቅት ዓይኑ እያየ ቤተ ክርስቲያንን ለዚህ ዓይነት አደጋ መዳረግ የለበትም። እነዚህ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ርኩሰትን አሹልከው ሊያስገቡና ቢያውቁም ባያውቁም የእግዚአብሔርን ቊጣ በሕዝብ ላይ ሊያመጡ ወይም መንፈስ ቅዱስ በዚያ ቤተ ክርስቲያን (አንድነት) እንዳይሠራ ዕንቅፋት ሊሆኑ ስለሚችሉ ይህ ታውቆ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምርጫ ጊዜ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ምክንያቱም በሥጋዊነት መንፈስ ቅዱስን እየተጋፉና እያሳዘኑ በረከት ይመጣል ብሎ መጠበቅ ሞኝነት ነውና።

መደምደሚያ

ውሸት ምንድን ነው? ዋሽቶ መናገር፥ ፈጥሮ ተናግሮ ማታለል፥ ውሸትን ማውራት (የሐዋ. 5፡3–4) ነው። የመዋሸት የመጀመሪያ ዓላማ አታልሎ ጥቅምን ለማስጠበቅ ነው። ውሸት የተናገሩት ቃል ብቻ አይደለም። በውሸት አስመስሎ መሥራት፥ ከፉ እያደረጉ መልካም ለመባል መጣር፥ የሆድን በሆድ ይዞ በጥርስ ማታለል፤ እነዚህ ሁሉ

ውሸት በሥራ ላይ ሲውል የሚታዩ ምልክቶች ናቸው (ኤርምያስ 23፡14)። ሰው በስውር የሚያደርገውን ነገር ጌታ ያያልና።

የማይገባውን ማድረግ፥ ለጣዖት መስገድ (ኢሳ. 59፡4)፥ በውሸት በዘዴ ማሳመን (ሮሜ. 3፡7)፥ ከእውነት ጋር የማይጣጣም ነገር ሁሉ (1ኛ ዮሐ. 2፡21)፥ የኢየሱስን ጌትነት መካድ (1ኛ ዮሐ. 2፡22)፥ እነዚህ ሁሉ ውሸቶች ናቸው።

የውሸት መነሻና መሠረቱ ሰይጣን ነው (ዮሐ. 8፡44፤ የሐዋ. 5፡3)። ከውሸት ሁሉ ለመጀመሪያ የተመዘገበው ሰይጣን ሔዋንን ያታለለበት ውሸት ነው (ዘፍጥ. 3)።

ውሸት የኃጢአት ውርስ ነው፡– ትውልድ ሁሉ በዚህ ኃጢአት የተበከለ ነው። «ጎጥአን ከማሕፀን ጀምረው ተለዩ፤ ከሆድም ጀምረው ሳቱ፤ ሐሰትንም ተናገሩ» [መዝሙር (58)፡3]። ውሸት የመጀመሪያው አዳም አሮጌ ሰውነት ነው (ቆላ. 3፡9)። ይህን አውልቀው እንዲጥሉ ቅዱሳን ተጠርተዋል። ውሸተኞች በገሃነመ እሳት ይቃጠላሉ (ራእይ 21፡8)።

እግዚአብሔር ውሸትን አጥብቆ ይጠላል። ቅዱሳንም ውሸትን እንዲጠሉ ተጠርተዋል (ምሳሌ. 13፡5)። ውሸትን ከአጠገባቸው ሊያርቁ (ሶፎ. 3፡13)፥ ውሸተኞችን ላይነኩና ከእነርሱ ጋር ላይተባበሩ ተጠርተዋል [መዝ(40)፡4፤ (101)፡7]፤ ከውሸት ለማምለጥ (ለመትረፍ) ሊጸልዩ [መዝ (119)፡29] ተጠርተዋል።

ክፉዎች ሊዋሹ ይወዳሉ [መዝ. (52)፡3]፤ በውሸት ይደሰታሉ (መዝ (62)፡4)፤ ሐሰትን ይሻሉ [መዝ. 4፡2]፤ ሐሰተኛ የተንኰለኛን ምላስ ያዳምጣል (ምሳሌ. 17፡4)።

መዋሸት ከሁሉም ወደ ከፋ ወንጀል ይመራል (ሆሴዕ 4፡1–2)። የውሸተኞች ቅጣት ከሁሉም የከፋ ነው። ውሸተኞች በፍጹም መንግሥተ ሰማያት አይገቡም (ራእይ 21፡17፤ 22፡15)።

የውሸተኞች ቅጣት፡– ይህንን ኃጢአት የሚፈጽሙ በገሃነመ እሳት ይጣላሉ (ራእይ 21፡8)። ሐናንያና ሰጲራ ዋሽተው ሁለቱም ሞቱ (የሐዋ. 5፡1–11)። ውሸተኞችን ጌታ ያጠፋቸዋል (መዝ. 5፡6)። ውሸተኛ ሳይቀጣ አያመልጥም (ምሳሌ 19፡5)። አዎን ውሸተኞችን ሰይፍ ይበላቸዋል (ኤር‌ም. 50፡36)። ውሸተኞች እግዚአብሔርን በቅንነት ሊያመልኩ አይችሉም [መዝ (24)፡3፥4]።

የጌታ ቃል መዋሸት ክፉ እንደሆነና የሚያስቡት ሰዎችም መዘዝና ቅጣት እንደሚያገኙ በግልጽ ያስረዳል።

እነዚህን ጥቅሶች በጥንቃቄ ማንበብ የውሸትን መጥፎነት ግልጽ ያደርጋል። አንዳንድ ጊዜ በውሸት ውስጥ ግማሽ እውነት አለ። ለምሳሌም ሰይጣን ሔዋንን ያታለለበትን ውሸት (ዘፍጥ. 3)፥ እና የቃየልን ውሸት (ዘፍጥ. 4፡9) ማየት ይቻላል። እነዚህ ሰዎች በጠየቃቸው ጊዜ የሰጡት ምላሽ ከቀጣው ለማምለጥ የተናገሩት ማስተባበያ ነው። ያዕቆብ የታላቅነትን በረከት ለራሱ ለማድረግ የዋሸው ውሸት አውቆና ዐቅዶ የዋሸው ውሸት ነው (ዘፍጥ. 27፡19)። የዮሴፍ ወንድሞች አባታቸው ያዕቆብ ስለ ዮሴፍ ደኅንነት በጠየቃቸው ጊዜ የሰጡት ምላሽ

እነርሱ በልባቸው የቀበሩት ከፋት ገሃድ በመውጣቱ ያንን ለመሸፈን ያቀነባበሩት ውሸት ነበር (ዘፍጥ. 37፡31–32)።

አንዳንድ ጊዜ ጥሩ ሰውም ይዋሻል። ይሁን እንጂ ቢዋሹም ምንም ለውጥ አያመጣም። ቅዱሳን እውነትን የሚከተሉ ናቸው ስለሚባሉ እነርሱ ቢዋሹ ግን በጣም ያስነውራል (ዳዊትን በ1ኛ ሳሙ. 21፡2 ተመልከት)። የጌታ ባርያ ኤልሳዕ ፈውሶ በንፃ ያስናበተውን የሶርያዊውን የንዕማንን ገንዘብ ተመኝቶ ንዕማንን ከሄደበት መልሶ ገንዘብ ስለወሰደው ስለ ግያዝ የተጻፈው ውሸት ቢነበብ ምንኛ አስደንጋጭ ነው! ኤልሳዕ እርሱን፥ «የንዕማን ለምጽ በአንተ ላይ፥ ለዘላለምም በዘርህ ላይ ይጣበቃል አለው። (ግያዝ ሰውነቱ) እንደ በረዶም ለምጻም ሆኖ ከእርሱ ዘንድ ወጣ» (2ኛ ነገሥት 5፡22–27)። እንደዚሁም ጴጥሮስ «የኢየሱስ ደቀ መዝሙር አይደለሁም» ብሎ የዋሸውን ውሸት ሲመለከቱት በኢየሱስ ተከታዮችም ውስጥ መዋሸት ሊኖር መቻሉ ለመናገር የሚያሳፍር ነው። እርሱ ጌታን «አላውቀውም» ማለት ብቻ ሳይሆን «አላውቀውም» ብሎ አጥብቆ ማለ (ማቴ. 26፡72)።

አንዳንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን ለሌላ ሰው የሚናገር አድርጎ ያስባል። እርሱም ያንን መጽሐፍ (ቃል) ለሌላ ሊናገር ይጣደፋል እንጂ ለራሱ ሊያደርግ ወይንም እንደ ቃሉ ሊኖር አይፈልግም። ተረድቶ ሊከተለው ወይም ራሱን ሊጠብቅበት የተጻፈውን ምሳሌ እንደ ተረት ይቆጥረዋል። የእርሱ ሩጫና እሽቅድድም የጌታን ቃል ከሚያውቁት ዘንድ አዋቂ ሊባል እንጂ «በቅድሚያ እኔ ልታዘዝ» በሚል መንፈስ አይደለም።

እኔም በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ካለው እውነት አስቀድሜ በየዕለቱ ሰው እየዋሸ የሚውለውን ውሸት የጻፍሁት በዚህ ምክንያት ነው።

ከጥቃቅን ጨው ጀምሮ እስከ ብዙ ብር፥ ለጓደኛችን ለምንዋሸው ከትንሽ ጉዳይ አንሥቶ እስከ ነፍስ ጉዳይ ድረስ እንደሚያድግ ሁሉ እኛ የምንዋሸው ውሸትም እንደዚሁ ትልቅ ኃጢአት እንደሚሆን አውቀን፥ «የጠራን ቅዱስ እንደ ሆነ» ሁሉ እኛም ቅዱሳን ሆነን እንድንኖር ጌታ ይርዳን።

ማስታወሻ፦

የመደምደሚያውን ጽሑፌን ሚስተር ውልያም ኢቫንስ ከጻፉት ጽሑፍ ስለ ተጠቀምኩ ምሥጋናዬ ይድረሳቸው።

በእውነት እንደዚህ ይላሉ?

☐ ያለ ዮሴፍ ስሚዝ (*JOSEPH SMITH*) ደኅንነት አይገኝም

☐ እግዚአብሔር አስቀድሞ ሰው ነበረ

☐ ሰው አምላክ መሆን ይችላል

☐ ኢየሱስ በአሜሪካ በአካል ታየ

☐ በሌሎች ዓለማት (*PLANETS*) ላይ አግልክት አሉ

☐ እግዚአብሔር ሚስት አለው

☐ ጥሮር ሰዎች ሁሉ እስከ 1971 ዓ.ም. ድረስ የተረገሙ ነበሩ

ሞርሞኖች (*MORMONS*) ከዚህ በላይ የተጻፉትን ነገሮች በእርግጥ ያምናሉን? ሞርሞኖች «*ELDER*» (ሽማግሌ) ወይም «*SISTER*» (እኅት) የሚሉ የመታወቂያ ምልክቶች ያሉባቸውን ነጭ ሸሚዞች እየለበሱ፥ ሁለት ሁለት ሆነው ሊዘዋወሩ በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ይታያሉ። እንግዲህ ትምህርታቸውን ለማወቅከፈለጉየሚከተለውንያንብቡ።



ያለ ዮሴፍ ስሚዝ ደኅንነት የለምን?

የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን «የኢየሱስ ክርስቶስ

የመጨረሻ ዘመን ቅዱሳን ቤተ ክርስቲያን (*THE CHURCH OF JESUS CHRIST OF LATTER-DAY SAINTS*)» ትባላለች። ሞርሞኖች ስለ ደኅንነት «ዮሴፍ ስሚዝ ባይመጣና ቤተ ክርስቲያን እንደገና ባትተከል ኖሮ ደኅንነት አይገኝም ነበር። ከኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻ ዘመን ቅዱሳን ቤተ ክርስቲያን ውጭ ደኅንነት አይገኝም» ይላሉ፤ ይህም የተጻፈው ከታወቁ የሞርሞን ሊቃውንት መካከል አንዱ ባዘጋጀው ዋና የሞርሞን መዝገበ ቃላት ነው (1)።

የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን መሥራች ዮሴፍ ስሚዝ በ1813 ዓ.ም. የአሥራ አራት ዓመት ወጣት ሳለ፥ እግዚአብሔርና ኢየሱስ በራእይ እንደተገለጡለት በአንክሮ ተናገረ። ስሚዝ እንደተረከው፥ እግዚአብሔር ሌሎች አብያተ ክርስቲያን «የተሳሳቱ»፥ «የሃይማኖታቸው ሥርዓት ሁሉ አስጸያፊ» እና «መምህራኖቻቸውም ሁሉ የተበላሹ» መሆናቸውን ገለጠለት (2)።

በዚህና በሌሎች «መገለጦች» ሞርሞኖች የክርስትና ሃይማኖት ከኢየሱስና ከሐዋርያት ትምህርት በፍጹም እንደወጣ ሲያስተምሩ፥ ከሐዋርያት ሞት ጀምሮ የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን በ1823 ዓ.ም. እስከትመሠረት ድረስ እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ወይም እውነተኛ ክርስቲያን እንዳልተገኘ ለማሳመን ይሞክራሉ።

ሞርሞኖች፥ እግዚአብሔር እውነተኛይቱን ቤተ ክስቲያን እንደገና ለመትከል በፈለገ ጊዜ፥ ዮሴፍ ስሚዝን ነቢዩ እንዲሆን የጠራው መሆኑን ያምናሉ። እግዚአብሔር በ«መገለጥ» የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን «በዓለም ሁሉ ብቸኛ፥ እውነተኛና ሕያው ቤተ ክርስቲያን» መሆንዋን አረጋገጠለት (3)።

<u>እግዚአብሔር አስቀድሞ ሰው ነበረን?</u>

እንደ ሞርሞኖች ትምህርት እግዚአብሔርና ሰዎች ሁሉ በዚህ ዓለም ከመገኘታቸው በፊት አስቀድመው መናፍስት ነበሩ። የዓለማችን አምላክ ከሌላ አምላክና ከሚስቱ ተገኘ፤ ሊሞት እንደሚችል እንደማንኛውም ሰው ተወለደ፥ በትክክለኛና ትርጕም ባለው ሕይወት ኖሮ ከሞቱ በኋላ አምላክነትን አገኘ።

ሞርሞኖች እንደሚያስቡት «በሚሞቱት ሰዎች ከተሰጡት ታላላቅ ስብከቶች በአንዱ»(4) ዮሴፍ ስሚዝ «እግዚአብሔር ራሱ አሁን እኛ እንዳለን ነበረ፥ አሁንም የከበረ ሰው ሆኖ ሩቅ ባሉት ሰማያት ተቀምጦ ይነግሣል! ... እግዚአብሔር ከዘላለም እግዚአብሔር እንደነበረ ስናስብ ኖረናል። ይህ ስሕተት መሆኑን አላያለሁ፤ እንድታስተውሉም ከዓይናችሁ መጋረጃውን አስወግዳለሁ ... የሁላችን አባት እግዚአብሔር ራሱ በአንድ ዓለም ኖረ» ብሎ ሰበከ (5)።

ሰው አምላክ ሊሆን ይችላልን?

በሞርሞን ትምህርት መሠረት ሰው አምላክ ሊሆን ይችላል። «ሰው አሁን እንደሚሆነው እግዚአብሔር ነበረ፤ እግዚአብሔር አሁን እንደሚሆነው ሰው ሊሆን ይችላል»። ይህ ትምህርት «ዘለዓለማዊ ሥርፀት (ETERNAL PROGRESSION)» የሚባል ሲሆን ለሞርሞን አስተሳሰብ መሠረታዊ መርህ ነው።

ዮሴፍ ስሚዝ «እናንተ ራሳችሁ አማልክት ለመሆን መማር አለባችሁ ... ከእናንተ በፊት ሁሉም አማልክት እንዳደረጉት ግለትም ከአንድ ትንሽ ደረጃ ወደ ተሻለና እንደዚሁም ከአንድ ዝቅተኛ ችሎታ ወደ ከፍተኛው በመሸጋገር ... በፊት እንደቀደሙአችሁ በመጨረሻ ወደ አምላክነት ከብር በመድረስ ወደ ዘላለም ኃይል ዙፋን ወጥታችሁ ትቀመጣላችሁ» አለ (6)።

በዚህ ትምህርት መሠረት ተገቢውን ሕይወት የሚኖርና የሞርሞንን መቅደስ ሥርዓት ሁሉ የሚፈጽም በሚቀጥለው ሕይወት አምላክ ይሆናል። እዚያም እግዚአብሔር አብ እንዳደረገልን ሁሉ (ከዚህ በፊትም የእግዚአብሔር አባት እንዳደረገው ... ወዘተ) መንፈሳዊ ልጆችን ወልዶ በርቀት የሚገኙትን ዓለማት በሕዝብ መሙላት ይችላል (7)። ይህ ሂደት ለዘላለም እየተከታተለ ይቀጥላል፤ ይኸውም አዲስ አማልክት ⟶ አዲስ

ዓለማት ⟶ አዲስ አማልክት ⟶ አዲስ ዓለማት ⟶ ወዘተ።

በሌሎች ዓለማት (PLANETS) አማልክት ይገኛሉን?

እንደ ሞርሞኖች ትምህርት እግዚአብሔር ኮሎብ ከተባለው ኮከብ አጠገብ ይኖራል። ይህም ከሞርሞን ቅዱሳት መጻሕፍት በአንዱ የተረጋገጠ ሌላው የዮሴፍ ስሚዝ ግኝት ነው (8)።

እግዚአብሔር አብ ግን ከብዙ አማልክት መካከል አንዱ አምላክ ብቻ ነው። እርሱም የዚህ ዓለም ዋና አምላክ ሲሆን፥ ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ ሁለት ሌሎች ልዩ አማልክት ናቸው (9)። በሌሎች ዓለማት ሊቈጠሩ የማይችሉ ሌሎች አማልክት አሉ። ዮሴፍ ስሚዝ «የአማልክት ራስ የሆነው በመጀመሪያ የአማልክትን ጉባኤ ጠራ፥ በአንድነት ተሰብስበውም ዓለምን ለመፍጠርና በሰዎች ለመሙላት ዕቅድ አዘጋጁ» አለ (10)።

እግዚአብሔር ሚስት፥ ሥጋና ደምስ ያለው አካል አለውን?

እንደ ሞርሞን ትምህርት ሰዎች ሁሉ በዚህ ምድር ከመወለዳቸው በፊት መንፈስ ሆነው ይኖሩ ነበር። እነዚህ መናፍስት በእግዚአብሔር አብና አምላክ በሆነች ሚስቱ መካከል ባለ ግንኙነት የተገኙ ናቸው። እግዚአብሔር ቁሳዊ ነውና ብቻውን ልጆች ሊኖሩት አይችሉም። የሞርሞን ዋና

መዝገበ ቃላት «በሰማይ አንድ እናት ትኖራለች» የሚለው ትምህርት፥ ዮሴፍ ኤፍ ስሚዝ፥ ዮሐንስ ውንደርና አንተን ኤች ሉንድ በጋራ በመሩበት በመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በግልጥ ታወጀ፤ እነዚህ መሪዎች ስለ ሰው አስቀድሞ መኖርና መገኘት ሲናገሩ፥ «ሰው እንደ መንፈስ ከሰማያዊ ወላጆች ተጸንሶ ተወለደ» እንደዚሁም «ወንዶችና ሴቶች ሁሉ የሁሉን አባትና እናት ይመስላሉና በእውነት ከመለኮታዊ ባሕርይ የተገኙ ወንድና ሴት ልጆች ናቸው» ይላሉ (11) በማለት ይናገራል።

ለዮሴፍ ስሚዝ ነበረው በተባለው በአንድ «መገለጥ»፥ «እግዚአብሔር አብ ሥጋና አጥንት የተዋሐደው አካል አለው፥ አካሉም እንደ ሰው የሚዳሰስ አካል ነው» ተብሎ ይነገራል (12)።

እስከ 1971 ዓ.ም. ድረስ ጥቁር ሕዝቦች ሁሉ የተረገሙ ነበሩን?

በ«የሞርሞን መጽሐፍ» አንዳንድ ሰዎች በመሪአቸው በነፊ ላይ ስላመፁ፥ እግዚአብሔር «መርገምን፥ ይልቁንም ከባድ መርገምን አመጣባቸው ... ጌታ እግዚአብሔር ጥቁር ቆዳን እንዲለብሱ አደረገ» በተሰኘው ቅጣት እንደቀጣቸው እናነባለን (13)።

ሌላው ቅዱስ የተባለው የሞርሞን ጽሑፍ «በከነዓን ልጆች ሁሉ ላይ ጥቁርነት መጣና በሕዝቦች ሁሉ ዘንድ

ተነቀፉ» (14)፤ ደግሞም ለእነዚህ የከነዓን ልጆች «በአገሩ ላይ መርገምን ያቆየው ዘር» ተወለደ ይላል (15)።

በ1971 ዓ.ም. የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን ፕሬዚዳንትና ነቢይ፥ ጥቁሮችና ሌሎች ነጭ ያልሆኑት ሰዎች ከሞርሞን መብቶች እንዳይከለከሉ ከእግዚአብሔር «መገለጥ» ተሰጠው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጥቁሮች ወደ ሞርሞን ክህነት መግባት፥ በቤተ መቅደስ ሥርዓት መሳተፍ፥ ሰማያዊ ጋብቻን መፈጸም፥ አማልክት መሆን ... ወዘተ ችለዋል። ከዚያ ጊዜ በፊት ግን እነዚህን መብቶች ሁሉ ለማግኘት አይፈቀድላቸውም ነበር።

ኢየሱስና ሰይጣን ወንድማማቾች ናቸውን?

እንደ ሞርሞን ትምህርት ኢየሱስና ሰይጣን እንደ ሰዎች ሁሉ ቅድመ ሕይወት ተብሎ በሚጠራው አማካይነት ከ«ሰማያዊ እናት» ተወለዱ፤ ስለዚህ ኢየሱስና ሰይጣን ወንድማማቾች ናቸው። ኢየሱስ ከሰይጣን የሚለየው የሰማያዊ ወላጆች የመጀመሪያ መንፈሳዊ ልጅ በመሆኑ፥ ደግሞም እርሱ ከመንፈሳዊ ወንድሞች ሁሉ መካከል የዚህ ዓለም አዳኝ እንዲሆን «በሰማያዊ ጉባኤ» በመመረጡ ነው (16)።

በሥጋዊ በኩልም እንኳ ሳይቀር እግዚአብሔር አባቱ በመሆኑ፥ ኢየሱስ የሚሞት ሰው ቢሆንም የእርሱ ሁኔታ በምድር ላይ ለየት ያለ ነበረ፤ የሞርሞን ዋና መዝገበ ቃላት እንደሚለው «የሚሞቱ ሰዎች ከሚሞቱ አባቶች

እንደሚወለዱ ሁሉ፥ ክርስቶስም ከማይሞት አባቱ ከእግዚአብሔር ተወለደ» (17)። እግዚአብሔር ሥጋና ደም ሆኖ ወደ ምድር በመውረድ በሥጋ ከማርያም ጋር ከተገናኘ በኋላ ወደ ሰማይ እንደተመለሰ ሞርሞኖች ያምናሉ። በዚህ አስተሳሰብ መሠረት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ማርያም በድንግልና አልነበረችም።

<u>የሚድኑት ባለ ትዳሮች ብቻ ናቸውን?</u>

በሞርሞንትምህርትመሠረት ለሰው በ «ዘላለም ሥርፀት» ማለፍና ወንድ አምላክ ወይም ሴት አምላክ ለመሆን ለዘላለም የሚጸና ሰማያዊ ጋብቻ ያስፈልገዋል (18)። እነዚህ ጋብቻዎች በልዩ ሥነ ሥርዓት በሞርሞን መቅደሶች ይፈጸማሉ።

ያለ ሰማያዊ ጋብቻ ሰው ወደ ሙሉ መዳን ሊደርስ አይችልም (19)፤ ምክንያቱም እንደ ሞርሞን ትምህርት ሦስት ሰማያት አሉና (20)። ከፍ ባለው ሰማይ ወንዶች አማልክትና ሴቶች አማልክት የሆኑ ይኖራሉ። በወሲባዊ ግንኙነት አዲስ ዓለማትን የሚሞሉትን መንፈሳዊ ልጆች ይወልዳሉ። በዚህ ሰማይ መንፈሳዊ ጋብቻን ያልተቀበሉት ሌሎች ሞርሞኖች ደግሞ ይኖራሉ፤ እነርሱም ልጅ ሳይወልዱ መላእክት ሆነው አማልክትን ያገለግላሉ።

ከዓለም ሕዝብ የሚበዙቱ በሌሎች ሁለት ሰማያት ይኖራሉ። አንዱ ሞርሞኖች ላልሆኑ ለመልካም ሰዎች፥ ሌላው ደግሞ ለክፉ ሰዎች ይሆናል።

በ1883 ዓ.ም. ሞርሞኖች በምድር ብዙ ሚስቶችን ከማግባት ተቆጠቡ፤ በሰማያዊ መንግሥት ግን ከአግልክት ብዙዎቹ ብዙ ሚስቶች ይኖሩአቸዋል።

<u>ኢየሱስ በአሜሪካ በአካል ታይቷልን?</u>

በ«የሞርሞን መጽሐፍ» ከሚገኙት ታላላቅ ትምህርቶች አንዱ፥ ኢየሱስ ከሞቱና ከትንሣኤው በኋላ ለአሜሪካ ሕዝብ መታየቱ ነው። በዚያን ጊዜ ሰዎች ሁሉ አምነው ተጠመቁ። በ«የሞርሞን መጽሐፍ» አገላለጥ መሠረት እነዚህ ሰዎች 600 ዓመታት ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ አሜሪካ ከፈለሱት መካከል የተገኙ የአይሁድ ዝርያዎች የሆኑ የአሜሪካ ሕንዶች ነበሩ። አንድ ነቢይ በወርቅና በነሐስ ጽላቶች ላይ ታሪካቸውን ጽፎ በ415 ዓ.ም. በመሬት ደበቃቸው (ሞርሞኖች ኮሎምበስ ከአንድ ሺህ ዓመታት በኋላ ወደ አሜሪካ በደረሰ ጊዜ ከነዚህ ሕዝቦች ዝርያዎች ጋር እንደተገናኘ ያምናሉ)።

እንደ ዮሴፍ ስሚዝ «አንድ ሰማያዊ መልእክተኛ» በ1816 ዓ.ም. ለእርሱ ታይቶ ወርቃማ ጽላቶቹ የተደበቁበትን አሳየው። ከአንድ ካልታወቀ ከ«ታደሰ ግብጽ ቋንቋ» ጽላቶቹን «ተረጐመ»፤ በኋላም ለወሰዳቸው መልእክተኛ መልሶ ሰጠው። በ1823 ዓ.ም. ይህ «ትርጉም» «የሞርሞን መጽሐፍ» በመባል ታትሞ ወጣ።

****

ከ«የሞርሞን መጽሐፍ» ጋር የሚዛመዱ ብዙ ችግሮች አሉ፤ ከእነዚህም የሚከተሉት ጥቂቶች ናቸው፡-

1. «የሞርሞን መጽሐፍ»ን ታሪክና እንደ ትምህርቱ በአሜሪካ አህጉር ሁሉ የነበሩ ታላላቅ ሥልጣኔዎችን የሚያረጋግጥ በአርኪዎሎጂ ጥናት የተገኘ አንድ እውነተኛ ቅርስ እንኳን አልተገኘም።
2. «የሞርሞን መጽሐፍ» እንደሚለው በአሜሪካ ከሺህ ዓመት በላይ የዕብራይስጥና «የታደሰ ግብጽ» ቋንቋ ጥቅም ላይ እንደዋሉ የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ማስረጃ ያገኘ ሰው የለም።
3. ከዚህ በላይ እንዳየነው «የሞርሞን መጽሐፍ» የአሜሪካ ሕንዶች የአይሁድ ፈላሻዎች ዝርያዎች መሆናቸውን ቢናገርም፥ ዘመናዊ የሰው ዘር ጥናት ተመራማሪዎች፥ የአሜሪካ ሕንዶች ከአይሁድ ሕዝብ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌላቸውና ከምሥራቅ እስያ ሕዝቦች ጋር እንደሚዛመዱ ያለ አንዳች ጥርጥር ያረጋግጣሉ።

የሞርሞን ሃይማኖት እንደ ክርስትና ሊቆጠር ይችላልን?

ሞርሞኖች ራሳቸውን ክርስቲያኖች እንደሆኑ ብዙ ጊዜ ያሳውቃሉ። በመጀመሪያ ደረጃ እምነታቸው ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ይመስላል፤ ምክንያቱም ስለ ኢየሱስ፥ እግዚአብሔር፥ ንስሓ፥ እምነት፥ ደኅንነት ... ወዘተ ይናገራሉ። ሆኖም ለነዚህ ቃላት የሚሰጡት ትርጉም ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ፍጹም የወጣ ነው።

ሞርሞኖች የክርስቲያን አብያተ ክርስቲያን «የተሳሳቱ» ሳይሆኑ «የተሟሉ» አይደሉም ይሉናል፤ ይህ ግን የቃላት ጨዋታ ብቻ ነው፤ ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብዙ ነገሮችን መጨመር ብቻ ሳይሆን፥ የክርስትናን ሃይማኖት ሁሉ በተለየ አኳኋን ተርጉመው የሚለውጡት ናቸውና። የሞርሞን «ወንጌል»፥ የሞርሞን እግዚአብሔር (አማልክት)ና የሞርሞን ኢየሱስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ እጅግ የተለዩ በመሆናቸው የሞርሞን ሃይማኖት ፍጹም ልዩ ሃይማኖት እንጂ በክርስትና ውስጥ ያለ አንድ ዘርፍ አይደለም። ይህንም ለመረዳት የሚከተሉትን አንቀጾች ያንብቡ።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

ስለ ዓለም ጠቅላላ ሁኔታ የሞርሞን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስን ፍጹም እንደሚቃረን ግልጥ ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሰው አምላክ ለመሆን ያለው ፍላጎት የውሸት ሁሉ አባት ከሆነው ከሰይጣን ይመነጫል (22)። ቅዱስና መሐን የሌለው እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው። ሰው ግን ውሱንና ኃጢአታዊ ፍጡር ነው። እግዚአብሔር ፍጹም አምላክ ነውና የሚተካከለው ወይም የሚመሳሰለው አንድም አይገኝም። «እግዚአብሔር በላይ በሰማይ

በታችም በምድር አምላክ እንደሆነ፥ ሌላም እንደሌለ ዛሬ እወቅ» (23)።

የሞርሞን ሃይማኖት አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠው እግዚአብሔር አይደለም። ኢየሱስ «እግዚአብሔር መንፈስ ነው» ብሎ በግልጥ አስተማረ (24)። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሥጋና አጥንት ባለው አካል ተገኝቶ የከበረ ሰው መሆኑን በግናቸውም አንቀጽ አያስተምርም። በተቃራኒ እግዚአብሔር ለዘላለም የሚኖርና የማይወሰን መሆኑን ብዙ ጊዜ ያውጃል። እርሱ «ከዘላለም»፥ «ሕያው አምላክና ለዘላለም ንጉሥ»፥ «አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያና መጨረሻ» እና «ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ» ነው ይላል (25)።

ከመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ሐቆች አንዱና ክርስቲያኖች በየክፍለ ዘመናቱ ያረጋገጡት አንድ እግዚአብሔር ብቻ እንዳለ ነው። ይህንም ለማሳየት ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጥቅሶችን መጥቀስ ስንችል የሚከተሉት ሦስቱ ሐሳቦች ለአሁኑ ሊበቁን ይችላሉ፦ «እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም»፤ «እኔ አምላክ ነኝና ከእኔም በቀር ሌላ የለምና»፤ «እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ» (26)። ሞርሞኖች እንደሚያደርጉት ብዙ አማልክት መኖራቸውን ማስተማር ዓረማዊነት እንጂ ክርስትና አይደለም።

«እግዚአብሔር ሚስት አለው፥ ኢየሱስ የሰይጣን ወንድም ነውና በወሲባዊ ግንኙነት የእግዚአብሔርና የማርያም ሥጋዊ ልጅ ነው» ስለሚሉት የሞርሞኖች ትምህርቶች ሐተታ አያስፈልግም፥ የመጽሐፍ ቅዱስንና የክርስትናን ትምህርት ፍጹም ይቃረናሉና።

በመጨረሻ ስለ «ሰማያዊ ጋብቻዎች» እና ስለ ጥምቀት መረገም የሚሰጠው የሞርሞን ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘርን ወይም የጋብቻ ሁኔታን ሳይመለከት ሰዎች ሁሉ ከመጀመሪያ ጀምሮ በእኩልነት ደኅንነትን ማግኘት እንደሚችሉ ገልጧል፤ ይህም ወደ ነጻነት የሚመራ እምነት ነው፤ እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያደላምና (27)።

ይህ አንስተኛ ጽሑፍ ለምን ተጻፈ?

ጽሑፉ ሞርሞኖችን በተለይ ለማጥቃት የተጻፈ አይደለም፤ ብዙዎችም በእርግጥ ቸሮችና ሕይወታቸውን ለእምነታቸው የሰጡ ሰዎች ናቸውና። ቢሆንም ብዙ ሰዎች የሞርሞን ትምህርት ምን እንደሆነ ባለማወቃቸው ከመሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ጋር ከሚጋጩ ብዙ የሞርሞን ትምህርቶች የተወሰኑትን ለማሳወቅ ለሙከራ ያህል የተዘጋጀ ጽሑፍ ነው።

በዚህ ጽሑፍ የሰፈሩ ሐሳቦች ሁሉ የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን ካሳተመቻቸው መጻሕፍት የተወሰዱ ናቸው።

እንዳንድ የሞርሞን ሚስዮናውያን የሞርሞንን ትምህርት የሚያብራሩትን አንቀጾች አንብበዋልና ሁሉም የተጻፈው ከእምነታቸው ጋር እንደሚስማማ አረጋግጠዋል፤ ቢሆንም ከቤት ወደ ቤት ሲዘዋወሩ እነዚህን ሐሳቦች ብዙ ጊዜ በግልጥ አይናገሩም።

<u>ከዚህ ችግር አኳያ ምን ማድረግ አለብዎ?</u>

በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠውን ኢየሱስን እንደ ሕይወትዎ መድኃኒትና ጌታ እስከ አሁን ድረስ ያልተቀበሉት ከሆነ፥ አሁኑኑ ይህን እንዲያደርጉ በጥብቅ እንመክርዎታለን፤ ይህ እርምጃ ሕይወትዎን ይለውጣልና። እንደ ሰማያዊ አባት ወንድ ወይም ሴት ልጅ ለመኖር የሞርሞን እምነት፥ ቤተ ክርስቲያን፥ ክህነት፥ ጥምቀቶች፥ ነቢያት ... ወዘተ አያስፈልጉዎትም። ለእርስዎ የሚያስፈልግዎ አንድ፥ እርሱም ኢየሱስ ብቻ ነው። እውነተኛውን ኢየሱስን ማወቅ እንዲጀምሩ ከመጽሐፍ ቅዱስ አዲስ ኪዳንን ያንብቡ (28)። ሌላ እርዳታ ቢያስፈልግዎ በመጨረሻ ላይ በተገለጸው አድራሻ ይጻፉልን።

ማስታወሻ፥-

የሞርሞኖች ቅዱሳት ጽሑፎች የሚከተሉት ናቸው፥-

THE BOOK OF MORMON - የሞርሞን መጽሐፍ

THE DOCTRINE AND COVENANTS - ትምህርቱና ቃል ኪዳናች

THE PEARL OF GREAT PRICE - ዋጋዉ እጅግ የበዛ ዕንቁ መጽሐፍ ቅዱስ

1. *Mormon Doctrine, Bruce McConkie, p.670, Salt Lake City, Utah 1979*
2. *Pearl of Great Price, Joseph Smith, History 1:19*
3. *Doctrine and Covenants, 1:30*
4. *Mormon Doctrine, Bruce McConkie p 421.*
5. *Teachings of the Prophet Joseph Smith, p 345-346 Salt Lake City, Utah.*
6. *Teachings of Prophet Joseph Smith, p 346-347. see also Doctrine and Covenants, 132:20*
7. ዮሴፍ ስሚዝ እንዲህ አለ፥- «ኢየሱስ አባት ካለው፥ አባቱ ደግሞ አባት እንዳለው ማመን እንችልምን? መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ትምህርት የተሞላ ነውና ከዚህ ሐሳብ የሚነሣውን ፍርሃት እንቀፍለው» *Teachings of the prophet Joseph Smith p.373*
   የ *"MORMON Doctrine"p. 322* ደግሞ ይህን ትምህርት ያረጋግጣል።
8. *Pearl of Great Price, Book of Abraham, 3:3,9,16. Mormon Doctrine p.428* ይመልከቱ።
9. «እነዚህ ሦስቱ ሦስት ልዩ አካላትና ሦስት አማልክት ናቸው ... የሆነው ሆኖ ሦስት አማልክት አሉን፥ ብዙ ናቸውና» *Teachings of the Prophet Joseph Smith, p.370*
10. *Teachings of the Prophet Joseph Smith p 349.*
11. *Mormor Doctrine, Bruce McConkie, p.516.*
12. *Doctrine and Covenants, 130:22*
13. *Book of Mormon, 2 Nephi 5:21-23, see also 1 Nephi 12:23.*

14. *Pearl of Great Price, Book of Moses 7:8*
15. *Pearl of Great Price, Book of Abraham 1:24* ጥቅሮች ወደ ከህነት እንዳይገቡ የሚከለክለውን 1፥21-27 ደግሞ ይመልከቱ።
16. *Pearl of Great Price, Book of Abraham, 3:24-28 and Book of Moses 4:1-4 see also Mormon Doctrine, p. 164.*
17. *Mormon Doctrine, Bruce McConkie p. 547.*
18. *Doctrine and Covenants, 132:15-20.*
19. *Doctrine and Covenants, 131:1-4.*
20. *Doctrine and Covenants, 76:50-113 and 131:1.*
21. *Doctrine and Covenants, 132:61-63.*
22. ዘፍ. 3፥1-5፤ ኢሳ 14፥12-15፤ ሕዝ. 28፥1-10፤ ዮሐ. 8፥44።
23. ዘጸ. 4፥39። 24. ዮሐ. 4፥24። 25. መዝ. 92(93)፥2፤ ኦር. 10፥10፤ ራእ. 22፥13፤ መዝ. 89(90)፥2።
26. ኢሳ 44፥6፤ 45፥22፤ ዮሐ. 17፥3። ደግሞም ኢሳ 43፥10-11፤ 45፥5-6፤ ዘጸ 32፥39፤ ያዕ. 2፥19 ይመልከቱ።
27. ሮሜ 2፥11፤ ገላ 3፥28፤ ቈላስ 3፥11።
28. ምንባብዎን በዮሐንስና በሉቃስ መንጌሎች ይጀምሩ፥ እነርሱም የኢየሱስን ሕይወት ታሪክ የሚተርኩ ናቸውና።

O.BENESTAD

****

እመነተኛ ክርስቲያን ለመሆን የሚገልጽ ጽሑፍ ከፈለጉ በዚህ አድራሻ ይጻፉ፡-

የሕይወት ቤር
ፖ.ሣ.ቁ. 4937
አዲስ አበባ